# በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# ድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት

## በጎንደር ከተማ አራት አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም

አሰፉ ደሳለኝ

ሰኔ፣ 2001 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# በጎንደር ከተማ አራት አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርትቤቶች አማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም


በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት

በ

አሰፋ ደሳለኝ


ለአማርኛ ማስተማር (TeAm)

ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

ሰኔ፣ 2001 ዓ..ም

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## ድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

### በጎንደር ከተማ አራት አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርትቤቶች አማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያዎች አጠቃቀም

በ

አሰፋ ደሳለኝ

የቋንቋ ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት

የፈተና ቦርድ አባላት

______________________ ______________________

አማካሪ ፊርማ

______________________ ______________________

ፈታኝ ፊርማ

# ማውጫ


**ገጽ**

ምስጋና ........ i
አበርክቶ ........ ii
የሰንጠረዦች ዝርዝር ........ iii
የአባሪዎች ዝርዝር ........ v
አጠቃሎ ........ vi

**ምዕራፍ አንድ**
***መግቢያ ........ 1***
***1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1***
***1.2 የጥናቱ ዓላማ ........ 3***
***1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 4***
***1.4 የጥናቱ ወሰን ........ 4***
***1.5 የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ፍቺ ........ 5***

**ምዕራፍ ሁለት**
**ክለሳ ድርሳን ........ *6***
***2.1 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ምንነት ........ 6***
***2.2 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መምህራን ለምን ይጠቀማሉ? ........ 7***
***2.3 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዓይነትና አከፋፈላቸው ........ 10***
***2.3.1 የሚደመጡ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ........ 11***
2.3.2 የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ........ ***12***
2.3.3 የሚደመጡና የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ........ ***16***
2.4 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ........ ***17***
2.4.1 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የአመራረጥ መርህ ........ ***18***
2.4.2 የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥ ........ ***20***
2.4.3 የትምህርት መሣሪያዎችን ለመምረጥ የሚውሉ መመዘኛዎች ........ ***20***
2.4.4 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ባህርያት ........ ***22***
2.5 የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ........ ***22***
2.5.1 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የማቅረብ (የማሣየት) መርህ ........ ***27***
2.5.2 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ሥነልቦናዊ ሁኔታ ........ ***28***
2.5.3 በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቀቀም ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙ ችግሮች ........ ***29***

2.5.4 የሥልጠና ጉዳይ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ዙሪያ ..... 32
2.6 የቋንቋ ትምህርትን በትምህርት መርጃ መሣሪያ ለማስተማር የመምህራን ተግባር ..... 36
2.7 የቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መሣሪያዎች የቋንቋን ትምህርት በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተጠቅሞ ለማስተማር ያላቸው እገዛ ..... 37
2.7.1 የተማሪ መፅሀፍና የመምህሩ መምሪያ ..... 37
2.7.2 መርሐ ትምህርት ..... 38
2.8 ቀደምት ተዛማጅ ጥናቶች ..... 38

**ምዕራፍ ሦስት**

**የጥናቱ አጠናን ዘዴና የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ..... 40**
3.1 የናሙና መረጣና የተጠኚዎች አመራረጥ ..... 40
3.1.1 የጥናቱ ክልል የናሙና አመራረጥ ..... 40
3.1.2 የትምህርት ቤት የናሙና አመራረጥ ..... 40
3.1.3 የክፍል ደረጃ የናሙና አመራረጥ ..... 41
3.1.4 የመምህራን የናሙና አመራረጥ ..... 41
3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ..... 41
3.2.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ ..... 42
3.2.2 የቃል መጠይቅ ..... 43
3.2.3 የፅሑፍ መጠይቅ ..... 43
3.3 የመረጃዎች የአተናተን ስልት ..... 44

**ምዕራፍ አራት**

**የጥናቱ ውጤት ትንተና እና ማብራሪያ ..... 45**
4.1 የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ..... 45
4.2 የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ብቃት ..... 48
4.2.1 በአገልግሎት ላይ የዋሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተገቢነት ..... 53
4.2.2 መምህራን እውነተኛ በሆኑ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የመጠቀም ልምድ ..... 54
4.2.3 መምህራን በኅትመት ውጤቶች የመጠቀም ልምድ ..... 59

4.2.4 መምህራን በተለያዩ ሠሌዳዎች የመጠቀም ልምድ ..... 60

4.3 ታላሚ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በተመለከተ ስለአጋጠማቸውን ችግር ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ..... 60

4.4 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችና የማስተማሪያ መሣሪያዎች ..... 61

4.4.1 ለመምህራን ከቀረበው ቃለመጠይቅ ..... 62

4.4.2 ለመምህራን ከተሰራጨው የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ..... 63

4.5 የመምህራንን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ብቃት የሚወሰኑት ተላውጦዎች ..... 69

4.5.1 ግለሰባዊ ተላውጦዎች ..... 69

4.5.1.1 የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ ቅድመ የሥራ ላይ ሥልጠና ..... 69

4.5.1.2 ታላሚ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አጠቃቀም በተመለከተ የሥራ ላይ ሥልጠና ..... 71

4.5.1.3 የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለመጠቀም የቋንቋ መምህራኑ ፍላጎትና ተነሳሽነት ..... 72

4.5.2 ተቋማዊ ተላውጦዎች ..... 73

4.5.2.1 ቦታን በተመለከተ ..... 73

4.5.2.2 በጀትን በተመለከተ ..... 73

4.5.2.3 የተለያዩ የትምህርት ባለሙያዎች አመራር ..... 74

**ምዕራፍ አምስት**

**ማጠቃለያና እና አስተያየት ..... 76**

5.1 ማጠቃለያ ..... 76

5.2 አስተያየት ..... 78

ዋቢ ጽሑፎች ..... 80

አባሪዎች ..... 85

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተገለፀውና የፈረምኩት፣ ይህ ጥናት የራሴ ሥራ መሆኑን፣ በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ጽሁፎችና ምንጮች በሙሉ የጠቆምኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም አሰፋ ደሳለኝ ወርቁ

ፊርማ ___________________________

አድራሻ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል አዲስ አበባ

ቀን ___________________________

# አባሪዎች

# ምስጋና

በቅድሚያ እዚህ ያደረሰኝን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡ በመቀጠልም ከርዕስ መረጣ ጀምሮ የተለያዩ መጻሕፍትን በማዋስ ረቂቅ ፅሁፌን በማረምና አካሄዱን በማስተካከል አሁን ለደረሰበት ደረጃ ለአበቁልኝ አማካሪዬ ለዶክተር አረጋ ኃይለሚካኤል ጥልቅ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ለማማከር ብልሃታቸው የተለየ አክብሮትና  አድናቆት አለኝ፡፡

በመቀጠል ለዚህ ለአደረሱኝ ቤተሰቦቼ ለአባቴ ለአቶ ደሳለኝ ወርቁ እና ለእናቴ ለእማሆይ ተሰየሁ አለሙ ውለታቸውን በቃላት ለመግለፅ ያስቸግረኛል፡፡

ከመጀመሪያው ጀምሮ እንድማር ላነሳሳኝና ገና በልጅነቱ በሞት የተለየኝ ባለቤቴን የአባቱን ድርሻ በመወጣት ቤተሰብ የመምራት ኃላፊነት በመሸከም እኔ ያለሃሳብና ጭንቀት ትምህርቴን እንድከታተል ላበረታታኝ ልጄ ለሀብታሙ ጅብሪል የእናትነት ፍቅሬንና እንክብካቤዬን በትዕግስት በመጠበቅ ለታገሱ ልጆቼ ኤዶም ገነት ጅብሪል እና አፎሚያ ጅብሪል ከሁሉም በላይ በሆነ የእናትነት ፍቅሬ ከልብ አመሰግናችኋለሁ፡፡

ይህን መርሃ ግብር ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮ ወጪዬን በመሸፈን ለተባበረኝ የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ ለዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ወጭውን በመሸፈን ለተባበረኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ እንዲሁም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቋንቋን የማስተማር ስነ ዘዴ መምህራንን በሙሉ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ በተለይ ረዳት ፕሮፌሰር ጌታቸው እንዳላማውን እንደጓደኛ፣ እንደወንድም፣ እንደመምህር በመሆን ለክፍለ ትምህርቱ ተማሪዎች የሚያደርጉትን ትምህርታዊ ድጋፍ ከልብ እያመሰገንኩ ለአደረጉልኝ ቤተሰባዊና ትምህርታዊ እንክብካቤ እዚህ ደረጃ ለመድረሴ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለውና ከልቤ ማህደር ዘለዓለም ተጽፈው ይኖራሉ፡፡

ከመጀመሪያው ጀምሮ የትምህርት መሠረትን አስይዘው ዛሬም ድጋፋቸው ሳልተለየኝ የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ መምህር ለሆኑት ተባባሪ ፕሮፌሰር ማረው አለሙን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

በተጨማሪም ይህን መርሃ ግብር ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮ በየጊዜው በአካል እና በስልክ የሞራል፣ የገንዘብ እና የቁሳቁስ ድጋፋቸው ሳልተለየኝ እህቶቼ፣ ወንድሞቼ፣ ጓደኞቼ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

በመጨረሻም የጥናቱን ውጤት ቅርፅና ይዘቱን አምሮ በዚህ መልኩ እንዲወጣ ያደረገችልኝ የኮምፒውተር ባለሙያ ሰብለ ተሰማን ላማሰግናት እወዳለሁ፡፡

# አበርክቶ

መታሰቢያነቱ ገና ከመጀመሪያው ጀምሮ በአምሳላቸው ቀርፀው ማንነቴን እንዳውቅ ሳደረጉኝ እና ዛሬ ለደረስኩበት ደረጃ እንድደርስ አይዞሽ በርቺ በማለት የመማር እሩጫዬን አስጀምረውኝ ፍሬዬን ሳያዩ የልፋታቸውን መሰረት ዛሬ አንድ ብዬ ሻማውን ስለኩስ እንደትናንቱ አደራውን ልቀበል ተሞሽሬ ስወጣ በሞት ተለይተውኝ በመንፈስ እንጂ በአካል ከጎኔ ላጣኋቸው ለባለቤቴ ለጅብሪል ሰኢድ፣ ለእህቶቼ ለፍቅርተ ደሳለኝና ለአስናቀች ደሳለኝ ይሁንልኝ፡፡

# የሠንጠረዥ ማውጫ


| | | ገጽ |
|---|---|---|
| **ሠንጠረዥ አንድ፡-** | የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለመምረጥ የሚያገለግሉ መመዘኛዎችን በሚከተለው መንገድ ዘርዝሮ ማየት ይቻላል | 21 |
| **ሠንጠረዥ ሁለት፡-** | የክፍል ውስጥ ምልከታ ከተካሄደባቸው ሃያ አራት ክፍለጊዜያት መካከል መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የተጠቀሙባቸው ክፍለ ጊዜያት ብዛት፤ | 46 |
| **ሠንጠረዥ ሦስት፡-** | በምልከታ ወቅት አገልግሎት ላይ የዋሉት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ጥራት፣ | 47 |
| **ሠንጠረዥ አራት፡-** | በምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠን /ስፋትና ጥበት/ | 47 |
| **ሠንጠረዥ አምስት፡-** | የክፍል ምልከታ በተካሄደባቸው ጊዜያት መምህራን አገልግሎት ላይ በዋሏቸው የቋንቋ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የመጠቀም ብቃት | 48 |
| **ሠንጠረዥ ስድስት፡-** | መምህራን የተጠቀሙበት ቋንቋ የትምህርት መርጃ መሣርያ ለተማሪዎች የዕርስ በርስ መስተጋበርን የመፍጠር ሁኔታ፤ | 49 |
| **ሠንጠረዥ ሰባት፡-** | በቋንቋ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ ተማሪዎች ከተማሩ በኂላ መምህሩ ለሚጠይቃቸው ጥያቄ የሚሰጡት ምላሽ፣ | 50 |
| **ሠንጠረዥ ስምንት፡-** | የዕለቱን ቋንቋ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ማራኪነት በተመለከተ የተማሪዎችን ስሜት የሚዳስሰ፣ | 51 |
| **ሠንጠረዥ ዘጠኝ፡-** | በምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ በዋሉት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመቀጠም ተማሪዎች የሚያሳዩት የክፍል ውስጥ ተሳትፎ | 52 |
| **ሠንጠረዥ አስር፡-** | በምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተገቢነት፣ | 53 |

**ሠንጠረዥ አስራ አንድ፡-** በክፍል ምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ከዓይነት አንፃር ሲታዩ 54
**ሠንጠረዥ አስራ ሁለት፡-** ከታላሚ ትምህርት ቤቶች ለናሙና በአንዱ /በመሰረት ትምህርት/ ቤት የአማርኛ ቋንቋ የትምህርት እቅድ ውስጥ የተጠቆሙትን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት በዓይነት 55
**ሠንጠረዥ አስራ ሦስት፡-** በሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ውስጥ የተጠቁሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር /የሁለተኛው መንፈቀ ዓመት 65
**ሰንጠረዥ አስራ አራት፡-** በ2001 ዓ.ም. ለሁለተኛ መንፈቅ ዓመት ለሰባተኛ ክፍል በተዘጋጀው ዕቅድ ውስጥ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር /ከታላሚ ትምህርት ቤቶች መካከል የአንዱን በናሙናነት የተወሰደ፣ 66
**ሰንጠረዥ አስራ አምስት፡-** በስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ-ትምህርት ውስጥ የተጠቆሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር (የሁለተኛው መንፈቅ ዓመት) 67
**ሠንጠረዥ አስራ ስድስት፡-** በ2001 ዓ.ም. ለሁለተኛው መንፈቀ ዓመት ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጀው ዕቅድ ውስጥ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር/ ከታላሚ ትምህርት ቤቶች መካከል የአንዱ በናሙናነት የተወሰደ፤ 68
**ሰንጠረዥ አስራ ሰባት፡-** የታላሚ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያን በተመለከተ ቅድመ ሥራ ላይ ሥልጠና 70
**ሠንጠረዥ አስራ ስምንት፡-** የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምን በተመለከተ መምህራን ያገኙት የስራ ላይ ስልጠና 71

# የአባሪ ማውጫ


**ገጽ**

አባሪ "ሀ"፣ የክፍል ውስጥ ምልከታ መከታተያ ቅፅ

(Classroom Observation Checklist) ........ ***85***

አባሪ "ለ"፣ በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላ የፅሁፍ መጠይቅ ........ ***89***

አባሪ "ሐ"፣ ከአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር የተደረጉ የቃለ

መጠይቅ ጥያቄዎች ........ ***94***

አባሪ "መ"፣ ከካሴት ወደ ፅሁፍ የተመለሰ የመምህራን የቃለ

መጠይቅ ምላሽ ........ ***96***

# አጠቃሎ (Abstract)

በቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደት የትምህርት መርጃ መሣርያዎች አጠቃቀም ዓቢይ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን ተጠቅሞ በገላጭ ሥልት በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ዕርከን ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያዎች አጠቀቀም ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡ ይህንን ፍተሻ ለማካሄድ አጥኚዋ በጎንደር ከተማ አስተዳደር ሥር ከሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ዕርከን ትምህርት ቤቶች መካከል አራቱን በናሙናነት መርጣለች፡፡ የተተኳሪዎች አመራረጥም የምርምር ስልትን በተከተለ መልኩ በአመች፣ በነሲብ እና በግኝት ናሙና አመራረጥ ዘዴዎች ነው፡፡ አጥኚዋ ዋና ዓላማዋን ለመፈተሽ የሚያስችሉ የክፍል ውስጥ የምልከታ ቅፅ፣ የጽሑፍና የቃል መጠይቆችንም ተጠቅማለች፡፡ በስምንት ተተኳሪ የሰባተኛ እና የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ክፍል ውስጥ በመገኘት ለእያንዳንዱ መምህር የሦስት ሦስት ክፍለ ጊዜያት ምልከታ በማካሄድ፣ ለስምንቱም መምህራን የጽሑፍ መጠይቅ በማስሞላት እና የቃል መጠይቅ በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች አማካኝነት መረጃዎቹ ተሰብስበው ከተተነተኑ በኋላ ውጤቶቹ በአብዛኛዎቹ ክፍለ ጊዜያት የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም (58% እስከ 67%)፣ መምህራን ያለትምህርት መርጃ መሣሪያ በቃል ብቻ ትምህርቱን እንደሚያስተምሩ በተወሰኑት ክፍለ ጊዜያት (33% እስከ 42%) መምህራን በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እንደሚጠቀሙ መረዳት ተችሏል፡፡ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ ጥራትና መጠንም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎና መስተጋብር ግን በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በተጠቀሙባቸው ክፍለ ጊዜያት በጥሩ ደረጃ እንደሚገኝ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ ለሚደመጡ፣ ለሚደመጡና ለሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያነት የሚያገለግሉ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን በእርዳታ በበቂ ሁኔታ አግኝተዋል፤ ግን በክፍል ውስጥ ለሚካሄደው የቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደት አላዋሉትም፡፡ በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ለትምህርት መርጃ መሣሪያነት የሚያገለግሉ የተለያዩ ሰሌዳዎች፣ እንዲሁም ለትምህርት መርጃ መሣሪያ ፍንጭ ሰጪ የሚሆኑ መርሃ ትምህርት እና የመምህሩ መምሪያ የሉም፡፡ መምህራን የሚጠቀሙባቸው መርጃ መሣሪያዎች አንዴ ተጠቅማችሁ ወዲያውኑ ጣሉ የሚል የትምህርት ባለሙያዎች ጣልቃ ገብ አመራር እንዲሁም መምህራኑ በግል ጥረታቸው ለትምህርት መርጃ መሣሪያ መጠቀሚያ በእርዳታ የሚያገኙትን ባጀት የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ለሌላ አስተዳደራዊ አገልግሎት ማዋል በዋነኛነት የቀረቡ ድክመቶች ናቸው፡፡ በመጨረሻም በዚህ ጥናት ውስጥ የቀረቡትን ድክመቶች ለማቃለል የሚረዱ የመፍትሄ ሐሣቦች ተሰንዝረዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደት ጥበባዊና ሳይንሳዊ ነው፡፡ "ጥበባዊ ነው" ሲባል ዕውቀትን፣ አስተሳሰብን እና ክሂልን አይረሴ በሆነ ስልት ማስተላለፊያነቱን ሲያመለክት፣ በቋንቋ መምህሩ ግላዊ ችሎታ እና የማስተማር ብቃት የሚገለፅ ነው፡፡ "ሳይንሳዊ ነው" ሲባል ደግሞ በሳይንሳዊነቱ "የሚያድግ፣ የሚለወጥና የሚማሩት ነው" (Celce-Murcia 1991፡12)፡፡ መምህሩ ዕውቀትን በተጨባጭ ቅደም ተከተሉን ጠብቀው በሥርዓት በማቅረብ የተፈለገውን ዕውቀት፣ አስተሳሰብና ክሂል በማስጨበጥ ትምህርቱን በሳይንሳዊ የቋንቋ መርሖች እያስደገፈ ማቅረብን ያሳያል (Celce-Murcia 1991፣ Corder 1975)፡፡

በዚህ ረገድ መምህራን ዕውቀቸውን፣ ልምዳቸውንና የፈጠራ ችሎታቸውን በመጠቀም ለተማሪዎቻቸው ተገቢ የቋንቋ ዕውቀትና ክሂል ካስጨበጡ ፁሰበው የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ስኬታማ ይሆናል፡፡ በማንኛውም ቋንቋን የመማር-ማስተማር ሂደት ፁቀደውን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ተማሪዎች በእያንዳንዱ የቋንቋ ክሂል ብቃት አግኝተው ታላሚውን ቋንቋ ለማጎልበት ትምህርቱን ግልፅና ቀላል አድርጎ ለማቅረብ፣ ጉልበትና ጊዜን ቆጥቦ ለማስተማር የትምህርት መርጃ መሣሪያ መጠቀምን ይጠይቃል፡፡ McArthur (1989:78) ሐሳቡን በሚከተለው አኳኋን ይገልፁታል፤ በእውነቱ ኀበዝ መምህራን ለራሳቸው ሰብዕናና ለተማሪዎቻቸው ምኞትና ፍላጎት የታቀደውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ፣ የተነደፉትን ይዘቶች ለመተግበርና በተማሪውና በሚማረው ይዘት መካከል የሚኖረውን ግንኙነት ግልፅና ተጨባጭ፣ የትምህርት አሰጣጡንም ሣቢና ማራኪ ለማድረግና ጊዜና ጉልፁቸውን በአግባቡ ለመገልገል ተገቢ የሆኑ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ይጠቀማሉ፡፡

በተለይ በአሁኑ ጊዜ ይበልጥ ተፈላጊና ውጤታማ በሆነው ተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብና ዘዴ መሠረት ለቋንቋ ተማሪዎች ተገቢነትና ተዛማጅነት ባላቸው የተለያዩ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ የመማር-ማስተማር ሂደቱን ማፋጠን ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው (Harmer 2001:12፣ Aggarwal 1996:253)፡፡ ምክንያቱም ቋንቋ ረቂቅና ውስብስብ የመግባቢያ መሣሪያ ነውና፡፡ በመሆኑም በመማር-ማስተማር ሂደት በዚህ ረቂቅና ውስብስብ መሣሪያ በአግባቡ መግባባትና መረዳዳትን ዲቻል በቋንቋ ትምህርት መርጃ

መሣሪያዎች በሙታገዝ በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት ከረቂቅነትና ውስብስብነት ወደ ተጨባጭነትና ግልፅነት አቅልሎ ማቅረብ ነው፡፡

ይሁን እን ጂ በአገራችን ነባራዊ ሁኔታ የሚታየው ደግሞ በየጊዜው፣ በየደረጃውና በየቦታው በሚደረጉ መደበኛም ሆነ ኢመደበኛ ትምህርታዊ ሥብሰባዎች የኢትዮጵያ ትምህርት ጥራት ወድቋል፤ የትምህርት ትክክለኛነት፣ አግባብነትና ችግር ፈችነት አጠያያቂ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ለዚህም ምስክሮቹ በየጊዜው የሚታዩት ተማሪዎች ናቸው ሲባል ይደመጣል፡፡ ይህንን ሐሳብ በማጠናከር ባየ (2000፣xxi) የዘመኑን ተማሪ በቋንቋው የመጠቀም ችግርን በተመለከተ [በታላላቆቹ የትምህርት ተቋማት ሳይቀር፤ ዛሬ ባለቤትና አንቀፅን የሚለይ ተማሪ ለማግኘት እያስቸገረ ነው፡፡ . . . ሁለተኛ ደረጃን የጨረሰ ተማሪ ዛሬ ጥሩ የሥራ ማመልከቻ ቀርቶ፤ ተራ ደብዳቤ እንኳን በወጉ ለመፃፍ እየተሳነው መጥቷል፡፡ ] ይህንን ሃቅ የትምህርት ሚኒስቴር (1994፣2-3) የኢትዮጵያ ትምህርት የተገቢነት፣ የጥራት፣ የተቀባይነትና የዋጋማጣት ውስብስብ ችግሮች ውስጥ እንዳለ ይገልፃል፡፡ ለትምህርት ጥራት መውደቅ በርካታ መገለጫዎች ቢኖሩትም ከነዚህ መካከል ቶሎ የሚከሰቱት የተማሪው የፈተና ውጤት ዝቅተኛ መሆን፣ የደጋሚዎች ቁጥር መጨመር፣ የሚያቋርጡ ተማሪዎች ቁጥር መብዛት ናቸው፡፡ የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት መጨረሻው በህብረተሰቡ ዘንድ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት መሸከም የማይ ችል ዜጋ ማፍራት ይሆናል፡፡ ስለዚህ መፍትሄ ከሚሆኑት አንዱ ይሉናል (Amare 1998:292) የትምህርት መርጃ መሣሪያን በመጠቀም ማስተማር ነው፡፡ መምህሩ ከተማሪዎች መካከል ቁሞ በገለፃ ብቻ ከማስተማርና በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጽፎ ተማሪዎች እንዲገለብጡ ከማድረግ በተጨባጭና ከአ ካባቢ በሚገኙ መርጃ መሣሪያዎች አስደግፎ ማስተማር ችግሩን ያቃልላል፡፡ በመርጃ መሣሪያ አስደግፎ የሚያስተምረውን መምህር ማበረታታት፣ መርጃ መሣ ሪያ የማይጠቀመውን መቆጣጠርና እንዲጠቀም ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመው ስለ ትምህርት መርጃ መሣሪያ አስፈላጊነት በአፅንኦት ሲገልፁ “ያለትምህርት መርጃ መሣሪያ ማስተማር በጣት ጥፍርእረስ እንደማለት ነው” (Amare 1998:292)፡፡

ከዚህ ላይ ስለትምህርት መርጃ መሣሪያ ሲነሣ መምህራን ስለትምህርት መርጃ መሣሪያ ያላቸው ዕወቀትና አመለካከት ከግምት ውስጥ መግባት ያለበት ጉዳይእንደሆነ Bestat (2000) ይገልፃሉ፡፡ ከፍ ሲል ከተገለፁት ነጥቦች በመነሳት በቋንቋ ትምህርት የትምህርት መርጃ መሣሪያን መጠቀም

አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን ነዘባለን፡፡ ይሁን እንጂ ከላይ ከተነሱት ነጥቦችእንደምንረዳው የትምህርት መርጃ መሣ ሪያዎችን ለመጠቀም የአጠቃቀም ግንዛቤ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ የተነሳ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን ምን እንደሚመስል የአጠቃቀማቸውን ሁኔታ መመርመር የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት ነው፡፡ አጥኝዋም በማስተማር ሥራ ላይእያለች በመምህራን የመገምገሚያ መስፈርት ላይ "የትምህርት መርጃ መሣሪያ ይጠቀማሉን?" የሚል ዝርዝር ይዘት በመመልከቷ ይህ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ሁኔታ ከሌሎች ጉዳዮች በተለይ ትልቅ ትኩረት የተሰጠበት ምክንያት ምን ይሆን የመምህራንስ አጠቃቀም? የሚሉ ጥያቄዎች በአዕምሮዋ ይመላለሱባት ነበር፡፡ ለድኅረ ምረቃ ትምህርት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከገባችበት ጊዜ ጀምሮ ደግሞ በተለያየ ጊዜ ያቀረበቻቸው የኮርስ ማሟያ ፅሑፎችም ጉዳዩን በጥልቀት ትመለከት ዘንድ ይበልጥ ገፋፍቷታል፡፡ አጥኝዋ ይህን ጥናት ለማጥናት ያነሳሳት ዋና ጉዳይም ይኸው ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ ዓላማ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በጎንደር ከተማ አስተዳደር አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡ ይህ ዓቢይ ዓላማ የሚያካትታቸው ዝርዝር ዓላማዎችም፡-

- በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም ተገቢ ሥልጠና ያገኙ መሆኑን መፈተሽ፣
- በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ያሉት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አጠቃቀም በተመለከተ ያላቸውን ግንዛቤና ዕውቀት ለመዳሰስ፣
- በተመረጡት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም ዙሪያ የሚያጋጥሟቸው ችግሮች ካሉ ለመለየት፣
- የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መሣሪያዎች (መርሐ ትምህርቱ፣ የመምህሩ መምርያና የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ) ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ያላቸውን አስተዋጽኦ ለመዳሰስ፣ እና

- መምህራን የሚጠቀሙባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን እገዛ ለመመርመር፣

የሚሉት ናቸው::

## 1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት የሚከተሉት ፋይዳዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፤

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምንእንዲረዱ የሚያመላክት መረጃ ይሰጣል::
2. ከጥናቱ ውጤት፣ ከሚሰጡት አስተያየቶችና የመፍትሔ ሐሳቦች በመነሳት የትምህርት ጥራትን ለመጠበቅ ተግባራዊ በሚደረገው ጥረት የቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም ምን መሆንእንዳለበት፣ የመማር -ማስተማር ክንውን የሚመለከታቸው ሌሎች አካላት (የትምህርት ባለሙያዎች) የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አጠቃቀም እንዲገነዘቡና ትኩረት እንዲሰጡ ያደርጋል::
3. ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተመሳሳይነትና ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ወደፊት ጥናት ለሚያካሂዱ ተመራማሪዎች እንደመነሻና ማጣቀሻ ሆኖ ያገለግላል::

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው በጎንደር ከተማ አስተዳደር ውስጥ ካሉት አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች ውስጥ በተመረጡት አራት አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች ብቻ ነው:: ትምህርት ቤቶቹ ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎችን ቢያስተምሩም ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በሰባተኛና በስምንተኛ ክፍል ላይ ብቻ ነው:: ለዚህ ምክንያቱ አጥኝዋ ለጥናቱ ሰፊ ጊዜ እንዲኖራትና ካለው የጊዜና የገንዘብ ውስንነት አንፃር ነው:: ከዚህ ሌላ ጥናቱ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ላይ ብቻ ያተኮረ ነው:: የሌሎችን የትምህርት ዓይነቶች መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም አይመለከትም፤ የሌሎችንም ሆነ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትም አይመለከትም::

## 1.5 የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ፍቺ

Audiovisual Aids = የሚደመጡና የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያ

Authentic = ኑባራዊ

Drawing Sound distribution system sets = ንድፎች

Flipcharts = የድምፅ ማስራጫ ዘዴዎች

Interaction = መስተጋብር

Magnetic Boards = መግነጢሳዊ ሰሌዳ

Motivation = ተነሳሶት (ንሺ)

Natural integration = ተፈጥሮአዊ ቅንጅት

Overhead Projector = ከአናት በላይ ፕሮጀክተር

Participation = ተሳትፎ

Target = ታላሚ/ተተኳሪ

Visuals = የማታይ

Learning resource = የመማሪያ ምንጮች

Educational psychology = ሥነትምህርታዊ ሥነልቡና

Relevance = ጠቃሚነት

Appropriateness = ተስማሚነት

Accuracy = ትክክለኛነት

Clarity = ግልፅነት

Focus of attention = ትኩረት

Simplicity = ቀላልነት

Principles of selection = የአመራረጥ መርሖዎች

Specific educational values = የተለዩ ትምህርታዊ እሴቶች

Real = እውነተኛ

Variables = ተላውጦዎች

Audio = የሚደመጥ

Classification = ክፍፍል

Simulation = ማነቃቂያ

Demonstration = ለዕይታ የቀረቡ መረጃዎች

Study trip = ጥናታዊ ጉዞ

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳን

## 2.1 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ምንነት

የተለያዩ ምሁራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በተለያየ ስያሜ ይጠሯቸዋል:: የማስተማሪያ ሚዲያዎች፣ የሚደመጡና የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፣ መርጃ መሣሪያዎች፣ የመማሪያ ምንጮች (learning resources) የሚሉት ምሁራን ለትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ከሰጧቸው ስያሜዎች ጥቂቶቹ ናቸው (Nkuuhe 2000:224፣ Quist 2000:27፣ Aggarwal 1995:157፣ Romiszowski 1988:7 እና Harrison and Gowin 1995:28)::

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚለው ፅንሰ ሐሳብ በተለያዩ ምክንያቶች የተነሣ በተለያየ መንገድ ሊተረጎም ይችላል:: በየትኛውም ደረጃ፣ በሁሉም የትምህርት ዓይነትና የትምህርት መስኮች፣ በመምህራንና በተማሪዎች ዘንድ ለመማር-ማስተማር ሂደት የሚውሉትን ፅንሰ ሐሳቦች ሁሉ ያጠቃልላል (Nkuuhe 2000:224):: (Nkuuhe 2000) አያይዘው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሲባል የህትመት ውጤቶችን፣ ምስሎችን፣ ሞዴሎችን፣ ዕውነተኛ ነገሮችን (real objects)፣ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎችና የተለያዩ ሰሌዳዎችን በአጠቃላይም ለመማር-ማስተማር ሂደት አጠቃላይና ዝርዝር የትምህርት ዓላማዎች ከግብ ለማድረስና የትምህርት ይዘቶችን በተጨባጭ ለማብራራት አገልግሎት የሚውሉ የትምህርት አጋዥ መሣሪያዎች (devices) መሆናቸውን ያስረዳሉ::

Heinich et al. (1996:8) በበኩላቸው "ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተማሪዎች ትምህርታዊ ይዘቶችን /ዕውቀት፣ ክህሎትንና አመለካከት/ ከተለያዩ ምንጮችየሚገ ኙ የሚያግዙና ትምህርታዊ ዓላማዎችን ስኬታማ የሚያደርጉ መሣሪያዎች ወይም ቁሳዊ አካሎች ናቸው::" ይላሉ:: Harrison and Gowin (1995:28) ደግሞ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በትምህርት አቀባበል ላይ ፍርሃትን፣ ጭንቀትን ወይም መረበሽን የሚያስወግዱ፣ የንባብና ሌሎች ክሂሎችን ተማሪዎች እንዲያሻሽሉ የሚያግዙና አንድን ክሂል ፣ ዕውነታ ወይም ሐሳብ የሚያጎሉና የሚያዳብሩ ናቸው:: በማለት ይገልጿቸዋል::

ከላይ ከቀረበው የምሁራን ሀሳብ እንደምንገነዘበው የትምህ ርት መርጃ መሣሪያዎች አንድን የትምህርት ይዘት ተጨባጭ በሆነ መልኩ በማቅረብ የታቀደውን ዓላማ በተገቢ መንገድ

ለማስፈፀም የሚያስችሉ የተለያዩ አጋዥ ነገሮች (የ**ሚ**፣ የሚደመጡ፣ የሚዳሰሱ) ናቸው ማለት እንችላለን::

## 2.2 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መምህራን ለምን ይጠቀማሉ?

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አገልግሎት በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን የተለያየ አስተያየት ሰጥተዋል:: (Harmer 2001:134) እንደሚሉት፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለተግባራዊ ልምምድ ብሎም የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማነሣሣት ያገለግላሉ:: እንደ Quist (2000:104) አገላለፅ፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የጽንሰ ሐሳቦችን ምንነት በቃል ብቻ ከማብራራት ፅንሰ ሐሳቦችን ግልፅ ለማድረግ የሚያስችሉ ተገቢነት ያላቸው ውክልናዎች በማቅረብ ረገድ ለተማሪዎችም ሆነ ለመምህሩ የላቀ ዕገዛ አላቸው:: ለተማሪው በቀላሉ የመማር ልምድ እንዲያካብት ያስችሉታል፤ ለመምህሩም ረቂቅ የሆኑ የትምህርት ይዘቶችን ተጨባጭና ዕውናዊ በሆነ መልኩ ግልፅና ቀላል አድርጎ ለማቅረብ ይረዱ ከዚህ ጋር በተያያዘ Nkuuhe (2000:226) የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የጎላ ጠቀሜታ ሲገልፁ ፣ ከሥነ ትምህርታዊ ሥነ ልቦና (Educational psychology) ጋር ያያዙታል:: ይኸውም እያንዳንዱ ሰው የሚማረው በስሜት ሕዋሳቱ (በአፍንጫው በማሽተት፣ በዓይኑ በመመልከት፣ በምላሱ በመቅመስ፣ በአንደበቱ በመናገር፣ በጆሮዎቹ በማዳመጥና ሔጆቹ በመዳሰስ) የተለያዩ መረጃዎችን በመሰብሰብ እንደሆነ ያብራራሉ::

በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለምን መጠቀም እንደሚያስፈልግ Nkuuhe (2000:226) ሲያብራሩ፣ አንድ ሂደት ወይም ቴክኒክ በተጨባጭእንዲታ ይ ያደርጋሉ:: የቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደት የተሳካ እንዲሆን ያግዛሉ:: በዚህም የተማሪዎችን ትኩረት በመሳብ የመማር ፍላጎት ያነሳሳሉ፣ የጽንሰ ሐሳቦችን ዕውነታ እንዲረዱ ያደርጋሉ፣ የተማሪዎችንም ሆነ የመምህራንን የፈጠራ ችሎታ ያሳድጋሉ፣ ቡድናዊም ሆነ ግላዊ የመማር ልምድን ያጎለብታሉ:: ተማሪዎች በዋና ዋና የትምህርት ይዘቶች ወይም ቁልፍ ሐሳቦች ላይ ትኩረትእንዲያደርጉ ያስችላሉ:: የአ ዳዲስ ቃላትን ትርጉም ለመረዳት ስለሚያስችሉ ለትርጉም ፍለጋ የሚባክነውን ጊዜ ይቆጥባሉ:: በአጠቃላይ የአንድን ድርጊት ወይም የአንድን ነገር ቅደም ተከተላዊ ሂደት በተማሪዎች አዕምሮ ምናባዊ ምስል በመፍጠር ሐሳቡ በአዕምሯቸው እየተደጋገመ እንዲመጣ ያደርጋሉ::

በተጨማሪም የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የመጠቀም ምክንያትን ሲገልፁ፣ ረቂቅ የሆኑ የትምህርት ሐሳቦችን ተጨባጭ አድርጎ በማቅረብ፣ ተማሪዎች ያለምንም ችግር የትምህርት ይዘቶችን እንዲረዱና የተማሪዎችን የማስታወስ ችሎታ በማፋጠን ፣ ተማሪዎች ከአካባቢያቸው ጋር መስተጋብራዊ ግንኙነት እንዲያደርጉና አካባቢያቸውን እንዲወዱ እንዲሁም እንዲያደንቁ በማገዝ፣ ተማሪዎች የተለያዩ ክሂሎችን ለምሳሌ:- የማዳመጥ፣ የምልክት ወይም እጅ የመጠቀም፣ የመገጣጠም፣ ችግር የመፍታት፣ አብሮ የመ ሥራት ልምዶችን እንዲያ ዳብሩና የመማር ጉጉት በመቀስቀስ ለመማር የሚኖራቸውን መነሳሳት በመጨመር፣ በተማሪዎችና በመምህራን ዘንድ ፈጠራን ለመቀስቀስና መምህራን የሚያቀርቧቸው የትምህርት ይዘቶች ለተማሪዎች ተአማኒ (እውነተኛ)፣ ተገቢና ትርጉም ያላቸው እንዲሆኑ ያስችላሉ (Malawi Institute of Education 2003)::

ከላይ ከቀረበው ገለፃ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ መገልገል እጅግ ጠቃሚ እንደሆነ እንገነዘባለን:: በመሆኑም የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መምህሩ ትምህርትን ለተማሪዎች ቀላልና ግልፅ በሆነ መንገድ ለማቅረብ፣ የመምህሩንም ሆነ የተማሪዎችን የፈጠራ ችሎታ በማጎልበት ፣ በመምህሩና በተማሪዎቹ ወይም ተማሪዎች እርስ በርሳቸው ጥሩ መስተጋብር እንዲኖራቸው እገዛ በማድረግ ጉልበትንና ጊዜን ከመቆጠብ አንፃር የጎላ ድርሻ አላቸው:: ትምህርቱን ለተማሪዎች ስሜት በሚያመች መንገድ ለማቅረብና ለተማሪዎቹም ትምህርቱን ከስሜታቸው ጋር ተጨባጭ በሆኑ መልኩ አቅልሎ ለማቅረብ ያስችላሉ:: በአጠቃላይ በየትኛውም ደረጃ ለሚቀርብ ትምህርት፣ በየትኛውም የዕድሜ ክልል ላለ ተማሪና በማንኛውም የትምህርት መስክ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መገልገል የላቀ ጠቀሜታ እንዳለው መረዳት ይቻላል::

Grant (1987:18) ተማሪዎች በተለያዩ ተግባራት ከተሳተፉ ተግባቦትን በተገቢው ሁኔታ ያቀላጥፋሉ ይላሉ:: ከዚህ ጋር በተያያዘ Wong and Wong (1998:168) በቋንቋ የመማር-ማስተማር ሂደት ተማሪዎች ተምረዋል የሚባለው በተለያዩ ተግባራዊ ክንውን የተሳተፉ እንደሆነ ነው:: ጥ ሩ የቋንቋ መምህርም ተማሪዎቹ በተሳትፎ የበለጠ የሚማሩበትን መንገድ በመለየት አብዛኛውን ጊዜ በተግባር ክንውኖች በማሳተፍ ተግባቦታዊ በ ሆነ ዘዴ ተፈጥሯዊ ወደ ሆነው የቋንቋ አጠቃቀም እንዲያዘነብሉና እንዲሳተፉ የሚያግዝ ሲሆን ነው፤ በተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመገልገል የተማሪዎቹን ትኩረት በመሳብ የተለያዩ የቋንቋ ክሂሎችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ

ሲያግዛቸው ነው ይላሉ:: ከእነዚህ ምሁራን ሐሳብ የምንገነዘበው በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አማካይነት መምህሩ ሲያስተምርና ተማሪዎች ሲማሩ ተግባራዊ ክንውን መኖሩን ነው:: ይህም ተማሪዎች በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሲጠቀሙ በመመልከት፣ የተመለከቱትን በማድረግ፣ በመነካካት እና በተለያዩ ተግባራዊ ክንውኖችእየተሳተፉ በክፍል ውስጥም የተማ ሩት ከክፍል ውጭ ካለው ሕይወት ጋር በማገናኘት እውነዊው ሕይወት እንዲገለገሉበት በር ስለሚከፍትላቸው የመማር ሂደቱ እንዲፋጠን ያደርጋሉ::

የመማር-ማስተማር ሂደት ውጤታማ እንዲሆን ገሺ (motivation) ከፍተኛ ሚና እንዳለው Stern (1991) ይገልፃሉ:: የተማሪውን ፍላጎት ያላገናዘበ ትምህርት ቃቀደውን ዓላማ ከግብ ሊያደርስ አይችልም:: Cook (1996:75) “ገሺ መማርን ስኬታማ እንዲሆን ያደርጋል” በማለት ሐሳቡን ያጠናክሩታል:: የማስተማር ሥነዘዴ የሚደግፈው ተማሪዎች በመጀመሪያ ለመማር መነሣሣት እንዳለባቸው ነው:: “ከክፍል ውስጥም በመማር-ማስተማር ሂደት ተማሪዎች በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሲማሩ በእጅጉ እንደሚነሣሡ” McDonough and Shaw (1993:214) ይገልፃሉ:: በአጠቃላይ ተማሪዎችን በማነሣሣት ጥሩ የቋንቋ ችሎታ እንዲኖራቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ጉልህ ድርሻ ስላላቸው የተማሪዎችን ፍላጎት አነሳስቶ ትምህርቱ ቋሚ እንዲሆን ያግዛሉ::

በተመሳሳይ ሁኔታም Bowen (1982:1) የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በተመለከተ የቋንቋውን ትምህርት ስፋትና ጥልቀት እንዲኖረው ያደርጉታል:: ተማሪዎች ከመማሪያ መጽሐፍ ወጥተው ተፈጥሯዊ ወደሆነው ቀላል ነገር እንዲያተኩሩ ያስችላቸዋል:: ይህም ሂደት የቋንቋውን ትምህርት ከተጨባጩ ዓለም ጋር ያገናኛል:: በመሆኑም በክፍል ውስጥ የሚማሩትን ትምህርት ከክፍል ውጭ ካለው ቀሪ ሕይወታቸው በቋንቋው እንዲጠቀሙበት የማድረግ አቅም አላቸው:: በቀላሉ ሊረሱ የሚችሉትን ረቂቅ የሆኑ አስተሳሰቦችን፣ የነገሮችን ስፋት፣ ክብደት፣ ጥልቀት፣ ጣዕም፣ ጠረን ስሜት፣ ቀለም፣ ጊዜና ርዝመት፣ ወዘተ. የመሳሰሉትንና የነገሮችን እንቅስቃሴ ለግንዛቤ አስቸጋሪ የሚሆኑትን ቀለል ባለ ዘዴ፣ ግልጽና ተጨባጭ በሆነ መንገድ ለማስረዳት ያስችላሉ:: ከዚህም ሌላ በመምህሩና በተማሪዎች መካከል የሚካሄዱትን ምልልሶች፣ ክርክሮች፣ ውይይቶች፣ ገለፃዎች፣ ጥያቄና መልሶች፣ አስተያየቶች፣ ግምታዊ ሐሳቦች፣ ወዘተ. ከምናባዊነት ይልቅ ተጨባጭነትእንዲኖራቸው በማድረግ ክንውኖቹ በተጨባጭ ዕውነታዎች ወይም በተፈጥሯዊ የተግባቦት ዐውድ የቀረቡት መረጃዎች ሐሳቡን እንዲያጠናክሩ ያደርጋሉ:: በሁሉም

የትምህርት ዕርከኖች የቋንቋ ብቃትን ያጎናፅፋሉ፣ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለየትኛውም የትምህርት ደረጃ፣ በየትኛውም የዕድሜ ክልል ላሉትእንደደረጃቸው በመጠቀም ከተማሪዎች የሚጠበቀወን የባሕሪ ለውጥ በቀላሉ ለማግኘት ያስችላሉ:: ለምሳሌ አንድ ተማሪ አንድን አዲስ ቃል ከመማሪያ መጽሐፍ ወይም ከመዝገበ ቃላት ለመረዳት ይከብደው የነበረውን በተለያዩ ሥዕሎች፣ ፖስተሮች፣ ወዘተ በመታገዝ ምናባዊ ምሥል በመፍጠር በቀላሉና በሚያስደስት፣ ሊረሱ በማይችሉ አኳኋን ለመገንዘብ ያስችለዋል:: በተጨማሪም ተግባፁዊ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብን ቀላልና ተፈጥሯዊ የማድረግ ፋይዳ አላቸው:: በመሆኑም መምህሩ ለተማሪዎቹ በመማር-ማስተማር ሂደት አራቱን የቋንቋ ክሂሎች (ማዳመጥን፣ መናገርን፣ ማንበብና መፃፍን) በተናጠልና በቅንጅት ለማስተማር ያግዙ ፤ የንዑሳን ክሂል ዘርፎች (ቃላትንና የሰዋስውን ክፍሎች) ለማስተማር የጎላ ጠቀሜታ አላቸው::

## 2.3 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዓይነትና አከፋፈላቸው

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በተናጠል ሲታዩ ቁጥራቸው ብዙ ነው:: በመስኩ ጥናት ያደረጉ ምሁራን እነዚህን በርካታ ቁጥር ያላቸውን የትምህርት መርጃ መሣ ሪያዎች እንደየተቀራራቢነታቸውና እንደአገልግሎታቸው በማቧደን በተወሰኑ ምድቦች ይመድቧቸዋል:: በዚህ መንገድ ሁለት ዓይነት አከፋፈሎች አሉ:: የመጀመሪያው የAggarwal (1996:161) አከፋፈል ሲሆን የሚደመጥ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች (Audio material)፣ የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች (Visual materials) እና የሚደመጡና የሚታዩ (Audio visual materials) በማለት በሦስት ዋና ዋና ምድቦች ይመድቧቸዋል:: የAggarwal (1996) አከፋፈል በሦስቱ ዋና ዋና ምድቦች ሥር ድምፃቸው በጆሮ ብቻ የሚደመጡትን ለብቻ በመለየት የሚደመጡ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፣ በዓይን ብቻ የሚታዩትን በመለየት የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፣ እና ድምፃቸው በጆሮ እየተሰማ በ ዓይን የሚታዩትን የሚደመጡና የሚታዩ በማለት መድበዋቸዋል:: በሥራቸውም እ ንደየመሣሪያዎቹ ሁኔታ በእነዚህ ምድቦች ሥር ተዘርዝረዋል::

Nkuuhe (2000:225) የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአምስት ይከፍሏቸዋልእነሱም የሕትመት ውጤቶች፣ የዕይታ፣ የኤሌክትሮኒክስ፣ የሚደመጡና የሚታዩ እና የማይንቀሳቀሱ

ናቸው:: የAggarwal (1996)ን እና የNkuuhe (2000)ን አከፋፈል፣ አንዱ በሌላው የሚካተቱ ናቸው:: በመሆኑም በNkuuhe (2000) ላይ ፁተሙ፣ የሚታዩና የማይንቀሳቀሱ በማለት የሚጠሩዋቸው Aggarwal የሚታዩ በሚሉት ውስጥ የሚመደቡ ናቸው:: "የሚደመጡና የሚታዩ" የሚለውም አከፋፈል የሚደመጡና የሚታዩ ከሚለው ጋር በአቻነት የሚቆም ነው:: በመጨረሻም "ኤሌክትሮኒክስ" የሚለውም የሚደመጡ በሚለው ውስጥ የሚካተት ነው:: በመሆኑም ከዚህ አሳማኝ ሁኔ በመነ ሣት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አከፋፈል በAggarwal (1996) መሠረት በሦስት (የሚደመጡ፣ የሚታዩ የሚደመጡና የሚታዩ በማለት መመደብ) ይቻላል:: ስለዚህ ቀጥለን እያንዳንዱን በአጭር በአጭሩ ለማብራራት ይሞከራል::

### 2.3.1 የሚደመጡ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

Aggarwal (1996:161) ባቀረቡት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሥር የተካተቱት መልዕክታቸውን በማዳመጥ የስሜት ሕዋስ ብቻ መቀበል የሚቻልባቸውን የሚደመጡ የመማር-ማስተማር ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ይይዛል:: በውስጡም ሬዲዮ ቴፕ፣ የሙዚቃ መሣሪያዎች፣ የቋንቋ ቤተሙከራ፣ ድምፅ ማጉያዎች፣ ቴፕና ዲስክ መቅጃዎች፣ ወዘተ. ያካትታሉ:: በመሆኑም የቋንቋ ትምህርት አቀራረብን ተከትሎ በተገቢው መንገድ መከወን ተገቢ ይሆናል:: ስለዚህ የሚደመጡ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በመጠቀም ተማሪዎች ተግባቦታዊ በሆነ ተግባር ላይ እየተሳተፉ ቋንቋን ለመማር የሚያስችላቸው ዓውድ ይፈጥራሉ:: ይህን አስመልክተው Nunan (1988፡38) የሚደመጠው ነገር እንደመ ሠረታዊ ዓውድ ራሱን ችሎ የሚቆምና መረዳትን፣ አፍልቆትን፣ አዙሮ ማሰብን፣ ወዘተ. እንደሚያካትት ገልፀው በተለየ ተግባሩ ሲደመጥ ለቋንቋው ፍች ትኩረት ስለሚሰጥ ኑባሪያዊነት ያለው የቋንቋ ትምህርት መስተጋብር ለመፍጠር እንደሚያስችል ያስረዳሉ::

ከዚህ አንፃር የሚደመጡ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አራቱን የቋንቋ ክሂሎች በተለይም የማዳመጥና የመናገርን ክሂሎች ቃሉብ ተማሪዎች ቋንቋውን ሲማ ሩ ሐሳብ የማመንጨትን፣ የማገናዘብን፣ መልዕክቱን በትክክል መረዳትእንዲችሉ በትክክል የተቀረፁትን ንግግሮች በማዳመጥና ለአዳመጡት ምላሽ በመስጠት ሐሳባቸውን በሚገባ መግለፅእንዲችሉ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ:: በሀገራችን ኤሌክትሪክ ባልደረሰባቸው የገጠር ትምህርት ቤቶች በፀሐይ ብርሃን እየተጓዙ ለገጠሩ ተማሪ የማዳመጥና የመናገርን ክሂሎች በማዳበር

በኩል ሬዲዮና ቴፕሪኮርደር ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረጉ እንዳሉ ይታወቃል (ጌታቸው 1992፣17)::

እንደ Atkins et al. (1996:227-228) አገላለፅ፣ ተማሪዎች አንድን ነገር አዳምጠው እንዲይዙ ወይም አጭር ጽሑፍ እንዲጽፉ ቢደረጉ ወይም ያዳመጡትን እንዲወያዩበት ቢሆን ክህሎትን በቅንጅት ማስተማር እንደሚቻል ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ አባባል የምንገነዘበው በቴፕሪኮርደር ወይም በሬዲዮ የሚደመጥ መልዕክት አራቱን የቋንቋ ክሂሎች አቀናጅቶ ለማስተማርም እጅግ ጠቃሚ መሆኑን ነው፡፡

በመሆኑም አማርኛ ቋንቋ በአጠቃላይ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ መምህሩም ሆነ ተማሪዎች በተግባቦታዊ የንግግር ልውውጥ ሂደት ላይ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣ የዓረፍተ ነገር አገባብና የሐሳብ አገላለፅን በአግባቡ በድምፃዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ የመማር-ማስተማር ሂደቱን ማጎልበት ይችላሉ፡፡ McDonough and Shaw (1993:214) ሁሉም ተማሪዎች በቡድን የሚያዳምጡት ነገር በተግባር ከተረጎሙት የዓይን አፋርነትንና የቅልጥፍናን ችግር ማስወገድ እንደሚቻል ያስገነዝባሉ፡፡

ከላይ ከቀረበው የምሁራን ሐሳብ የሚደመጡ ነገሮች ለምሳሌ በቴፕና በሬዲዮ የቀረቡ መልዕክቶች ላይ የመሣሪያዎቹ መኖር ፍላጎትን በመቀስቀስ ተማሪዎችን ተሳታፊ ከማድረጉ ባሻገር ምላሽ እንዲሰጡ እንደሚጠየቁ ስለሚያውቁ በንቃት እንዲከታተሉት በማድረግ ረገድ የጎላ አስተዋፅኦ እንዳላቸው እንረዳለን፡፡

### 2.3.2 የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

Aggarwal (1996፡157)፣ Wright (1989፡4)፣ Bowen (1982፡6) እንደሚገልፁት፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የቋንቋ ትምህርትን በማገዝ ረገድ ቀዳሚውን ሥፍራ ይይዛሉ፡፡ Aggarwal (1996:157) ዋቢ አድርገው እንደጠቀሱት የሰብዓዊ መብት ተሟጋችና ፀሐፊ Desiderious Erasmus (1466-1536) በዘመኑ የነበረውን ቃላዊና በሽምደዳ ላይ ያተኮረ የትምህርት አሰጣጥን በመቃወም ሕፃናት በሥዕሎችና በሌሎች የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ መማር እንዳለባቸው በይፋ ማወጁ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የጎላ ድርሻ ያሳያል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እኒህ ምሁር በጥናታቸው የሚታዩ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ፋይዳ

በቀዳሚነት John Amos Comenius (1592-1670) የተባሉ ምሁር ("Sensulium pictus") በእንግሊዝኛው "The world sense objects" በመባል የሚታወቀው 150 ሥዕሎችን ያካተተ የመማሪያ መጽሐፍ እንዳዘጋጁና ሥዕሎችም በዕለት ተዕለት የሕይወት እንቅስቃሴ ላይ ያተኮረ እንደነበር፣ ይህ የመጀመሪያው በሥዕል የተደገፈ የሕፃናት መማሪያ መፅሐፍ ተደርጎ ሊቆጠር እንደሚችልና መጽሐፉም በመላው ዓለም በሚገኙ የትምህርት ማዕከሎች ሰፊ ስርጭት አግኝቶ አገልግሎት እንደሰጠ አክለው ይገልፃሉ፡፡ ሥዕላዊ መግለጫዎች በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪውን ስሜትና ፍላጎት ከመቀስቀስ ባሻገር ቋንቋውን የመድበለ ቃላት ዕውቀቱ ከማጎልበትና በቃላትና በሐረጋት ዓረፍተ ነገሮችን ከመመሥረት አንፃር ጥሩ ልምምድ ለማድረግ እንደሚያስችሉት Nunan (1991:136) የሥዕላዊ መጽሐፎችን ፋይዳ በሚገልፁበት አባባል ሐሳቡን አጠናክረውታል፡፡

እንደ Wright (1989:136) ገለጻ፣ ሥዕሎች የተማሪዎችን የማዳመጥና የማንበብ ክሂሎች ለማዳበር ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በተለይ ይህን በተመለከተ ሁለት ምክንያቶች አሉ፡፡ በመጀመሪያ ከቃላት የሚወጡት ትርጉሞች በሥዕሎች ውስጥ በሚገኙበት ዓውዳዊ አገባብ ላይ ይወሰናሉ፤ ወይም ሥዕሎች የተለያዩ አውዶችን በመፍጠር በክፍል ውስጥ ለማስተማር ላቅ ያለ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ብዙ ጊዜ ተማሪዎች ለሥዕሉ ኢ-ንግግራዊ በሆነ መልኩ ምላሽ ቢሰጡ መልካም ነው፡፡ ሥዕሎቹ ኢ-ንግግራዊ ምላሾችን እንዲሰጡ በማድረግ ረገድ ጥሩ ዕድል ይሰጣሉ በማለት ይገልፃሉ፡፡

ተስፋዬና ማረው (1993፣63) እንዳሠፈሩት፣ በክፍል ውስጥ የሚከናወን የማዳመጥ ትምህርት በሥዕላዊ መግለጫዎች፣ በካርታዎች፣ በቅርፃ ቅርፆች፣ በምሥሎች፣ ወዘተ. አማካይነት ድጋፍ መስጠት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ እንደነዚህ ዓይነት የድጋፍ መስጫ መሣሪያዎች የማዳመጥን ክሂል ለማስተማርና ትርጉማዊ ለማድረግ አጋዥነታቸው የጎላ ነው፡፡

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አገልግሎት በተመለከተ Bowen (1982:IV)፣ መማር ውስብስብ ሂደት እንደሆነ ጠቁመው፣ ይህን ውስብስብ ሂደት በሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም ቋንቋን በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎችን እንደሚያነሳሳ ይገልፃሉ፡፡ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተማሪዎችን ለመማር ማነሳሳት ብቻ ሳይሆን፣ የትምህርቱን ይዘት በቀላሉና በተጨባጭ መልኩ እንዲገነዘቡት እንደሚያግዟቸውም ያብራራሉ፡፡

ንባብን ከማስተማራቸው በፊት ጽሑፎችን በጥንቃቄ መምረጥ ያስፈልጋል፡፡ ተገቢ ንባብን ለመምረጥ በቅድሚያ የንባብ መምረጫ ነጥቦችን ማወቁ ተገቢነት ስላለው አንድ ንባብ ሊያሟላ የሚገባ መመዘኛ ብዙ ነው፡፡ ከነዚህም መካከል የሚመረጠው ምንባብ በካርታ በግራፍ፣ በሠንጠረዥና በሥዕላዊ መግለጫዎች ቢደገፍ ለተማሪዎች ተገቢ፣ ጠቃሚና ቀላል እንዲሆን የጎላ ጠቀሜታ አለው፡፡ በጥንቃቄ የተመረጠ ጽሑፍ ደግሞ በተገቢው መንገድ የተላለፈውን መረጃ በቀላል ሂደት ለመውሰድ ያስችላል፡፡ የንባብ ፍጥነትንም ያጎለብታል (Nuttall 1982:25)፡፡

በሥዕል፣ በፍቶግራፍ፣ በሠንጠረዥና በቻርት መሰል በሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አስደግፎ ቃላትን ማስተማር በመካከለኛ የክፍል ደረጃ ለሚማሩ ተማሪዎች የቃላት ፍች ግልፅ እንዲሆንላቸው እየተመለከቱ ትምህርቱን መከታተል ይኖርባቸዋል (Wallace 1992፡42፣ Grains and Redman 1986፡76፣ Allen 1983:7)፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ለተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ከማስተማር ይልቅ በሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመጠቀም ተማሪዎች የቀደመ ዕውቀታቸውን መሠረት አድርገው የቃላትን ቅርፅ (የትኛው ከየትኛው ቃል ጋር አብሮ ሊገባ እንደሚችል) በመመርመር ራሳቸው ፈልገው እንዲያገኙ እንደሚያስችሉ (Harmer 2001:161) ይገልፃሉ፡፡

በድሉ (1996፣63-64) እንደሚገልጹት፣ ንግግር የተለያዩ ንዑሳን ተግባራትን የያዘ ሂደት እንጂ በአንድ ውስን ጊዜ የሚከናወን ተግባር አይደለም፡፡ ጥሩ ንግግር ቅድመ ዝግጅትን ይጠይቃል፡፡ ንግግር በሚቀርብበት ጊዜና ከንግግሩም በኋላ ሊተኮርባቸው የሚገቡ ተግባራት አሉ፡፡ እነዚህ ተግባራት የቅድመ ንግግር፣ የንግግርና የድኅረ ንግግር ተግባራት ተብለው ይከፈላሉ፡፡ መምህራን በንግግር ተግባራት ላይ ማድረግ ከሚገቸው ከተግባራት መካከል በሚታዩ መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ይህም መምህራን ተማሪዎችን የንግግር ክሂልን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ሲያስተምሩ በመጀመሪያ በተግባር እንዲከውኑ እያደረጉ በማስተማር በአጭር ጊዜ በሥርዓት ንግግር የማድረግን ሁኔታ እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል፡፡ ከዓይን አፋርነት ተላቀው አድማጭን ለመሳብ በሚችል መንገድ ንግግር የማድረግ ክህሎትን እንዲያዳብሩ ለማስተማርም ያግዛል፡፡

የሕትመት ውጤቶችን በተመለከተ በድሉ (1996፡13) ሲያብራሩ፣ ጸሐፊው የሚፅፈው ሕይወትን ነው፡፡ ሕይወት ደግሞ በድርጊት ብቻ ሳይሆን በቋንቋ አጠቃቀም ይንጸባረቃል፡፡ እውነተኛ የቋንቋ አጠቃቀም የአንድን ኅብረተሰብ ሐሳብ ከባህሉ ጋር አመሳጥሮ ያሳያል፡፡ ይህን በቋንቋ ክፍል ውስጥ መጠቀም ተማሪውን ካልተከለሰና ለማስተማሪያ እንዲሆን ሆን ተብሎ ካልተዘጋጀ፣ ዕውነተኛ የቋንቋ አጠቃቀም ጋር እንዲገናኝ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም ሥነ ጽሑፍ ሆን ተብለው ለሚዘጋጁ የማስተማሪያ ጽሑፎች ጠቃሚ አጋዥ መሣሪያዎች ናቸው ይሉናል፡፡ ይህንን ሐሳብ ተስፋዬና ማረው (1993፡26) መምህራን የተቀነጨቡ ውህድ አሃዶችን ከመጽሔት፣ ከጋዜጣና ከተለያዩ መጽሐፎች በመውሰድ አባዝተው ለተማሪዎቻቸው በክፍል ውስጥ በማደል መጠቀም የተለያዩ የቋንቋ ክሂሎችን ለማጎልበት አስተዋፅኦ አላቸው፡፡ ምክንያቱም ከራሳቸው፣ ከቤተሰባቸው እና ከሕብረተሰቡ የሕይወት ገጠመኝ የተቀዱ በመሆናቸው ዕውነተኛውን የቋንቋ ዐውድ ወደ መማሪያ ክፍል በማምጣት በቡድንና በጥንድ በመወያየት የመናገርና የማዳመጥ ክሂላቸውን የተገነዘቡትን በመጻፍ፣ የጻፉትን በማንበብ፣ የማንበብ ክሂሎቻቸውን ሊያዳብር ይችላል፡፡ በተጨማሪም ቃላትንና ሰዋስውን ለማስተማር መምህሩ ለቀረፁት የዕለት ትምህርት ዓላማ ማስፈፀሚያ ለተነደፈው ይዘት በተናጠልም ሆነ በቅንጅት ክሂሎችን እንዲሁም የተለያዩ የቃላት ዕውቀትንና የቋንቋ አጠቃቀምን ለማጎልበት የጎላ ጠቀሜታ እንዳላቸው ይገልፃሉ፡፡

የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለቋንቋ ትምህርት ያላቸው ፋይዳ ተደጋግሞ ተነሥቷል፡፡ የሚታዩ ትምህርት መርጃ መሣርያዎችን ባሕርያዊ አከፋፈል እንደ አገልግሎታቸው Bowen (1982፡13-14) በሦስት ምድቦች ይከፍሏቸዋል፡፡ እነዚህም ሥዕሎች፣ ሠሌዳዎችና ፕሮጀክተሮች ሲሆኑ በውስጣቸውም ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን እንደሚያካትቱ ምሁሩ ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም በሦስቱ አይነት የሚታዩ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሥር የሚካተቱትን ዝርዝር ተዛማጅ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ቀጥለን እንመለከታለን፤

- ሥዕሎች
    - የግድግዳ ላይ ሥዕሎችና ቻርቶች
    - ተከታታይ ሥዕሎች
    - ፍላሽ ካርዶች

- የቃላት ፍላሽ ካርዶች
- የሥዕል ፍላሽ ካርዶች
- የሥራ ካርዶችና የሥራ ወረቀቶች

➢ ሠሌዳዎች

- የማስታወቂያ ሰሌዳዎች
- የማሣያ ሰሌዳዎች
- ከወፍራም ሱፍ ጨርቅ የተሰራ ሰሌዳ
- መግነጢሳዊ ሰሌዳ

➢ ፕሮጀክተሮች

- ከአናት በላይ ፕሮጀክተሮች
- ስላይድ ፕሮጀክተሮች
- ሌሎች ፕሮጀክተሮች

ናቸው።

የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደት በቀላሉ ከቦታ ቦታ ሊንቀሳቀሱ መቻላቸውና በመጠነኛ ዋጋ አብዛኛዎቹን እንደልብ ማግኘት መቻሉ አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ለመጠቀም ብዙ አስቸጋሪ አለመሆናቸው ጠቀሜታቸውን ያጎላዋል፤ ግን እንደ መግነጢሳዊ ሠሌዳዎች እና ፕሮጀክተሮች ያሉት እንደልብ ሊገኙ አለመቻላቸው በተወሰነ ደረጃ በአጠቃቀም ችግር ሊኖር ይችላል።

### 2.3.3 የሚደመጡና የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

እነዚህ የሚደመጡና የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ድምፅንና ምሥልን አካተው የያዙ ናቸው። በመሆኑም በቋንቋው መማር-ማስተማር ሂደት ተማሪው በዓይኑ እየተመለከተ፣ በጆሮው እያዳመጠ እንዲማር የሚያስችሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ናቸው። Aggarwal (1996:153) እንደሚሉት፣ የሚደመጡና የሚታዩ  የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለተማሪዎች የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶችን ግልፅ ለማድረግ፣ ይበልጥ ለማረጋገጥ፣ የትክክለኛ ግንዛቤዎች፣ ትርጉምና አድናቆቶች ተዛምዶ ተዋሕደው መኖራቸውን ተማሪው እንዲለይ በማድረግ የሚያግዙት ተጨማሪ መሣሪያዎች ናቸው። ለመምህሩም ቢሆን የማስተማር ሂደቱን ይበልጥ

ተጨባጭ፣ ውጤታማ፣ አስደሳችና ትርጉም ያለው አድርጎ ለማቅረብ ያስችሉታል፡፡ እኒህ ምሁር አያይዘው በነዚህ የሚደመጡና የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የመገልገል ዓቢይ ዓላማ በተማሪውና በሚቀርበው የትምህርት ይዘት መካከል የሚኖረውን ግንኙነት ግልፅ፣ አስደሳችና ተጨባጭ እንዲሆን ሦስት ጎነዮሻዊ የመማር ሂደትን ማለትም ንሺ፣ ክፍፍልን (Classification) እና ማነቃቂያን (Simulation) በማሟላት ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡

Aggarwal (1996) አክለው እንደሚገልፁት፣ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም በተማሪውና በሚቀርበው የትምህርት ይዘት መካከል የሚኖረውን የግንኙነት መሥመር ማጥራት ነው፡፡ በመሆኑም የሚደመጡና የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመማር-ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች የሚተላለፋትን መረጃዎች እንዳይረሱ በምክንያት አስደግፈው እንዲገልፁ፣ በተግባር እንዲተረጉሙ፣ ትምህርቱ ተወዳጅ እንዲሆንና ምናባዊ ምሥል ፈጥረው ከተማሩት ጋር እንዲያዋሕዱ ያደርጋሉ፡፡ በአጠቃላይ ተማሪዎች የሚያጋጥማቸውን በቋንቋ የመግባባት ክፍተት የመሙላት ኃይል አላቸው፡፡

Burns et al. (1999:46)፣ ዓለም (1995:26) እና McDonough and Shaw (1994:14) እንደሚገልጹት፣ የሚደመጡና የሚታዩ መሣሪያዎችንና "ኦዲዮቪዲዮ" ማቴሪያሎችን በመጠቀም እያዳመጡ፣ ማስታወሻ እንዲይዙ፣ በአንድ ርዕስ ዙሪያ አጫጭር ንግግሮችን እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የተቀናጀ የቋንቋ ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ መሆናቸውን ይገልፃሉ፡፡

Gagne, et al. (1992:225) በሚደመጡና በሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ምድብ ሥር የሚካተቱ መርጃ መሣሪያዎች ለእይታ የቀረቡ መረጃዎች (demonstrations)፣ ፊልሞች፣ ከተቀዳ ድምፅ ጋር የተቀረፁ ውጤቶች፣ የድምፅ ፊልም፣ ጥናታዊ ጉዞ (study trip)፣ ቴሌቪዥን፣ ቪዲዮ ቴፖችና የመሳሰሉት እንደሆኑ ይገልፃሉ፡፡

## 2.4 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም

እንደ Clark and Irbing (1996:63) አገላለፅ፣ የመማር-ማስተማር ሂደቱን ግልፅና ተጨባጭ ለማድረግ ተገቢ የሆነ የትምህርት መርጃ መሣሪያ መምረጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህም ተግባር በአግባቡ ሊከናወን ይገባል፡፡ አንድ መምህር መርጃ መሣሪያውን መምረጥ የሚገባው በትምህርት ቤት ውስጥ ብዙ መሣሪያዎች ስለሚገኙ ወይም በትምህርት ዕቅድ ውስጥ ለዚህ ተብሎ

የተዘጋጀውን ዓምድ ለመሙላት ወይም የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚሰጡትን ጠቀሜታ በመቀበል መሆን የለበትም። በመሆኑም አንድን ትምህርት ለማስተማር ሲያዘጋጁ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው የሚወስኑት ተጨባጭ የሆኑ ምክንያቶችን ወይም መመዘኛዎችን በመመርኮዝ ነው። ከእነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚቀርጿቸው የትምህርት ዓላማዎች፣ የሚያስተምሯቸው ይዘቶች፣ የተማሪዎቻቸው ቁጥር፣ ሁኔታ፣ ደረጃና ብስለት፣ የሚመርጡት የማስተማር ዘዴ፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለመጠቀም መምህሩ ያለው ችሎታ፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የማግኘት ዕድልና በተግባር የሚታዩ ችግሮች ለምሳሌ የጊዜ፣ የኢኮኖሚ፣ የአስተዳደርና የቦታ፣ ናቸው። ይህንን ሐሳብ በማጠናከር ተስፋዬና ማረው (1993፡12-13) እንደገለጹት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚሰጡት ጥቅም ከፍተኛ እንደሆነ ብዙ አያጠያይቅም። ይሁን እንጂ እንደ ትምህርቱ ይዘት ባሕርይ አግባብ ባላቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም ተገቢ ይሆናል። የትምህርት መርጃ መሣሪያን መጠቀም የሚገባው አንድን ትምህርት ለማብራራትና ተጨባጭ ለማድረግ የሚረዳ መሆኑ ሲታመንበት ብቻ ነው። ከነዚህ ምሁራን የምንገነዘበው በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም የሚገባው አስፈላጊነቱ በሚገባ ተጢኖ ሲታመንበት መሆኑን ነው።

### 2.4.1 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የአመራረጥ መርሕ

መምህራን፣ በመማር-ማስተማር ሂደት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአጋዥነት ለመጠቀም በቅድሚያ ለየትኛው የትምህርት ዓላማ መቼ መቅረብ አለበት? እንዴትስ መቅረብ ይኖርበታል? ለነማን? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥ መርሕ መከተል ይኖርባቸዋል። ይህን መርሕ ተከትሎ የሚመረጡ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለትምህርቱ ዓላማ ግብ-መምታት፣ ለመምህሩ የማስተማር ተግባር መቀላጠፍ፣ ለተማሪው የትምህርት አቀባበል ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ መሆናቸውን በመስኩ የተካሄዱ ጥናቶች ያረጋግጣሉ።

እንደ Aggarwal (1996:158-160) ገለጻ፣ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ሂደት ውስጥ መከተል የሚገባንን መርሕ በተመለከተ የአዘገጃጀት፣ የአመራረጥ፣ የአካላዊ ቁጥጥር፣

የአቀራረብ፣ የፍላጎት ምላሽና የግምገማ መርሕ በማለት በዝርዝር ይገልጿቸዋል። ከነዚህ መካከል ለዚህ ጽሑፍ የሚስማማውን የአመራረጥ መርሕ ብቻ በመውሰድ ቀርቧል፤

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ውጤታማነት የሚረጋገጠው ለታሰበላቸው የትምህርት ዓላማ ግብ መምታትና ለሚማሩባቸው ተማሪዎች የተለያዩ ባሕርያት አመቺ ሲሆኑ ነው። በዚህም ሁኔታ የሚመረጡት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉት የሚከተሉትን የአመራረጥ መርሖዎች (principles of selection) ሲከተሉ ነው፤

- ከተማሪዎች ዕድሜ፣ ፍላጎት፣ ማኅበራዊና ባህላዊ ዳራ፣ የክፍል ደረጃ እና ከሌሎች ባሕርያት ጋር የሚጣጣሙ መሆን አለባቸው።
- ስሜትን ከማነሣሣትና ፍላጎትን ከመቀስቀስ ባሻገር የተለዩ ትምህርታዊ እሴቶች (specific educational values) ያሏቸው ሊሆኑ ይገባል።
- የሚወክሉትን እውነተኛ ነገር በትክክል መምሰል ይኖርባቸዋል።
- የተፈለገውን የትምህርት ዓላማ እውን ለማድረግ እገዛ የሚያደርጉ መሆን ይኖርባቸዋል።

አንድ የትምህርት መርጃ መሣሪያ በመማር-ማስተማር ሂደት ለመጠቀም በሚመረጥበት ጊዜ ከተማሪዎቹ ዕድሜና የትምህርት ደረጃ አንፃር፣ እጅግም ያልተወሳሰበና በቀላሉ የሚረዱት ሊሆን ይገባል። በተጨማሪም በሚመረጠው ትምህርት መርጃ መሣሪያ ከሚማሩት ተማሪዎች መካከል የተለያዩ አካል ጉዳተኞች መኖርና አለመኖራቸውን፣ ካሉም በትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ መጠቀም መቻላቸውንና አለመቻላቸውን፣ እንዲሁም የተማሪዎችን ፆታዊ ልዩነት ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን አስቀድሞ ማጤን ይገባል።

የሚመረጠው የትምህርት መርጃ መሣሪያ ጠቀሜታው በውበቱና በሳቢነቱ የተማሪዎችን የትምህርት ፍላጎት ቀስቃሽ ብቻ መሆን የለበትም። ከዚህ ባለፈ ትምህርታዊ እሴት ያለውና የተማሪውን ሁለንተናዊ ባሕርይ ከመለወጥ አንፃር የተለየ ሚና የሚጫወት መሆን ይኖርበታል።

የሚመረጠው የትምህርት መርጃ መሣሪያ በተቻለ መጠን የሚወክለውን እውነተኛ ነገር ሊመስል ይገባል። የሚወክለውን እውነተኛ ነገር ካልመሰለ የትርጉም አሻሚነትን ከመፍጠሩ በላይ በተማሪዎቹ ዘንድ ተቀባይነትን ያጣል። የመምህሩንም የማስተማሪያ መሣሪያ አመራረጥ ብቃትና የትምህርቱን ይዘት ተዓማኒነት ከጥያቄ ውስጥ ሊያስገባው ይችላል።

የሚመረጠው የትምህርት መርጃ መሣሪያ የተፈለገውን የትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያግዝ ሊሆን ይገባል፡፡ የተፈለገውን የትምህርት ዓላማ ከማሳካት አንፃር የሚመረጠው የትምህርት መርጃ መሣሪያ ቀጥተኛ ሚና የማይጫወት ከሆነ ምንም እገዛ እንዳላደረገ ይቆጠራል፡፡

### 2.4.2 የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥ

መምህራን በመማር-ማስተማር ሂደት የዕለት ትምህርት ዕቅድ ከማዘጋጀታቸው በፊት የትኛውን መርጃ መሣሪያ በትምህርት ዕቅድ ውስጥ ማካተት እንዳለባቸውና በሚያስተምሩበት ወቅትም በዕቅዱ መሠረት መገልገል እንዳለባቸው በበርካታ ጥናቶች የተደገፈና የሚታመንበትም ነው፡፡ ከዚህ አንፃር Clark and Irbing (1996:53) መምህራን ማጤን ያለባቸውን ነጥቦች እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ፤

- የዕለት ትምህርት ዓላማንና የመርሐ ትምህርቱን አጠቃላይ ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያግዝ መሆኑን፣
- ዝርዝር የትምህርት ዓላማን የሚያሳካ መሆኑን፣ በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችን ትምህርታዊና ባህላዊ ዳራ፣ ቋንቋውን፣ ዕድሜ፣ ፆታ፣ ፍላጎትና ቋንቋውን ለመማር የሚፈልጉበትን ምክንያት ከግምት ውስጥ ማስገባትና በተጨማሪም እንደዓይን ዓፋርነት፣ ጭንቀት ወይም ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር ከሚፈጠር የመግባባት ችግር የተነሳ ትምህርቱን ሊያደናቅፉ የሚችሉ የመግባቢያ ዕክሎችን ያገናዘበ መሆኑን፤ የትምህርት ዕቅድ ሲቀረጽ የትኛውን ክሂል ለማዳበር ታስቦ እንደሆነ ያገናዘበ መሆኑንና ለዕለቱ ትምህርት የሚመረጡ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እንደልብ (በቀላሉ) ሊገኙ ሊተገበሩና ከቦታ ቦታ ሊንቀሳቀሱ የመቻል (አለመቻል) ሁኔታ ሊታሰብበት የሚገባ መሆኑን በአፅንኦት አስፍረዋል፡፡

### 2.4.3 የትምህርት መሣሪያዎችን ለመምረጥ የሚውሉ መመዘኛዎች

በመማር-ማስተማር ሂደት የተስማማ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ለማግኘት የመምረጡ ሂደት ቀላልና ተገቢ የሚሆነው መመዘኛዎችን በመመርኮዝ ሲከናወን ነው፡፡ በርግጥ ምርጫውን ለማከናወን የምንጠቀምባቸው መመዘኛዎች እንደትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ ምድብና ቅርፅ ይለያያሉ፡፡ ሆኖም ግን አብዛኛዎቹን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለመምረጥ የሚያገለግሉና

የጋራ የሆኑት ጠቃሚነት (relevance)፣ ተስማሚነት (appropriateness)፣ ትክክለኛነት (accuracy) እና ግልፅነት (clarity) ናቸው (Farrant 1984)፡፡

**ሠንጠረዥ አንድ**፡- የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለመምረጥ የሚያገለግሉ መመዘኛዎች

| ተ.ቁ. | መመዘኛ | መግለጫ |
|---|---|---|
| 1 | ጠቃሚነት (relevance) | የትምህርቱን ይዘት ለማቅረብ ያለው ጠቀሜታና የታሰበውን ይዘት ለማስተላለፍና የተተለሙትን የትምህርት ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ያለው አስፈላጊነት፣ |
| 2 | ተስማሚነት /ከተማሪው አቅም ጋር መመጣጠኑ (appropriateness) | ለተማሪዎች ልምምድና የብስለት ደረጃ ያለው ተስማሚነት ከተማሪዎች የመረዳት ችሎታ በላይና በታች አለመሆኑ፣ |
| 3 | ማራኪነት (attractiveness) | ማራኪ ቀለም ያለውና ትክክለኛ ንድፍ የያዘ የተማሪዎችን ስሜት የሚያረካ፣ |
| 4 | ትኩረት (focus of attention) | በተፈላጊው የትምህርት ክፍል ላይ ተማሪዎች እንዲያተኩሩ ማድረግ<br>ጠቃሚውን የትምህርት ሃሳብ ለተማሪዎች በግልፅ የሚያሳይ (የሚያመላክት) |
| 5 | መጠን (size) | ለተማሪዎች በሚገባ የሚታይ (ክሱት) የሆነ መጠን ያለው |
| 6 | ትክክለኛነት (accuracy) | እውነተኛ ነገር ወይም ድርጊት የተመጣጠነ፣ ትክክለኛነት እንዲታይበት ማድረግ፣ እውነታው ያልተዛባ መሆን፣ |
| 7 | ግልፅነት (clarity) | ለሁሉም ተማሪዎች በግልፅ የሚስማማና የሚታይ መሆን አለበት፡፡<br>ለሁሉም ክፍሎች ግልፅ የሆነና ከውስብስብነትና አደናጋሪነት የፀዳ መሆን |
| 8 | ቀላልነት (simplicity) | ለተማሪዎች መረዳት የማያስቸግርና በብዙ ጭብጦችና ሐሳቦች ያልተሞላ |

**ምንጭ**፡- (Farant 1984:13)

### 2.4.4 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ባሕርያት

የትምህርት መርጃ መሣሪያ ለተፈለገው የትምህርቱ ዓላማ ማስፈፀሚያ የመማር-ማስተማር ሂደቱ ውጤታማ እንዲሆን ከመዘጋጀቱ፣ ከመመረጡና በአገልግሎት ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ ምን ዓይነት ባሕርይ እንዳለውና በምን ዓይነት ሁኔታ መዘጋጀት፣ መመረጥና በአገልግሎት ላይ መዋል እንዳለበት አስቀድሞ ሊጤን ይገባል፡፡ ይህንን ተግባራዊ ማድረግ ደግሞ አዋቂነት ነው፡፡

እንደ Aggarwal (1996:157) አገላለፅ፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ባሕርያት እንደሚከተለው ይቀርባሉ፤

- በሙከራ የተረጋገጡ፣
- ለማጓጓዝ ችግር የማይፈጥሩ፣
- ከትምህርቱ ዓላማ ጋር የሚዛመዱ፣
- ትርጉም ሰጭና ምክንያታዊ፣
- ዋጋቸው ርካሽና ተመጣጣኝ፣
- ለዕለቱ ትምህርት አገልግሎት የሚሰጡ፣ ጊዜያቸውን የጠበቁ፣
- ተማሪዎች ሊያዩዋቸው በሚችሉበት መጠን የተዘጋጁ፣
- ለአያያዝ ቀላልና ምቹ የሆኑ፣
- ተማሪዎችን ለትምህርት የሚያነሣሡ፣
- ከተማሪዎች ዕድሜ፣ ደረጃ፣ ባህላዊ፣ ማህበራዊ ዳራና ፍላጎት ጋር የተስማሙ እና
- ለማንኛውም ለሚሠሩበትና እንዲያገለግሉበት ለታሰቡበት ዓላማ ትክክለኛ

መሆን አለባቸው፡፡

## 2.5 የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም

በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተገቢ መመዘኛ ተጠቅሞ መምረጥ ብቻ የሚፈለገውን ዓላማ ለማሳካት ያስችላል ለማለት አያስደፍርም፡፡ የታሰበውን የትምህርት ዓላማ ለማሳካት በተገቢ መንገድ የተመረጡትን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በአግባቡ በጥቅም ላይ ማዋል ያስፈልጋል፡፡ Heinich et al. (1996:22) እንደሚገልፁት፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ከተመረጡና ከተደራጁ በኋላ ቀጥሎ የሚመጣው ሥራ መምህራን ራሳቸው መርጃ መሣሪያውን

ለማስተማር ተግባር እንዴት ይገለገሉባቸዋል? ተማሪዎችውንስ በመርጃ መሣሪያዎች በመገልገል ትምህርቱን በቀላሉ እንዲረዱ እንዴት ይመሯቸዋል? የሚሉት ቁልፍ ጥያቄዎች በመርጃ መሣሪያዎች አጠቀቀም ረገድ የሚኖረውን ሁኔታ በግልፅ የሚያሳዩ ናቸው፡፡

የመማር-ማስተማሩን ሂደት እውን ለማድረግ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአግባቡ መጠቀም ተገቢ ነው፡፡ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአግባቡ መጠቀም በነገሮች ላይ ለሚኖረን እሳቤ እና ግንዛቤ ተጨባጭ መሰረት የሚጥሉ፣ ለግንዛቤያችን ትርጉም የሚሰጡ፣ ሐሳባችንን በተሟላ ትርጉም የሚገልፁ፣ ለቃላዊ ትምህርት በሽታ ፈዋሽ መድኃኒት እንዲሆኑ ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እኒህ ምሁር የሚደመጡና የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአግባቡ መጠቀም የሚያስገኘውን ፋይዳ (Aggarwal 1996:154) በሚከተለው መልኩ ይገልፁታል፤

1. **ጤናማ የክፍል ውስጥ መስተጋብር እንዲፈጠር ማበረታታት (Encouraging healthy classroom interaction)**

   ቀደም ሲል ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት እንደሚያነሳሱ አይተናል፡፡ ስለዚህ በዚህ አንጊነታቸው፣ አነቃቂነታቸውና በንቃት የማሳተፍ ኃይላቸው፣ እውነተኛ ነገር ወካይነታቸው ወዘተ. ለመማር-ማስተማሩ ሂደት መሣካት ጤናማ የክፍል ውስጥ መስተጋብር ይፈጥራሉ፡፡

2. **ትምህርቱን በትምህርት መገናኛ ማሰራጨት (Spread of education on a mass scale)**

   በተለያየ አካባቢ ለሚኖሩ ተማሪዎች ቴክኖሎጅን ተጠቅሞ (ሬዲና፣ ቴሌቪዥን ወዘተ.) ትምህርትን በርቀት በአንድ ጊዜ ለማዳረስ አመች ናቸው፡፡

3. **ሳይንሳዊ እውነታዎችን ማስተዋወቅ (Promotion of scientific temper)**

   ትምህርትን በንድፈ ሐሳብ ብቻ ሳይሆን በተግባር ለማቅረብ ያስችላሉ፡፡ ተማሪዎች ስለአንድ ነገር ዕውነታ በቃል ከመስማት ይልቅ ሰርቶ በማሳየት ነገሮችንና ክስተቶችን በመመልከት ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ እንዲረዱት ያግዛሉ፡፡ በአጠቃላይ የመማሪያ ክፍሉ አካባቢ ለፈጠራ የተመቻቸ እንዲሆን የላቀ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡

## 4. ግለሰባዊ ልዩነቶችን ማጥበብ (Meeting individual differences)

በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች በመካከላቸው በተለያዩ ምክንያቶች ግለሰባዊ ልዩነቶች ይኖሯቸዋል፡፡ ለምሳሌ አንዳንዱ ተማሪ መናገር የሚወድ፣ ሌላው ለእይታ የቀረቡ ነገሮችን በማየት መማር የሚፈልግ፣ ሌሎች ደግሞ በእጃቸው በመነካካት እያደረጉ መማር የሚመርጡ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዚህ አንፃር የተለያየ ዝንባሌ ያላቸው ተማሪዎች በአንድ ክፍል ውስጥ ይኖራሉ፡፡ ስለዚህ እንደፍላጎታቸው እንዲማሩ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥሩላቸዋል፡፡

## 5. ግልፅነት (Vividness)

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለመማር-ማስተማር ዓወድ ግልፅነት ከፍተኛ ፋይዳ አላቸው፡፡ ለምሳሌ አንድ የጥንት ታሪክ የሚያወራ ጉዳይ በጥሬ ለማስተማርያነት ከሚቀርብ ስለጉዳዩ በተቀነባበረ ተንቀሳቃሽ ፊልም አማካይነት ቢቀርብ ሐሳቡ የበለጠ ለመረዳት ይቀላል፡፡

## 6. እውነቱን እንዳለ ማቅረብ (Realism)

ለትምህርት የሚቀርቡ ይዘቶች ባሉበት ሁኔታ ያላቸው ገፅታ እንዲታይና እንዲዳሰስ ለማድረግ ያስችላሉ፡፡ ለምሳሌ ፊልሞችና ዓውደ-ርዕዮች በመጠቀም ረጅም ጊዜ የሚወስድን የንባብ ሥራ በጥቂት ሰዓታት ጊዜ ውስጥ ለመገንዘብ ይረዳሉ፡፡

## 7. ጊዜና ጉልበትን መቆጠብ (Saving of energy and time)

ረቂቅ ሐሳቦችን/ክስተቶችን/ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አማካይነት በቀላሉ እንደገለፁ፣ ከተማሪው ስሜት ጋርእንዲዋሃዱ በማድረግ አጉልቶ በማቅረብ ለመረዳት በሚደረገው ጥረት የመምህሩንም ሆነ የተማሪዎችን ጊዜ ይቆጥባሉ፡፡

## 8. ምናባዊ አስተሳሰቦችን ያጠራሉ (Clear images)

አንድን ሐሳብ በማብራራት ከማቀረብ ይልቅ በአይን በሚታዩ፣ በጆሮ በሚደመጡ፣ በእጅ በሚዳሰሱ፣ በምላስ በሚቀመሱ እና በአፍንጫ በሚሸተቱ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አማካይነት ቢቀርብ ሐሳቡ ግልፅነት ይኖረዋል፡፡ ለስሜት ሕዋሳት በሚቀርብ መንገድ

የቀረበ ትምህርት ተማሪው የሚቀስመው ልምድ ቀጥተኛ፣ ተጨባጭና ቋሚ ከመሆኑ ባሻገር ትምህርቱን ተፈጥሮአዊ ለማድረግ ያስችላል።

9. **በዓይነት መለያየት** **(Variety)**

በድምፃዊ ወእይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የታገዘ ትምህርት ተማሪው በአይነትና በመጠን የተለየዩ ነገሮችን በመምህሩም ሆነ በተማሪው እጅ እንዲገኝ ያስችላሉ። ይህም ማለት ተማሪውም በተገቢ መንገድ እንዲማር፣ መምህሩም እንዲያስተምር ምቹ ሁኔታዎች ይፈጥሩላቸዋል።

10. **አዳዲስ ነገሮችን ለመገንዘብ** **(Helping in fixing up new learning)**

በተማሪው አዕምሮ አዳዲስ ነገሮች/ዕውቀቶችና ክሂሎች እንዲቀረፁ፣ ተቀርፀውም በተገቢው ጊዜና ቦታ በተግባር እንዲገለገሉባቸው ያስችላሉ። ምክንያቱም የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የተለያዩ ተግባራትንና ልምዶችን በማቅረብ የተማሪዎችን ስሜትና ፍላጎት በማነሳሳት፣ ትኩረታቸውን ወጥሮ በመያዝ ወደሚፈለገው ግብ እንዲያመሩ ያደርጋሉና።

11. **ትኩረትን ለመሳብ ማገዝ** **(Helpful in attracting attention)**

በመማር-ማስተማር ሂደት በተማሪዎች ፈላጎት ላይ የተመሰረተ የትምህርት አቀባበል ላይ ትኩረት የሰጠ ዘላቂነት ያለው አውድ በመፍጠር የትምህርት አሰጣጥ ሂደቱን ምቹና ማራኪ ያደርጋሉ፤ የመምህሩን የሥራ ጫና ይቀንሳሉ።

12. **በማሰተማር መርሕ ላይ የተመሰረቱ** **(Based on maxims of teaching)**

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ተጠቅሞ ማስተማር መምህሩ ትምህርቱን ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ፣ ከሚታወቅ ወደማይታወቅ እና ተግባራዊ በሆነ መልኩ ለማስተማር ያስችሉታል።

13. **የማስታወስ ችሎታን ይዞ የማቆየት ብቃት** **(Receptivity)**

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለስሜት ቅርብ ስለሆኑ (በዓይን ስለሚታዩ፣ በእጅ ስለማዳሰሱ . . .) የትምህርት ልምዶችን የማስታወስ ችሎታን ይዞ የማቆየት ኃይል አላቸው።

## 14. ትምህርቱን ለመያዝ፣ ለመፈተሽ ወይም የትምህርቱን ባሕርይ ለመመርመር ዕድል መስጠት (Opportunities to handle and manipulate)

ድምፃዊ ወእይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚቀርበውን ትምህርት ተማሪዎች በአዕምሮአቸው እንዲይዙት፣ የተማሩትን መነሻ አድርገው አካባቢያቸውን እንዲፈተሹበት እና እንዲመራመሩበት እድል ይፈጥራሉ።

## 15. ነፃነት (Freedom)

ስለ መርጃ መሣሪያዎቹ በመነጋገር፣ መርጃ መሣሪያዎችን በማንቀሳቀስ፣ በመነካካት፣ በመርጃ መሣሪያዎች በመዝናናት (በመደሰትና በመሣሣቅ) ብሎም ሰለመርጃ መሣሪያዎቹ አሰራር፣ ቀለም፣ ወዘተ. አስተያየት በመስጠት እንዲማሩ ለተማሪዎች ነፃነት ይሰጣሉ። በዚህ ዓይነት ስሜት ውስጥ ተማሪዎችን በማስገባት መምህራን ማሠራት ቢፈልጉ፣ ተማሪዎች ደግሞ እንዲሰሩ ቢታዘዙ ወይም የመሥራት ፍላጎት ቢኖራቸው እንደልባቸው በተግባራዊ ተሳትፎ ቋንቋውን እንዲማሩ ያደርጋሉ።

## 16. ለቃል ትምህርት በሽታ ፈዋሽ መድኃኒት መሆን (Antideste to the disease of verbal instruction)

በቃል የሚቀርብ ትምህርት የሚኖረውን ችግር በመቅረፍ ረገድ ተወዳዳሪነት እንደሌላቸው ያጠይቃል። በመሆኑም የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የትምህርቱን ሂደት በቃል ከማቅረብ ወደ ተግባራዊ ተሳትፎ ያሸጋግራሉ። ለተማሪዎች የሚቀርበው ትምህርት ግልፅ እንዲሆንና ትክክለኛነት እንዲላበስ ያስችላሉ። ለተማሪዎች በቃል በርካታ ቃላትና ሐረጋትን ልናስተምር እንችላለን፤ ቃላትንና ሐረጋትን በቃል ብቻ ማስተማር በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ ቃላትና ሐረጋትን ለማፍለቅ ቢያስችልም ተማሪዎች በቃል የተነገሯቸውን ቃላትና ሐረጋት በሙሉ በአዕምሮአቸው ይዘው መተርጎምና መጠቀም አለመቻል ችግር አለ። በዚህ ረገድ ተማሪዎች በቃል የተነገራቸውን ቃላትና ሐረጋት የመርሳት ችግር ይገጥማቸዋል ማለት ነው። ስለዚህ ይህን የመርሳት፣ የተማሩትን ትምህርት አስታውሶ የመጠቀም ችግር የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በመጠቀም ይቃለላል።

### 17. የበለጠ መነሣሣትን መፍጠር (Best motivators)

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት የማነሳሳት ኃይል ስላላቸው ስሜታቸውን በመሣብ ትኩረታቸው ወደ ትምህርቱ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

### 18. እውነተኛ የትምህርት ልምዶችን መወከል (Vicarious experiences)

አንድን አዲስ ልምድ በተለመደው የማስተማር ዘዴ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን ይህን አዲስ ልምድ ለተማሪ ማቅረብ ተግባራዊ የማይሆንበትን ጊዜያት ይበረክታሉ፡፡ ምክንያቱም በዚህ አዲስ ልምድ ውስጥ በርካታ ለትግበራ የሚያስቸግሩ ሁነቶች ያጋጥማሉ፡፡ ለምሳሌ አዲስ አበባ ለሚማር ተማሪ የሚቀርብለት ምንባብ "የኢትዮጵያ ብርቅዬ እንስሳት" የሚል ሲሆን ብርቅዬ እንስሳት ወደሚገኙበት ቦታ ተማሪውን ወስዶ በአካል ለማሣየት ሁኔታዎች ላይፈቅዱ ይችላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለችግር ደራሽ ናቸው፡፡ ማለትም የተለያዩ ብርቅዬ እንስሳትን ምስል /ሥዕል በመጠቀም ማስተማር ይቻላል፡፡ ምስላቸውን ተጠቅሞ የብርቅዬ እንስሳዎችን ምስል ተማሪዎች ከሚያነቡት ነገር ጋር አዋህደው ትምህርቱን ለመገንዘብ ይችላሉ፡፡ በዚህ ረገድ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የወካይነት ሚና ይጫወታሉ ማለት ይቻላል፡፡

## 2.5.1 የትምህርት መርጃ መሣርያዎችን የማቅረብ (የማሳየት) መርሕ

Aggarwal (1996:155-156) የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም መርህ የሚኗቸው በሚከተሉት ነጥቦች ይንፀባረቃሉ፤

- መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለማስተማሪያ መርጃነት ከመጠቀማቸው በፊት መርጃ መሣሪያዎቹን በጥንቃቄ በዓይነ ሕሊናቸው መቃኘትና ስለትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ በቂ ግንዛቤ መጨበጥ ይኖርባቸዋል፡፡ በሌላ አባባል የትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹን አካላዊ ገፅታም ሆነ ምንነት በመጀመሪያ ለራሳቸው መረዳት ያስፈልጋል፡፡
- በክፍል ውስጥ ለመማር-ማስተማር መምህራን በአጋዥነት የሚጠቀሙባቸውን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፣ የአፈታት፣ የአገጣጠም፣ የአሠራርና የአጠቃቀም ቴክኒኮችን በቅድሚያ ማወቅና መሞከር መቻል አለባቸው፡፡

- የክፍሉ ተማሪዎች በሙሉ መመልከት በሚችሉበት ሁኔታና በምልከታውም የሚፈለገውን ዕውቀትና ክህሎት ለመቅሰም ያስችላቸው ዘንድ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በትክክል በሚታይ ቦታ ሊቀመጡ ይገባል፡፡
- በአጠቃቀም ጊዜ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ ጉዳት እንዳይደርስባቸው በአጠቃቀም ጊዜ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ ላይ ሙሉ ትኩረት ለመስጠት ያመች ዘንድ በተቻለ መጠን ትኩረትን የሚሰርቁ ነገሮችን ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡
- ከትምህርቱ በኋላ ተማሪዎች ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች ፈጣን መልስ መስጠትና ከዕለቱ የትምህርት ዓላማ ጋር ያለውን ተዛማጅነት ተገቢነትና የአጠቃቀም ቴክኒክ ብቃትን መገምገም ያስፈልጋል፡፡

### 2.5.2 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ሥነልቦናዊ ሁኔታ (The psychology of using teaching aids)

የትምህርት ልምዶችን ተጨባጭና አሳማኝ በማድረግ ማቅረብ ከእውነታ ጋር ያዛምደዋል፡፡ የመማር-ማስተማሩን ሂደት ውጤታማ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም ቋንቋን በመማር-ማስተማር ረገድ ለንባብ ከሚቀርበው ጉዳይ በተጨማሪ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች (ሥዕሎች፣ ፊልሞች፣ ተንቀሳቃሽ ፊልሞች፣ መቅረፀ ድምፆች፣ ትምህርታዊ ጨዋታዎች (Mockups)፣ ቴሌቪዥን፣ ወዘተ.) ከመሳሰሉት እውነተኛ የትምህርት ልምድ ውክልና ማግኘት ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የተደገፈ ትምህርት በተማሪው ዘንድ እንደ እውነታ እንዲታሰብ፣ የወከለውን የትምህርት ልምድ እውነተኛ ውክልና አምኖ እንዲቀበል በአጠቃላይ የቀረበው ትምህርት በሃቅ ላይ የተመሠረተ መሆኑን እንዲገነዘቡ ያስችላሉ፡፡ ከዐውድ ጋር ለማገናኘት የሚደረገው ጥረት ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይሆንም፡፡

የመማር-ማስተማሩን ሂደት ከስሜት ሕዋሳት ጋር በማዋሐድ የተማሪውን የመማር ፍላጎት በመቀሰቀስ፣ የተማሪውን ትኩረት ወደሚፈለገው የባሕርይ ለውጥ በማምጣት ረገድ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የጎላ አስተዋፅኦ እንዳላቸው ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የቋንቋውን ትምህርት ተግባቦታዊ በማድረግ ከንድፈ ሐሳብ ወደ ተግባር እንደሚያሸጋግሩም ተጠቁሟል፡፡ ከዚህ አንፃር Aggrawal (1996:157) እንደሚሉት፣ አንድ ተማሪ

ከቀረበለት ትምህርት ውስጥ በተለያዩ የስሜት ሕዋሳቱ አማካይነት የሚቀስመው የትምህርት ልምድ ምን ያህሉን ለረጅም ጊዜ ለማስታወስ እንደሚጠቅመው Cubon (1969)ን በመጥቀስ የሚከተለውን አስፍረዋል፤ ከቀረቡት ትምህርቶች ውስጥ በስሜት ሕዋሳት አማካይነት የማስታወስ ችሎታ ከመቶ ስሌት ሲታይ፣

| | |
|---|---|
| በመቅመስ | 1% |
| በመንካት | 1.5% |
| በማሽተት | 3.5% |
| በማዳመጥ | 11% |
| በማየት | 83% |

እንደሚይዙ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሰዎችን የማስታወስ ደረጃ ከሚነበብ ነገር 10%፣ ከማዳመጥ 20%፣ ከሚታይ 30%፣ እና እየሠሩ ከሚናገሩት 90% የማስታወስ አቅም መፍጠር እንደሚቻል ይገልፃሉ፡፡

ከዚህ በጥናት የተደገፈ የምሁሩ ሐሳብ በክፍል ውስጥ የሚቀርብ የቋንቋ ትምህርት በተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተደግፎ ሲቀርብ የመርጃ መሣሪያዎቹ ከስሜት ሕዋሳት ጋር ያላቸው ቅርበት የቀረበውን የትምህርት ይዘት ዝርዝር ነጥቦች የማስታወስ ችሎታ እንደሚወስን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ከስሜት ሕዋሳቶች ውስጥ ተማሪዎች በማየት የሚማሩትና የተማሩትን በረጅም የማስታወስ አቅም እንዲፈጥርላቸው ብሎም በደረጃ ሲታይ ደግሞ የትምህርቱ አቀራረብ ተማሪዎችን አሳታፊና አወያይ ከሆነ ትምህርቱን የበለጠ አይረሴ እንደሚያደርገው መረዳት ይቻላል፡፡

### 2.5.3 በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙ ችግሮች

በመማር-ማስተማር ሂደት የዘመኑ ተፈላጊ የማስተማር ዘዴ ተማሪ-ተኮር የማስተማር ዘዴ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ያላቸው አስተዋፅኦ የጎላ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ተፈላጊነቱ ከቀን ወደቀን እየጨመረ ቢመጣም በአጠቃቀም ላይ የሚታዩ መጠነኛ ችግሮች ይኖራሉ፡፡ እነዚህንም Aggrawal (1996:159-161) በሚከተለው አኳኋን ይገልጿቸዋል፤

## 1. የተማሪዎች ግድየለሽነት

በጥራትና በተገቢ ሁኔታ የተዘጋጁ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመማር-ማስተማር ሂደት መጠቀም የተማሪዎችን የትምህርት ፍላጎት በከፍተኛ ሁኔታ ይጨምራል። በስርዓት ያልተዘጋጀ፣ ግልፅ የሆነ ዓላማ ያልያዘ፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ጠቀሜታ የሌለውና የተማሪዎች ፍላጎት እንዲቀንስና እምነት እንዲያጡ ብሎም ግድ የለሽ እንዲሆኑ ያደርጋል።

## 2. የገንዘብ ችግር

የትምህርት መርጃ መሣሪያን ለመጠቀም መምህራን የተዘጋጀውን ለመግዛትም ሆነ ለማዘጋጀት ወይንም የትምህርት መርጃ መሣሪያን በተመለከተ ሥልጠና ለመውሰድ የገንዘብ ችግር ትምህርት ቤቱ ካጋጠመው የተፈለገው የትምህርት መርጃ መሣሪያ ላይዘጋጅ ወይም ላይገዛ ይችላል፤ በሥልጠና ላይም መምህሩ ወይም የትምህርት ባለሙያው ላይሳተፍ ይችላል።

## 3. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ፋይዳ ቢስ መሆን

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ፋይዳቢስነት የሚከሰተው በመምህሩ ችሎታ ማነስና ግድየለሺነት ወይም ተገቢ የሆነ ምርጫ ባለማካሄድ፣ የአቀራረብና አጠቀቀም ችግር፣ በአጠቃላይ መርሕን ያልተከተለ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መረጣና አጠቃቀም የተነሳ ነው። እንደ እነዚህ ዓይነት ችግሮች ካሉ ደግሞ በመማር-ማሰተማር ሂደት የምንጠቀምባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ጠቀሜታ ፋይዳ ቢስ ይሆናል።

## 4. የመምህራን ግድየለሽነት

ትምህርቱን ያለትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በቃል ብቻ ማስተማር አሰልቺ፣ ጊዜን አባካኝ እና ውጤታማ ያልሆነ መሆኑን በግልፅ አምነው ሊቀበሉ ይገባል። በትምህርት መርጃ መሣሪያ አመራረጥና አጠቃቀም ረገድ ግድየለሽነት ካጠቃቸውና ሚናና ተግባራቸውን በአግባቡ ካልተወጡ የመማር-ማስተማር ሂደቱ ችግር ያጋጥመዋል።

## 5. የኤሌክትሪክ ኃይል ያለመኖር

አብዛኛዎቹ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እንደሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና ፕሮጀክተሮች ያለ ኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ሊሰጡ አይችሉም፡፡ የኤሌክትሪክ ስርጭት ደግሞ በገጠር ትምህርት ቤቶች እንደልብ የማይደርስበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ በዚህ መንገድ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም ችግር ሊከሰት ይችላል፡፡

## 6. የሥልጠና እጥረት

የማሠልጠኛ ኮሌጆች ወይም የትምህርት ሥልጠና ማዕከላት መምህራንንና የትምህርት ባለሙያዎችን በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ረገድ ተገቢ ክሂሎት እንዲጨብጡ የማድረግ ሚና ይጫወታሉ፡፡ እንደነዚህ ያሉ የትምህርት የሥልጠና ማዕከላትና የማሠልጠኛ ኮሌጆች በማይኖሩበት አካባቢ ባሉ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራንና የሚያገለግሉ የትምህርት ባለሙያዎች ሥልጠናውን የማግኘት አጋጣሚ ዝቅተኛ ይሆናል፤ ሥልጠና ባለማግኘታቸው ምክንያት በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቀቀም ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡

## 7. በአካባቢ በሚገኙ ቁሳቁስ የመጠቀም ፍላጎት ማነስ

በአነስተኛ ወጭ የአካባቢ ሀብትን በመጠቀም በመማር-ማስተማር ሂደት በመርጃ መሣሪያ የተሟላ የመማሪያ ክፍል ሊኖር ይገባል፡፡ ነገር ግን ባካባቢ በሚታዩ ማሕበረሰባዊ፣ ትምህርታዊና ሥነልቦናዊ ምክንያቶች የተነሳ በአካባቢ በሚገኙ ቁሳቁሶች የመጠቀም ሁኔታው ዝቅተኛ ነው፡፡ የእነዚህ ተፅዕኖዎችና ከአካባቢ የሚገኙ ነገሮችን ምንም ትምህርት እንደማይቀስምባቸው እንደዝቅተኛ ነገር መመልከት፣ ከፋብሪካ ተመርቶ ካልመጣ ወይም ውድ ከሆኑ ነገሮች ካልተዘጋጀ ጠቀሜታ ያለው ስለማይመስላቸው የመምህራንም ሆነ የተማሪዎች የስነትምህርታዊ አስተሳሰብ ችግር የአካባቢ ቁሳቁሶችን የመጠቀም አቅምን ዝቅተኛ ያደርጋል፡፡

## 8. ተማሪዎች ጉብኝት የሚያደርጉባቸው ቦታዎች (የትምህርት ማዕከላት) በበቂ ሁኔታ ያለመኖር

ተማሪዎች በመማር-ማስተማር ሂደት በትምህርት ቤት በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከሚቀርቡላቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ውጭ ትምህርታዊ ጉብኝት

የሚያካሂዱበት፣ የተደራጁ እና ደረጃቸውን የጠበቁ የፊልም ቤተሙከራዎች፣ የሚደመጥና የሚታይ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሙዚየም፣ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ዓውደ-ርዕዮች፣ የሥዕል ሙዚየም፣ የፎቶግራፍ ክምችት፣ ታሪካዊ መረጃዎች ወዘተ. በትምህርት ባለሙያዎች በተለያዩ ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች ሊዘጋጁና ለጉብኝት ሊቀርቡ ይገባል፡፡ የእነዚህ ዕጥረት ወይም ምቹነት አለመኖር በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

9. **የትምህርት መርጃ መሣሪያን በተገቢ ሁኔታ መምረጥ አለመቻል**

የታቀደውን የትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ የመማር-ማስተማር ክንውኑን ለማፋጠን የሚያግዙ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአግባቡ መምረጥ ካልተቻለ የተማሪዎችን ፍላጎት በመቀስቀስ የታለመውን የትምህርት ዓላማ ተግባራዊ ማድረግ ዓይቻልም፡፡ ስለዚህ በተገቢ ሁኔታ መርጦ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለመጠቀም በቅድሚያ የመማር-ማስተማር ሂደቱን ለማፋጠን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምን በሁለት መንገድ ከፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት ለተማሪዎች ግልፅ ለማድረግ የሚጠቀሙበት ሲሆን፤ ሁለተኛው ተማሪዎች በንቃት ለመሳተፍ እንዲችሉ ለማድረግ የሚገለገሉባቸው ናቸው፡፡ ከትምህርቱ ጎናዊና ተዋረዳዊ ዝምድና አንፃርም የወደፊቱን የመማር-ማስተማር ሁኔታ በማሰብ መጠቀም ቀዳሚ ተግባር ነው፡፡ ዛሬ ለማስተማር አገልግሎት ላይ የዋለው የትምህርት መርጃ መሣሪያ ለሚቀጥለውና በተከታታይ ለሚቀርበው ትምህርት መሠረት ሊሆን ይገባል፡፡ ለአንድ ጊዜ ብቻ ተጠቅመው ለሌላ ጊዜ እንደማያገለግል ቆጥረው በሥርዓት የማያስቀምጡ ከሆነ ከትምህርቱ ተለጣጣቂነት፣ ተከታታይነትና ተዛማጅነት አንፃር የሚሰጠው ፋይዳ አይኖርም፡፡

### 2.5.4 የሥልጠና ጉዳይ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ዙሪያ

ቀደም ሲል የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደት መገልገል ያለው ሥነትምህርታዊ ፋይዳ ተዳሷል፡፡ የላቀ ሥነትምህርታዊ ፋይዳ የሚኖረውም ከተቀረፀው ዓላማና ዓላማውን ለማስፈፀም ከቀረበው የትምህርት ይዘት ጋር የሚጣጣሙ የትምህርት መርጃ

መሣሪያዎች በጥንቃቄ በመምረጥና በአግባቡ መጠቀም ሲቻል እንደሆነ ተዳሷል፡፡ ቀጣዩ ሥራ የተነደፈውን የትምህርት ዓላማ ከግቡ ለማድረስ የሚያስችሉ ተገቢ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን መርጦ የመጠቀም ክህሎት እንዴት ይገኛል? የሚል ይሆናል፡፡ የጥያቄው ምላሽም "በሥልጠና" እንደሚሆን አያጠራጥርም፡፡ Newby et al. (1996:263) ይህን አስመልክተው መምህራን ወደሥራ ዓለም ከመሠማራታቸው በፊት ወይም በሥራ ላይ እያሉ ሥልጠና በመስጠት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥና አጠቃቀም ክህሎት ማስጨበጥ እንደሚቻል ይገልፃሉ፡፡ እነዚህ ምሁራን አያይዘውም ሥልጠና ብቻውን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአግባቡ መርጦ የሚጠቀም ሊቅ አያፈራም ይላሉ፡፡ ከዚህ ይልቅ መምህራን በሥልጠና ወቅት ያገኙትን መንደርደርያ ሐሳብ መነሻ በማድረግ በተግባር በመማር-ማስተማር ክፍል ውስጥ የተረጎሙት እንደሆነ ከራሳቸው ጋር የተዋሃደ፣ በዕለተ ተዕለት ህይወታቸው የሚጠቀሙበት ዘላቂነት ያለው ክህሎት እንደሚያጎናፅፋቸው ይገልፃሉ፡፡

ከዚህ አንፃር Newby et al. (1996፡22) እንደሚሉት በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዙሪያ የሚሰጡ ሥልጠናዎች በንድፈ ሐሳባዊ ትንታኔ ላይ በቻ ከሚያተኩሩ ከተግባራዊ ክንዋኔዎች ጋር ተዋሕደው ቢቀርቡ የተሻለ ውጤት ይኖራቸዋል፡፡ በተለይ በዓውደ ጥናቶች /workshops/ እና በመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የሚሰጡ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም ሥልጠናዎች በተግባራዊ ልምምድ ላይ ትኩረት የሰጡ ቢሆኑ ይመረጣል፡፡ Betsate (2000:73)፣ Melvin and Dennis (1973)ን ጠቅሰው ተግባራዊ ሥልጠና የሚያስገኘው አመርቂ-ውጤት በጥናት የተደገፈ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ እኒህ ምሁር በማስረጃነት ያቀረቡት ጥናት በኦውበርን ዩኒቨርሲቲ በተከታታይ ከሁለት ዓመታት በላይ ጥናት ተካሂዶ ነበር፡፡ ዓላማውም ለሠልጣኝ መምህራን ውጤታማ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥና አጠቃቀም ላይ ተግባራዊ የሚሆን የማስተማሪያ ስልት በመለየት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ የጥናቱ ውጤትም ሠልጣኞቹ በገለፃና በውይይት ከሚሰጥ ትምህርት ይልቅ በኑባራዊ ተግባራዊ ልምምድ (authentic practice experiences) ይበልጥ እንደሚሳተፉ፣ በንቃት እንደሚከታተሉና እንደሚተገብሩ ይገልፃል፡፡ በመሆኑም እኒህ ምሁር እንደሚያብራሩት፣ ሠልጣኞች በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ ጥናታዊ ጽሑፎችን እንዲፅፉ፣ የፕሮጀክት ሥራ ሠርተው ስለጥናቱ በዘገባ መልክ እንዲፅፉ፣ በውነተኛ የመማሪያ ክፍል ውስጥ በተግባር እንዲለማመዱ፣

የትምህርት መርጃ ማዕከላትን እንዲጎበኙ፣ የቢጤ የማስተማር ልምምድ እንዲያደርጉ ወይም በሕፃናት የመማርያ ክፍል ገብተው እንዲሞክሩ በማድረግ ንድፈ ሐሳብን ከተግባር ጋር ያካተተ ሥልጠና መስጠት ውጤታማ እንደሆነ በአፅንኦት ይገልፃሉ፡፡ በዚህ ሐሳብ Newby et al. (1996፡263)፣ “በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሥልጠና ወቅት ሠልጣኝ መምህራን በእጃቸው እየነካኩና እየተለማመዱ ቢሠለጥኑ ውጤታማ ይሆናሉ፡፡” ይላሉ፡፡ አክለውም “ሰዎች ብስክሌት መንዳት የሚችሉት በነፃ በቀረበላቸው ንድፈ ሐሳባዊ ትንታኔ ወይም ከመጻሕፍት ካነበቡት ሳይሆን በተግባር ከብስክሌቱ ጋር አካላዊ ሰውነታቸውን በማገናኘትና በማለማመድ ነው” ብለው ካሠፈሩ በኋላ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥና አጠቃቀም ክህሎትም በተግባራዊ ልምምድ እንደሚገኝ ያስገነዝባሉ፡፡

በአንፃሩ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዙሪያ የሚሰጡ ሥልጠናዎች ችግሮች እንደማይታጡባቸው መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ Nacino-Brown, et al. (1982:73) እንደሚሉት፣ ከመምህራን ማሠልጠኛ ተቋማት ሠልጥነው ከሚወጡ መምህራን ውስጥ በርካታዎቹ በመማርያ ክፍል ውስጥ የታቀደውን ዓላማ ለማስፈፀም የሚያስችሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የመምረጥና የመጠቀም ክህሎት ሳይኖራቸው ነው፡፡ ምሁሩ እንደሚጠቁሙት፣ ለዚህ ችግር መፍትሔው ለሠልጣኞች ትግበራን መሠረት ያደረገ ሥልጠና መስጠት ነው፡፡ Tucker (1979:21) እንደዚሁ በመምህራን ማሠልጠኛ ተቋማት የሚሰጡ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሥልጠናዎች (የአሜሪካን የትምህርት ኮሌጆች መሠረት አድርገው) በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዙሪያ የሚያጠፉት ጊዜ እጅግ በጣም አነስተኛ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ Kieffer and Lee (1974:66) ስለትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚሰጠው ሥልጠና ትኩረት የተነፈገውና በንድፈ፣ ሐሳብ ላይ ብቻ የተመሠረተ መሆኑን ሲገልፁ “ስለሚደመጡና የሚታዩ ኮርሶች ያየነውና የሰማነው ኮርሶቹ ያለሚደመጡና የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሲሰጡ ነው” ይላሉ፡፡

በመምህራንና ማሠልጠኛ ተቋማት በሚሰጡ ሥልጠናዎች በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ትኩረት ዙሪያ የሚከሰቱ ችግሮች መፍትሔ አላቸው፡፡ Kieffer and Lee (1974:66) እንደሚሉት፣ ሠልጣኝ መምህራንን ስለትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥና አጠቃቀም አሠልጣኝ መምህራን በሚያስተምሩበት ጊዜ መርጃ መሣሪያዎችን ወደመማሪያ ክፍል በማምጣት ራሳቸው በመምረጥና በመጠቀም በተግባር ማሳየት፣ ሠልጣኞችም እንዲመርጡና እንዲለማመዱ

(እንዲጠቀሙ) በማድረግ ችግሩን መቅረፍ እንደሚቻል ይገልፃሉ። እነዚህ ምሁራን አክለው በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዙሪያ በሚሰጥ ሥልጠና ላይ ደረቅ እውነታ፣ ጥሬ መረጃ (raw data) ብቻ የሠልጣኞችን አዕምሮ ያለ ተገቢ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥና አጠቃቀም ዕውቀት ለመሙላት ለተጨባጭነትና ለምክንያታዊነት ምንም ፋይዳ እንደሌለው ያብራራሉ። ከዚህም ሌላ ምሁሩ መምህራን በተግባር ሲያሳዩ፣ ሠልጣኞችም ሲለማመዱ ከተማሪ-ተኮር ዘዴ ጋር አያይዘው መከወን እንደሚገባቸው ያሳስባሉ። Ashby and Besse (1972:3) ይህን አስመልክቶ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በተግባራዊ ተሳትፎ ማቅረብና በተማሪ-ተኮር ዘዴ መጠቀም ለአሠልጣኙም ሆነ ለሠልጣኞች ጠቃሚ እንደሆነ ይገልፃሉ። ለአሠልጣኝ መምህራን ስለትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚሠጠው ትምህርት የተሳካ እንዲሆን ሲያግዝ ለሠልጣኞችም ከሥልጠና በኋላ ለሚሰማሩበት የማስተማር ሥራቸው ተግባራዊና አሳታፊ የሆነ ዘዴን እንዲጠቀሙና በመርጃ መሣሪያ እያስደገፉ ትምህርት እንዲሰጡ ያስችላቸዋል።

ከዚህ ሌላ መምህራን ከወቅታዊ የመርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምና የማስተማር ዘዴ ጋር የሚያስተዋውቅ የሥራ ላይ ሥልጠና ያስፈልጋቸዋል (Newby et al. 1996፣259)። ይህም በቅድመ ሥራ ላይ ሥልጠና በጥልቀት ያልታየ በንድፈ ሐሳብ ብቻ ገረፍ ገረፍ ተደርጎ የታለፈን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ዕውቀትና ክህሎት ለመከለስ እድል ይሰጣቸዋል።

የሥልጠናው ሂደት በማን ይከናወን? ሲባል ደግሞ ከውጭ አገር አማካሪዎችና አሠልጣኞች ይልቅ የአካባቢ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ባለሙያዎች እና በዚያ ሙያ የተካኑ የትምህርት ቤት መምህራን ሥልጠናውን ቢሰጡ ይመረጣል (Newby et al. 1996:263)። ምክንያቱም እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች የትምህርትቤቱንና የመማሪያ ክፍሉን ተጨባጭ ሁኔታ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ እንደሆነ (Newby et al. 1996:263) ይገልፃሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ (I.C.D.R. 1988:3) ልምድ ያላቸው መምህራንና የትምህርት መርጃ መሣሪያ ባለሙያዎች በተለይ በገጠር ትምህርት ቤቶች መምህራን የሥራ ላይ ሥልጠና ለመውሰድ ችግር የሚገጥማቸው መሆኑን ጠቁመው፣ ትምህርት ቤቱና አሠልጣኞቹ ከመምህራን ጋር በጋራ በመሆን አመቺ ጊዜና ቦታ በመምረጥ የሥልጠና የጊዜ ሰሌዳ ሊያዘጋጁና በየጊዜው ስልጠናውን ሊወስዱ እንደሚችሉ Newby et al. (1996:263) አክለው ይገልፃሉ።

## 2.6 የቋንቋ ትምህርትን በትምህርት መርጃ መሣሪያ ለማስተማር የመምህራን ተግባር

በቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደት የታቀደውን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ መምህራን ትምህርቱን ግልፅ፣ ቀላልና ተጨባጭ ለማድረግ በትምህርት መርጃ መሣሪያ መጠቀም በማስተማር በኩል ወሳኝ ሚና አላቸው፤ መምህራን በተለያዩ የመማር-ማስተማር ስልቶች ተጠቅመው ተማሪዎችን በታላሚው ቋንቋ እንዲገለገሉ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ መምህራን ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ለመወጣት የመማር ማስተማር ሂደቱን የተሳካ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ Gower et al. (1983:154) ይህን ሐሳብ እንዲህ በማለት ይገልጹታል፤ የመማር ሁኔታውን ተቆጣጥረው በተማሪዎች ዘንድ መስተጋብር እንዲኖር ማድረግ የመምህራን ተግባር ነው፡፡ ተማሪዎች በቋንቋው የመግባባት ሂደትን እንዲማሩ በክፍል ውስጥ መስተጋብርን ይሻሉ፤ የመምህራን ተግባርም የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በመጠቀም ለተማሪዎች የጥንድና የቡድን ሥራዎችን መስጠት፣ መቆጣጠር፣ ማማከርና መገምገምነው፡፡

Burns et al. (1999:337) ተማሪዎችን ማበረታታትና ለመማር-ማስተማር ምቹ የሆኑ የክፍል ውስጥ ሁኔታን መፍጠር እንዳለባቸው በመግለፅ በጣም ጠቃሚ ከሆኑ የመምህራን ኃላፊነቶች አንዱ የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያን መጠቀም እንደሆነ ያስረዳሉ፤ ጥሩ መምህራን ይህንን እውን በማድረግ የቋንቋውን ትምህርት ኑባራዊነት ባለው ሁኔታ ያቀርባሉ (Burns et al. 1999:536)፡፡

በክፍል ውስጥ ተማሪዎች እርስ በርስ በመወያየት ሐሳብ እንዲለዋወጡ መምህራን በተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም አለባቸው፡፡ Hittleman (1988:69-70) መምህራን ከክፍል ክንውኖች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የሕትመት ውጤቶች (የተለያዩ መጻሕፍት፣ መጽሔት፣ ጋዜጣ) እና ታሪኮች፤ ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ ማንበብ፣ የክፍል ውይይት ማድረግ፣ ንባብን ወይም ንግግርን መምራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህም የቋንቋውን ትምህርት ዓላማ ግብ እንዲመታ ለማድረግ የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው ገልፀው፤ የመምህሩ ትልቅ ኃላፊነት በተግባር ሊተረጎም የሚገባው መሆኑን ያብራራሉ፡፡

ባአጠቃላይ መምህራን የክፍሉን ሁኔታ በመቆጣጠር የትምህርት መርጃ መሣሪያን በመጠቀም ጥሩ የመማር-ማስተማር ሂደት ከፈጠሩ፣ ተማሪዎች በሚገባ ቋንቋን ለተግባቦታዊ ዓላማ ያውሉታል፡፡ ተማሪዎች በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ታግዘው ፍላጎታቸው ከተነሣሣ በተለያዩ የጥንድና የቡድን ክንውኖች ሲሳተፉ ተፈጥሮአዊ የሆነውን ቋንቋ ይገለገላሉ ማለት ነው፡፡ በዚህ ስልት የታላሚውን ቋንቋ ትምህርት ዓላማ ግልፅ፣ ቀላልና ተጨባጭ በሆነ መንገድ እንዲጠቀሙበት በር ይከፍታል፤ የመምህራንም ትልቁ ተግባራና ኃላፊነት ይህ ነው፡፡

## 2.7 የማስተማሪያ መሣሪያዎች በመርጃ መሣሪያዎች ለመጠቀም ያላቸው እገዛ

የቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መሣሪያዎች የምንላቸው በዚህ ጥናት መርሐ ትምህርትን፣ የተማሪን መጽሐፍ፣ የመምህሩ መምሪያን ብቻ ያጠቃልሉ ናቸው፡፡ የቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መሣሪያዎች የቋንቋ ትምህርት ሂደትን የተሳካ ለማድረግ የሚመሩ የትምህርት መሣሪያዎች ናቸው፡፡ Nunan (1988:105) የትምህርት መሣርያዎች በቋንቋ ትምህርት ክፍልና በእውኑ ዓለም ያለውን ግንኙነት ግልፅ የሚያደርጉ እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡ እነዚህ መሣሪያዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ የተለያዩ ቁም ነገሮችን ከግምት ውስጥ የሚያስገቡ ቢሆንም እዚህ ላይ ለማየት የተፈለገው ለትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚሰጡትን ትኩረትና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ለማስተማር በትምህርት መርጃ መሣሪያ ለመጠቀም ያላቸውን እገዛ ነው፡፡ ቀጥሎ የተማሪው መጽሐፍ፣ የመምህሩ መምሪያና መርሐ ትምህርቱን ለማየት ይሞከራል፣

### 2.7.1 የተማሪ መጽሐፍና የመምህሩ መምሪያ

Harmer (2001:257)፣ Sheldon (1987:238)፣ Richards and Rogers (1986:25) የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት የቋንቋ መማር ማስተማርን የሚመሩ፣ የቋንቋ ትምህርቱን መነሻና መድረሻውን የሚጠቁሙ፣ የተለያዩ ይዘቶችን በምሳሌ አስደግፈው የሚያቀርቡ መልመጃዎችንና የተለያዩ ተግባራትን በማቅረብ ተማሪዎችን እንዲለማመዱ የሚያደርጉ፣ በአጠቃላይ መሠረታዊ እውቀትንና የተለያዩ ጽንሰ ሐሳቦችን ለተማሪው የሚያስጨብጡ፣ ለመምህሩም ሥራ አጠቃላይ መማር-ማስተማር ሂደት እንቅስቃሴ መረጃ የሚሰጡ በመሆናቸው በጥንቃቄ ሊዘጋጁ እንደሚገባቸው ያስገነዝባሉ፡፡

በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ባለሙያዎች የመማሪያና ማስተማሪያ መጻሕፍቱ በሚዘጋጁበት ጊዜ የቋንቋን ትምህርት በትምህርት መርጃ መሣሪያ አስደግፎ በማስተማር ተማሪውን በተለያዩ

ተግባራት እንዲሳተፍ ትምህርቱን ቀላል፣ ግልጽና ተጨባጭ እንዲሆን የሚያደርጉ መሆናቸውን በመግለፅ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባ መሆኑን ያብራራሉ፡፡

### 2.7.2 መርሐ ትምህርት

መርሐ ትምህርትና ሥርዓተ ትምህርት በአንዳንድ ሀገራት አንዱ አንዱን እየተካ የሚያገለግልበት ሁኔታ ይታያል፡፡ በዚህ ጥናት ግን የሚከተለውን ሀሳብ የያዘ ብያኔ ተቀባይነት አለው፡፡ መርሐ-ትምህርት ከሥርዓተ-ትምህርት በጠበበ መልኩ የአንድ የትምህርት ዓይነት ይዘቶችን ለማዋቀር በመነሻነት የሚያግዝ፣ የትምህርቱን አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች የሚያሳይ፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችን እና ትምህርቱ የሚቀርብበትን የጊዜ ገደብ የሚያመላክት እንዲሁም የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችንና የግምገማ ስልቶችን የሚጠቁም ሰነድ ነው (Cunningworth 1989:22, Ur 1996:176, Hutchinson and Waters 1987:65)፡፡

Widdowosen (1990:129) መርሐ ትምህርት ለመምህራን እንደመምሪያ እንደሚያገለግላቸው የተለያዩ ሥነዘዴዎችን በማሳየት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በመጠቆም የመማር-ማስተማር ሂደቱን እንዴት እንደሚተገብሩ፣ ለመምህራን መሪ የትምህርት መሣሪያ ሆኖ እንደሚያገለግል ያስረዳሉ፡፡

Yalden (1987፡81)፣ Dubin and Olshtain (1986፡79)፣ Nunan (1988፡43) እንደሚሉት መርሐ ትምህርት ተማሪው ምን መማር ይገባዋል? ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚሰጥ፣ የሃገሪቱን አጠቃላይ የትምህርት ፍልስፍናና የቋንቋ ትምህርት ፖሊሲ መነሻ አድርጎ መምህሩ ማስተማር የሚገባውን፣ ተማሪው መማር ያለበትን የሚገልፅ መሠረታዊ የቋንቋ ትምህርት ሰነድ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር መርሐ ትምህርት የአንድን ሀገር የቋንቋ ትምህርት ፖሊሲ ስለሚያንፀባርቅ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አደራጆች የመማሪያ መሣሪያ አዘጋጆች፣ መምህራን፣ ፈተና ክፍሎች በአጠቃላይ የሚመለከታቸው አካላት የሀገሪቱን የቋንቋ ትምህርት ፖሊሲ ተመርኩዘው ለማዘጋጀት አስፈላጊውን መረጃ የሚያገኙት ከመርሐ ትምህርቱ ነው፡፡

## 2.8 የቀደምት ተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

የዚህ ጥናት አቅራቢ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶችን ለማየት ባደረገችው ፍተሻ አራት የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፎችን አግኝታለች፡፡ አንዱ በጌታቸው ለገሰ (1992)፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል አማርኛን በማስተማር ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ "በአዲስ አበባ መስተዳድር ለ7ኛ ክፍል የሚተላለፈው አጋዥ የአማርኛ

ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የቋንቋውን ትምህርት ጥራት ለማሻሻል ሊያበረክተው የሚችለው አስተዋፅኦ" በሚል ርዕስ ጥናቱን አካሂዷል፡፡ ጥናቱ የመርጃ መሣሪያ ዓይነት በሆነው በሚደመጡ መሣሪያ በሬዲዮ ላይ የተጠና ሲሆን፣ ይህ ጥናት ግን በአጠቃላይ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የመምህራን አጠቃቀም ላይ የሚያተኩር በመሆኑ በዓላማው፣ በጥናቱ አካባቢ እና በክፍል ደረጃው ይለያል፡፡

በዚህ ርዕስ ቀጣይ ሆኖ የሚገኘው በAbebe Zewdie (1997) በትምህርት ፋኩልቲ በካሪኩለምና ኢንስትራክሽን ትምህርት ሥልጠናና በሥራ ላይ ሥልጠና በወሰዱ መምህራን መካከል ባለው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥና አጠቀቀም የንፅፅር ጥናት ነው፡፡ ይህ ጥናት ግን የሚያተኩረው አሁን በሥራ ላይ ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን በመሆኑ በዓላማው በጥናቱ አካባቢና በትምህርት ዓይነቱ በክፍል ደረጃው ይለያል፡፡

ተከታዩ ጥናት ደግሞ በBetsate (2000) በትምህርት ፋኩልቲ በካሪኩለምና ኢንስትራክሽን ትምህርት መስክ "Application of instructional materials in pre-primary school of SNNPR" በሚል ርዕስ የተጠና ሲሆን ይህ ጥናት ግን የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም የሚመለከት በመሆኑ በዓላማው፣ በጥናቱ አካባቢ እና በትምህርት ዓይነቱ ይለያል፡፡

ተከታዩ ጥናት ደግሞ በጌታቸው ኮቼ፣ (2000)፣ በኢትዮጵያ ቋንቋቸውና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል "በቦንጋ ከተማ አምስት የመጀመሪያ ደረጃ እርከን ትምህርት ቤቶች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በማስተማር ሂደት የቋንቋ ትምህርት መሣሪያዎች እና የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም" በሚል ርዕስ የተጠና ጥናት ሲሆን ጥናቱ የሚያተኩረው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በማስተማር ሂደት መሆኑና የትምህርት መሣሪያዎችን መርጃ መሣሪያዎችን አዘገጃጀት መጨመሩ ከዚህ ጥናት ይለየዋል፤ ምክንያቱም ይህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን ብቻ የሚመለከት በመሆኑ በጥናት አካባቢ በትምህርት ዕርከኑና አማርኛን እንደአንደኛ ቋንቋ (የአፍ መፍቻ ቋንቋ) ለሚጠቀሙ በመሆኑ ይለያል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የጥናቱ አጠናን ዘዴና የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

የዚህ ጥናት ትኩረት በጎንደር ከተማ አስተዳደር የሚገኙ የሰባተኛና የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምን መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱ የተከተለው የአጠናን ዘዴም ዐይነታዊ የምርምር ዘዴ ክፍል የሆነው ገላጭ ምርምርን ነው፡፡ በዋናነት በስራ ላይ የዋለው የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ምልከታ ሲሆን፣ የጥናቱን ተጨባጭነት የበለጠ ለማጉላት ከመምህራን በጽሑፍና በቃል መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ የጥናቱን ውጤት ይበልጥ ለማጠናከርም ምልከታው በቪዲዮ ካሜራ ተደግፏል፡፡ የእያንዳንዱ የጥናቱ የአከዋወን ስልት የሚከተለውን ይመስላል፤

### 3.1 የአጠናን ዘዴ

#### 3.1.1 የጥናቱ ክልል የናሙና አመራረጥ

- ለጥናቱ የተመረጠው ጎንደር ከተማ አስተዳደር ነው፡፡ ጎንደር ከተማ አስተደዳር የተመረጠበት በአመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴ በመጠቀም ነው፡፡ በአመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴ በመጠቀም ጎንደር ከተማ አስተዳደር የተመረጠበት ምክንያት፣
  - አጥኝዋ ቀደም ሲል ትሠራበት የነበረ አካባቢ በመሆኑ ጥናቱን በተቃና መንገድ ለማካሄድ የሚያስፈልገውን መረጃ በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችል ሆኖ በመገኘቱ፣
  - ጥናቱን ለማካሄድ ትምህርት ቤቶቹ አንፃራዊ በሆነ መንገድ በተቀራራቢ ርቀት ላይ በመገኘታቸው፡፡

#### 3.1.2 የትምህርት ቤት የናሙና አመራረጥ

ምንም እንኳን በጎንደር ከተማ አስተዳደር ውስጥ የመንግሥትና የመንግሥት ያልሆኑ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቢገኙም ይህ ጥናት የተካሄደው በመንግሥት 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ነው፡፡ 2001 ዓ.ም. በጎንደር ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽሕፈት ቤት በተገኘው መረጃ መሠረት በጎንደር ከተማ አስተዳደር ውስጥ አሥራ አንድ የመንግሥት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሉ፡፡ ከነዚህ ትምህርት ቤቶች መካከል አራቱ በነሲብ የዕጣ ናሙና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡

ይህም የናሙና መረጣ ዘዴ በከተማ መስተዳድሩ ለሚገኙ የመንግሥት 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እኩል እድል ይሰጣል ተብሎ ስለተገመተ ነው፡፡

አመራረጡም የትምህርት ቤቶቹ ስም የተጻፈባቸውን፣ በእኩል መጠን የተቆራረጡና በተመሳሳይ ሁኔታ የተጠቀለሉ ወረቀቶችን አዘጋጅቶ በነብስወከፍ እጣ በማስወጣት የመጀመሪያዎቹን አራት ባለ ዕጣዎች በመውሰድ ተከናውኗል፡፡

በዚህም ስልት የተመረጡት 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፤

- ፈለገ አብዮት 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣
- መሠረት 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣
- በካፋ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ እና
- ኅብረት 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣

ናቸው፡፡

### 3.1.3 የክፍል ደረጃ የናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ውስጥ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ ከ5ኛ-8ኛ ክፍል በጣም በርካታ በመሆናቸው በሁለት ክፍል ደረጃ ላይ ለመሥራት በነሲብ የናሙና ዘዴ አራት ዕጣዎች አምስተኛ፣ ስድስተኛ፣ ሰባተኛና ስምንተኛ ክፍሎች በሚል እኩል በሆኑ ወረቀቶች ላይ ተጽፎ ተጠቅሎ ነሲብ ናሙና በተከተለ ዘዴ ሰባተኛና ስምንተኛ ክፍሎች ተመርጠዋል፡፡

### 3.1.4 የመምህራን የናሙና አመራረጥ

በተመረጡት አራት ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የሰባተኛና የስምንተኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስምንት ሲሆኑ ሁሉም በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል፡፡ በዚህም መሠረት መምህራኑ የግኝት ናሙና ዘዴን በመከተል ተመርጠዋል፡፡

## 3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለዚህ ጥናት ተገቢ ናቸው ተብለው የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ዋና መሣሪያው ምልከታ ሲሆን በአጋዥነት የጽሑፍና የቃል መጠይቆች ናቸው፡፡ የጥናቱ ትኩረት

የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቀቀም በመሆኑ፣ የሚሰበሰቡት መረጃዎች በሦስት ማዕዘናዊ ዘዴ እውነታውን ለማረጋገጥ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰያ መሣሪያዎች መጠቀም አስፈላጊ ሆኗል፡፡ በዚህም መሠረት የሚከተሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

### 3.2.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ

ጥናቱ በዋናነት መሠረት ያደረገው ምልከታን ነው፡፡ በዚህ የመረጃ ማግኛ ስልት በመጠቀም በክፍል ውስጥ በስምንቱም መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምን ለመፈተሽ ጥረት ተደርጓል፡፡ በምልከታውም ወቅት ተጨባጭነት ያላቸው አስተያየቶችና ዳኝነቶችን ለመስጠት፣ የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችሉ ጠቃሚ መረጃዎችን ለመሰበሰብ፣ የDay (1990)ን ሐሳብ መሠረት በማድረግ ለጥናቱ በሚመች መልኩ ተሻሽለው "እጅግ በጣም ጥሩ"፣ "በጣም ጥሩ"፣ "ጥሩ"፣ "በቂ" እና "አነስተኛ" የሚሉ የተደራጁ መስፈርቶች ተዘጋጅተዋል፡፡ የመከታተያ ቅፅ በአማካሪዬና በአንድ የአማርኛ ቋንቋ የማስተማር ሥነዘዴ መምህር ታይቶ መጠነኛ ማስተካከያ ከተሰጠበት በኋላ በሙከራ ጥናት /Pilot study/ ተፈተሾና የማሻሻል ሥራ ተደርጎበት በሥራ ላይ ውሏል፤ ምልከታው በእያንዳንዱ ተጠኚ መምህራን ላይ ለሦስት ሦስት ክፍለ ጊዜያት ተካሂዷል፡፡ ምልከታው በቪዲዮ ካሜራ እንዲደገፍ ተደርጓል፡፡ በቪዲዮ ካሜራ እንዲደገፍ የተደረገበት አንዳንድ ጥቃቅን የተዘለሉ ነገሮች እንዳሉ ደጋግሞ ለማዬት፣ ለማስተካከል ስለሚረዳ ነው፡፡ መምህራኑም ሆነ ተማሪዎቹ የካሜራ ባለሙያው ክፍል ውስጥ በመገኘቱ ምክንያት ከተለመደው ተግባር የተለየ ክንዋኔ እንዳያሳዩ ለማድረግ ለመጀመሪያዎቹ አንድ አንድ ቀናት የማስመሰል ቀረፃ ተካሂዷል፡፡ በሚቀጥሉት ቀናት እውነተኛ ቀረፃ ተከናውኗል፡፡ በዚህ ጊዜም መምህራኑም ሆነ ተማሪዎቹ በተደጋጋሚ ስለተቀረጹ በየትኛው ጊዜ እውነተኛ ቀረፃ እንደተደረገ ስለማያውቁ መረጃዎቹን አስተማማኝ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ ከክፍል ምልከታው የሚገኘውን መረጃ አስተማማኝነት ከፍ ለማድረግ እና የግል አስተያየትን ለመቀነስ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተመቻችተዋል፡፡

ረዳት የክፍል ምልከታ አድራጊዎች ጋር የመማር-ማስተማሩን ሂደት ለመከታተል ተሞክሯል፡፡ ረዳቶቹም በማስተማር ሥነ ዘዴ የተመረቁ የጎንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ መምህራን

በመሆናቸው በክፍል ምልከታው የሚገኘውን መረጃ አስተማማኝ ከማድረጉም በላይ በአንዳንድ ነጥቦች ልዩነት ሲታይ በውውይት ከ90% በላይ ስምምነት ላይ በመደረሱ (Best and Kahn 2003:225) የሚገኘውን መረጃ ልዩነት ለማጥበብ ተሞክሯል፡፡

### 3.2.2 የቃል መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ ማካሄድ በተዘዋዋሪ መንገድ በምልከታ የተገኙትን መረጃዎች አስተማማኝነት ለማረጋገጥ አጋዥ እንደሚሆን ታምኖበታል፡፡ በዚህ ስልት ጥያቄዎቹ የቀረቡት በያለው (2006፡86) ሞዴልነት ተዘጋጅቶ በጥናቱ አማካሪ ከተረጋገጠ በኋላ ጥናቱ በተካሄደባቸው አራት ትምህርት ቤቶች ከስምንት ተተኳሪ መምህራን ጋር የተደረገ ነው፡፡ መረጃውን (ምላሹን) በመቅረፀ ድምፅ በመቅዳት ወደ ጽሑፍ ተመልሶ በአባሪነት ተያይዟል፡፡ (አባሪ "መ" ገጽ 95ን ይመልከቱ)፡፡

### 3.2.3 የጽሑፍ መጠይቅ

የጽሑፍ መጠይቅ የተዘጋጀው በተጠኝ ትምህርት ቤቶች በተመረጡ በሰባተኛ እና በስምንተኛ ክፍሎች ደረጃ በሚያስተምሩ መምህራን ተተኳሪነት ነው፡፡ የመጠይቁ መሠረታዊ ዓላማ በምልከታ የሚሰበስበውን መረጃ ከተጠኝዎች በሚገኘው መረጃ ለማጠናከርና መረጃውን አስተማማኝ ለማድረግ ነው፡፡ የጽሑፍ መጠይቁ የመጠይቅን ቅርፅ /format/ እንዲይዝ ተደርጓል፡፡ ጥያቄዎቹም በጥናቱ አማካሪ አስፈላጊው ማስተካከያ ተደረጎባቸዋል፡፡ የጽሑፍ መጠይቁም አዘገጃጀት ያለው (2006)ን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ መጠይቁ የተዘጋጀው ከመግቢያው ውጭ በሁለት ክፍሎች ተለይቶ ነው፡፡ በመግቢያው ላይ የጽሑፍ መጠይቁ የተዘጋጀበት ዓላማና ከመጠይቁ ስለሚገኙ መረጃዎች ፋይዳ የተገለጹበትና ተጠኚዎቹ ስለመጠይቁም ሆነ ስለሚሰጡት መረጃ ጥርጣሬ እንዳያድርባቸው ማሳሰቢያ የተሰጠበት ነው፡፡ የመጠይቁ የመጀመሪያው ክፍል ስለተጠኚዎች አጠቃላይ የሆኑ ዳራዊ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የታለሙ ይዘቶችን አካቷል፡፡ ሁለተኛው ክፍል የጥናቱን ዓላማ መሠረት ያደረጉ በመማር-ማስተማር ሂደቱ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን የሚመለከቱ አማራጭ መልሶች ያሏቸው ጥያቄዎችና የጥያቄዎችን አመላለስ የሚመሩ መመሪያዎች የቀረቡበት ነው፤ በተጨማሪም በዚህ ሥር ክፍት ጥያቄዎች ይገኛሉ፡፡

የጽሑፍ መጠይቁን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ የሙከራ ጥናት (Pilot study) ተካሂዷል፡፡ ከሙከራው የተገኘው ምጋቤ ምላሽ ማሻሻያ ተደርጎበት በአንድ ሥነዘዴ መምህርና በሁለት የማስተማር ሥነ ዘዴ የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች ተገምግሞ አስተማማኝነቱ ተረጋግጧል፡፡ በመጨረሻም የተዘጋጀው የጽሑፍ መጠይቅ ለስምንቱም መምህራን የክፍል ምልከታ ከተጠናቀቀ በኋላ ተበትኖ በሁሉም ተሞልቶ መመለሱ ተረጋግጧል፡፡

## 3.3 የመረጃዎች የአተናተን ስልት

በዚህ ጥናት ውስጥ በተመረጡ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍሎች ውስጥ የተካሄዱትን የምልከታ ውጤቶች በአጋዥነት ከተሰበሰቡት የጹሑፍ መጠይቅና የቃል መጠይቅ ውጤቶች በመነሣት በንዑስ ክፍል 1.2 ለቀረቡት የጥናቱ ዓላማ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ትንተና ተደርጓል፡፡ ትንተናውም መረጃዎቹ በሚያነሱት ጉዳይ መሠረት ተከፍሎ በሠንጠረዥ ውስጥ በቁጥርና በመቶኛ ስሌት (%) ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የጥናቱ ውጤት ትንተና እና ማብራሪያ

ከጥናቱ ታላሚ ትምህርት ቤቶች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ከፍ ሲል በምዕራፍ ሦስት በተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች አማካኝነት የተሰበሰቡትን እነዚህን መረጃዎች እንደሚከተለው በሦስት ክፍሎች በመመደብ ለመተንተን ተሞክሯል፤

- የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም፣
- የመምህራን ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለመጠቀም የቋንቋ ማስተማሪያ መሣሪያዎች እገዛ፣ እና
- የመምህራንን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ብቃት፣

የሚወሰኑ ተላውጦዎች፡፡

## 4.1 የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም

መምህራን በዕለት ተዕለት የመማር-ማስተማር ሂደት ወቅት የሁሉንም ተማሪ ፍላጎት የሚያሟሉ ከሚያስተምሩት ከዕለቱ ትምህርት ጋር ቀጥተኛ ተዛማጅነት ባላቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በክፍል ውስጥ ዘወትር ይጠቀሙ (አይጠቀሙ) እንደሆነ ለመግለፅ በተወሰኑ በሦስት እና በአራት ክፍለ ጊዜያት የክፍል ውስጥ ምልከታ ብቻ የተሟላ መረጃ ተገኝቷል ለማለት አያስደፍርም፡፡ ምክንያቱም በዓመት ወይም በመንፈቀ ዓመት ከሚማሩት ክፍለ ጊዜያት ቢያንስ 30% ያህል ምልከታ መካሄድ እንዳለበት Day (1990:42) ይገልጻሉ፡፡ ሆኖም ግን የመምህራንን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምን በተመለከተ ተጨባጭ መረጃ ለማግኘት ከክፍል ምልከታ የተሻለ አማራጭ ባለመኖሩ በአራቱም ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ ታላሚ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሲያስተምሩ በክፍል ውስጥ በመገኘት እያንዳንዳቸውን ለሦስት ሦስት ክፍለ ጊዜያት ለመመልከት ችላለች፡፡ በተጨማሪም ከላይ የተጠቀሰውን የመረጃ ተዓማኒነት ሥጋት ለመቀነስ እንዲረዳ በማሰብ የመምህራንን የመንፈቀ ዓመቱን የዕለት ትምህርት ዕቅድ በመመልከት በመንፈቀ ዓመቱ ላይ የተጠቀሱት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ከዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ጋር መጣጣምና አለመጣጣሙን ለማገናዘብ ሞክራለች፡፡

ከላይ እንደተገለጸው በአጠቃላይ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት ጊዜ ምልከታ የተደረገባቸው ሃያ አራት ክፍለ ጊዜያት ናቸው። ለ7ኛ ክፍል አራት ምድቦች (Sections) አስራ ሁለት ክፍለ ጊዜያት የክፍል ውስጥ ምልከታ ሲደረግ፣ ለ8ኛ ክፍል አራት ምድቦችም እንደዚህ አስራ ሁለት ክፍል ጊዜያት ምልከታ ተካሂዷል። በዚህም መሠረት ምልከታ ከተካሄድባቸው ሃያ አራት ክፍለ ጊዜያት መካከል መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለምን ያህል ጊዜ ተጠቅመውባቸዋል? የሚለው ጥያቄ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ውስጥ ቀርቧል፤

**ሠንጠረዥ ሁለት**፡- የክፍል ውስጥ ምልከታ ከተካሄደባቸው ሃያ አራት ክፍለ ጊዜያት መካከል መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የተጠቀሙባቸው ክፍለ ጊዜያት ብዛት

| ምልከታ የተካሄደባቸው ክፍሎች ደረጃ | ምልከታ የተካሄደባቸው ጠቅላላ ክፍለ ጊዜያት ብዛት | መምህራን በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የተጠቀሙባቸው ክፍለ ጊዜያት ብዛት | | መምህራን በትምህርት መርጃ መሣሪያ ያልተጠቀሙባቸው ክፍለ ጊዜያት ብዛት | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) |
| 7ኛ ክፍል | 12 | 5 | 41.67% | 7 | 58.33% |
| 8ኛ ክፍል | 12 | 4 | 33.33% | 8 | 66.67% |

ሠንጠረዥ ሁለት እንደሚታየው በአራቱ ታላሚ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሁለቱ የክፍል ደረጃዎች በተደረገው የአስራ ሁለት አስራ ሁለት ጊዜ የክፍል ውስጥ ምልከታ በሰባተኛ ክፍል አምስት ጊዜ (41.67%) በስምንተኛ ክፍል ላይ አራት ጊዜ (33.33%) መምህራኑ በትምህርት መርጃ መሣሪያ አስደግፈው እንደአቀረቡ ይገልፃል። በአንፃሩ በ7ኛ ክፍል ሰባት ጊዜ (58.33%)፣ በ8ኛ ክፍል ደግሞ ስምንት ጊዜ (66.67%) ያለ ትምህርት መርጃ መሣሪያ በቃል ብቻ ትምህርቱን እንደሚሰጡ ያሳያል።

በምልከታው ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ጥራትና መጠን በተመለከተ በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ በተደረገው ምልከታ በተራ ቁጥር 13 ሥር በቀረበው ጥያቄ መሠረት እንደሚከተለው ለማሳየት ተሞክሯል፤

**ሠንጠረዥ ሦስት**፡- በምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ጥራት

| የክፍል ደረጃ | በአገልግሎት ላይ የዋሉ መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | የጥራት ደረጃ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እጅግ በጣም | | በጣም ጥሩ | | ጥሩ | | በቂ | | አነስተኛ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) |
| 7ኛ ክፍል | 5 | - | - | - | - | 1 | 20% | 1 | 20% | 3 | 60% |
| 8ኛ ክፍል | 4 | - | - | - | - | - | - | 2 | 50% | 2 | 50% |

መግለጫው የሚያስገነዝበው በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች መምህራን የተጠቀሙባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የጥራት ደረጃ በአብዛኛው አነስተኛ እንደሆነና የተወሰኑት ብቻ በጥሩ እና በበቂ ደረጃ ላይ መገኘታቸውን ነው፡፡

በዚህ ጥናት ምዕራፍ ሁለት ውስጥ 2.4.4 ላይ ጥሩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ባሕርያት ብለው ካስቀመጡዋቸው አሥር ነጥቦች መካከል አንዱ፣ ጥሩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በክፍል ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች በሙሉ በሚታይ ሁኔታ ሰፋ ባለ መጠን መዘጋጀት ይኖርባቸዋል የሚል ነው፡፡ በዚህም መሠረት በመማር-ማስተማር ሂደት በክፍል ምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉትን የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠን ደረጃ በማዘጋጀት እንደሚከተለው በሠንጠረዥ አራት ቀርቧል፡፡ የመጠን ደረጃውም "እጅግ በጣም ሰፊና ጉልህ"፣ "በጣም ሰፊና ጉልህ"፣ "በቂ" እና "አነስተኛ" በሚሉት ገላጭ ሐረጋት እንዲለካ ተደርጓል፤

**ሠንጠረዥ አራት**፡- በምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠን

| የክፍል ደረጃ | በአገልግሎት ላይ የዋሉ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | በአገልግሎት ላይ የዋሉ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠን | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እጅግ በጣም ሰፊና ጉልህ | | በጣም ሰፊና ጉልህ | | በቂ | | አነስተኛ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) |
| 7ኛ ክፍል | 5 | - | - | 2 | 40% | 2 | 40% | 1 | 20% |
| 8ኛ ክፍል | 4 | - | - | 2 | 50% | 2 | 50% | - | - |

መግለጫው የሚያመለክተው በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች በመማር-ማስተማር ሂደት ወቅት መምህራን የተጠቀሙበት የመርጃ መሣሪያዎች መጠንም በየክፍል ደረጃው ሲታይ በጣም ሰፊና ጉልህ የሆኑ ሁለት ብቻ ሲሆኑ፣ ከዚያ በታች በቂ የሚባሉት ደግሞ በየክፍል ደረጃው ሁለት ሁለት ብቻ ናቸው፡፡ እንደዚሁም አነስተኛ መጠን ያለው የትምህርት መርጃ መሣሪያ በሰባተኛ ክፍል ላይ አንድ ብቻ መሆኑን ሠንጠረዡ ያሳያል፡፡

በሠንጠረዥ ሦስት እና አራት ላይ እንደተገለጸው፣ አብዛኛዎቹ መምህራን በክፍል ውስጥ ለማስተማሪያነት የሚጠቀሙባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በጥራትም ሆነ በመጠን ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠን አነስተኛ መሆንና ጎልቶ አለመታየት በተለይ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ወደ ኋላ ለሚቀመጡ ተማሪዎች ለእይታ ስለሚያዳግት በትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ አማካይነት ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ሊያዛባው ይችላል፡፡

## 4.2 የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ብቃት

መምህራን በቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደት የታቀደውን የትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ ከፍተኛ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑ ዕሙን ነው፡፡ መምህራን የቋንቋውን ትምህርት፣ ብቃት ባላቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አስደግፈው ማቅረብ ለዓላማው ስኬት ወሳኝ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የመምህሩን ችሎታ ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም የመምህራንን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ብቃት በተመለከተ በምልከታ ጥያቄ ተራ ቁጥር አስራ ሰባት አማካይነት የተገኘው ምላሽ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ቀርቧል፤

**ሠንጠረዥ አምስት**፡- የክፍል ምልከታ በተካሄደባቸው ጊዜያት መምህራን አገልግሎት ላይ በአዋሏቸው የቋንቋ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የመጠቀም ብቃት

| ምልከታ የተካሄደባቸው ክፍሎች ደረጃ | በአገልግሎት ላይ የዋሉት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | መምህራን አገልግሎት ላይ በአዋሏቸው የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የመጠቀም ብቃታቸው | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እጅግ በጣም ጥሩ ነው | | በጣም ጥሩ ነው | | ጥሩ ነው | | አነስተኛ ነው | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) |
| 7ኛ ክፍል | 5 | - | - | 1 | 20% | 3 | 60% | 1 | 20% |
| 8ኛ ክፍል | 4 | - | - | 1 | 25% | 2 | 50% | 1 | 25% |

በሰንጠረዥ አምስት ላይ እንደተገለፀው በአራቱ ታላሚ ትምህርት ቤቶች የሰባተኛ ክፍል መምህራን ከተጠቀሙባቸው አምስት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አንዱን (20%) እጅግ በጣም ጥሩ፣ ሦስቱን (60%) በጥሩ፣ አንዱን (20%) በአነስተኛ ደረጃ እንደተገለገሉበት ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በስምንተኛ ክፍል ላይ ከተጠቀሙባቸው አራት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አንዱ ብቻ (20%) በጣም ጥሩ በሆነ መልኩ፣ ሁለቱ (40%) በጥሩ ሁኔታ፣ አንዱ (20%) ደግሞ በአነስተኛ ደረጃ አገልግሎት እንደሰጡ እንረዳለን፡፡ ከዚህም ሌላ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች መምህራን ከተጠቀሙባቸው ዘጠኝ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፣ መምህራኑ በአመዛኙ "በጥሩ" ሁኔታ የተገለገሉባቸው ቢሆንም አጠቃቀማቸው ሙሉ በሙሉ ብቃት አለው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ይህ ደግሞ በምዕራፍ ሁለት 2.5.3 ላይ እንደተገለጸው ለመምህራኑ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም ብቃት ማነስ ሊሆን የሚችለው የመምህሩ ችሎታ ማነስ ወይም ግድየለሽነት መሆኑ ከተብራራው ሐሳብ ጋር ይዛመዳል፡፡

በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመጠቀም ማስተማር ጤናማ የክፍል ውስጥ መስተጋብር እንደሚፈጥር በምዕራፍ ሁለት በ2.5 ላይ ተገልጿል፡፡ መርጃ መሣሪያዎች የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት በመቀስቀስ በንቃት የመሳተፍ ሀይል ይጨምራሉ፡፡ የሚቀርበውን ትምህርት እውነተኛነት ስለሚያጎላው ለመማር-ማስተማሩ ሂደት መሣካት ፋይዳ ያለው ጤናማ የክፍል ውስጥ መስተጋብር ይፈጥራሉ፡፡ ከዚህ አንፃር መምህራኑ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በሚጠቀሙበት ጊዜ የነበረውን የክፍል ውስጥ መስተጋብር በተመለከተ በምልከታ ጥያቄ ቁጥር ሃያ አማካኝነት ለመዳሰስ ተሞክሯል፤

**ሠንጠረዥ ስድስት፡-** መርጃ መሣሪያዎቹ በአገልግሎት ላይ ሲውሉ የነበረው የክፍል ውስጥ መስተጋብርን በተመለከተ

| ምልከታ የተካሄደባቸው ክፍሎች ደረጃ | መምህራን የተጠቀሙባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | | መርጃ መሣሪያዎቹ አገልግሎት ላይ ሲውሉ የነበረው የክፍል ውስጥ መስተጋብር | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | እጅግ በጣም ጥሩ ነው | | በጣም ጥሩ ነው | | ጥሩ ነው | | አነስተኛ ነው | |
| | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) |
| 7ኛ ክፍል | 5 | - | - | - | - | - | 3 | 60% | 2 | 40% |
| 8ኛ ክፍል | 4 | - | - | - | 1 | 25% | 2 | 50% | 1 | 25% |

በሠንጠረዥ ስድስት እንደተገለጸው መምህራን በሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለማስተማር ከተገለገሉባቸው አምስት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ውስጥ ሦስቱ (60%)

“ጥሩ” የሆነ የተማሪዎች እርስ በርስ መስተጋብር ሲፈጥሩ በሁለቱ (40%) ደግሞ መስተጋብሩ “አነስተኛ” እንደሆነ ለማየት ተችሏል፡፡ በስምንተኛ ክፍል ከተጠቀሙባቸው ከአራቱ ውስጥ አንዱ (25%) “በጣም ጥሩ” ሁለቱ (50%) “ጥሩ” እና አንዱ (25%) “አነስተኛ” የእርስ በርስ መስተጋብር እንደፈጠሩ ያሳያል፡፡ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች በቋንቋ ትምህርት አገልግሎት ላይ ከዋሉት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች “እጅግ በጣም ጥሩ” የተማሪ-ለተማሪ የእርስ በርስ መስተጋብር የፈጠረ መርጃ መሣሪያ እንደሌለ ከተገኘው መረጃ ለመመልከት ተችሏል፡፡ ጥቅም ላይ የዋሉት መርጃ መሣሪያዎች በተወሰነ ደረጃ በተማሪዎች መካከል የእርስ በርስ መሰተጋብር እንደፈጠሩ የሚያሳይ ቢሆንም ክፍተት እንዳለ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ በምዕራፍ ሁለት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአግባቡ የመጠቀም ፋይዳ ተብለው ከተዘረዘሩት ውስጥ አንዱ ጤናማ የክፍል መስተጋብር እንዲፈጠር ማበረታታት እንደሆነ ከተብራራው ሀሳብ አንፃር ሲታይ የተወሰነ ክፍተት እንዳለው ያመላክታል፡፡

በምልከታ ጥያቄ በተራ ቁጥር ሃያ ሦስት አማካይነት ተማሪዎች በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ታግዞ የቀረበላቸውን የቋንቋ ትምህርት ምን ያህል እንደተገነዘቡት ለመገምገም በመምህራኑ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምን ያህል? አፋጣኝ ምላሽ መስጠት እንደቻሉ ለሚዳስሰው ጥያቄ የተገኘው መረጃ ቀጥሎ ቀርቧል፤

**ሠንጠረዥ ሰባት፡-** በመርጃ መሣሪያዎች ታግዞ የቀረበውን ትምህርት በተመለከተ ለተማሪዎች ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች የሚሰጡት ምላሽ የፍጥነት ደረጃ

| የክፍል ደረጃ | በአገልግሎት ላይ የዋሉት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | በመርጃ መሣሪያዎች ታግዞ የቀረበውን ትምህርት በተመለከተ ለተማሪዎች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች የተሰጠው ምላሽ የፍጥነት ደረጃ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እጅግ በጣም ፈጣን ነው | | በጣም ፈጣን ነው | | ዝቅተኛ ነው | | በጣም ዝቅተኛ ነው | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት(%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) |
| 7ኛ ክፍል | 5 | - | - | 3 | 60% | 2 | 40% | - | - |
| 8ኛ ክፍል | 4 | - | - | 2 | 50% | 2 | 50% | - | - |

ሠንጠረዥ ሰባት የሚያመለክተው ተማሪዎች በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተደግፎ የቀረበላቸውን የቋንቋ ትምህርት መሠረት በማድረግ መምህራኑ ለሚያቀርቡላቸው የግምገማ ጥያቄዎች የሚሰጡትን ምላሽ በተመለከተ በተገኘው መረጃ መሠረት፣ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች

መምህራን ከተገለገሉባቸው አምስት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መካከል በሦስቱ (60%) ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ ተምረው ለሚጠየቁት ጥያቄ “በጣም ፈጣን” ምላሽ ይሳጣሉ፡፡ በአንፃሩ በሁለቱ ጊዜ (40%) “በዝቅተኛ” ደረጃ ነው መልስ የሰጡት፡፡ በተጨማሪም በስምንተኛ ክፍል በሁለቱ ጊዜያት (50%) ደግሞ “በጣም ፈጣን” ምላሽ ሲሰጡ በቀሪዎቹ ሁለት (50%) ደግሞ የተማሪዎቹ ምላሽ “በዝቅተኛ” ደረጃ ላይ የሚገኝ ነበር፡፡

ቋንቋን በመማር-ማስተማር ሂደት መምህራኑ የተገለገሉባቸውን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ከማራኪነት አንፃር፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ማራኪ ቀለም ያላቸው ትክክለኛ ንድፍ የያዙ እና የተማሪዎችን ስሜት የሚያረኩ ሊሆኑ ይገባል የሚል ሐሳብ በምዕራፍ ሁለት 2.4.3 ላይ ተገልጿል፤ ይህም ተስማሚ የሆነ ትምህርት መርጃ መሣሪያን አግኝቶ ለመጠቀም ካሏቸው ሰባት መመዘኛዎች አንዱ ማራኪነት ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ በክፍል ውስጥ ምልከታ በጥያቄ ተራ ቁጥር 22 ላይ በዕለቱ ስለቀረበው የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ ማራኪነት፣ “ለሁሉም ተማሪዎች”፣ “ለአብዛኛዎቹ”፣ “ለግማሹ የደስታ መንፈስ የፈጠረባቸው” መሆኑን የሚመለከትና “ምንም ደስታ አልፈጠረባቸውም” በሚሉ ገላጭ ሃረጋት እንዲለካ ተደርጓል፡፡ ይህንም በሚቀጥለው ሠንጠረዥ እንመልከት፤

**ሠንጠረዥ ስምንት**፡- በዕለቱ መምህራን የተገለገሉባቸው የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ማራኪነት በተመለከተ የተማሪዎችን ስሜት የሚዳስስ

| የክፍል ደረጃ | በአገልግሎት ላይ የዋሉት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | በዕለቱ መምህራን የተገለገሉባቸው የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ማራኪነት በተማሪዎች ላይ ያሳደረው የደስታ ስሜት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ለሁሉም ተማሪዎች የደስታ ስሜት ፈጥሯል | | ለአብዛኛዎቹ ተማሪዎች የደሰታ ስሜት ፈጥሯል | | ለግማሾቹ ተማሪዎች የደስታ ስሜት ፈጥሯል | | ለተማሪዎቹ ምንም የደስታ ሰሜት አልፈጠረባቸውም | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) |
| 7ኛ ክፍል | 5 | - | - | 2 | 40% | 3 | 60% | - | - |
| 8ኛ ክፍል | 4 | - | - | 2 | 50% | 2 | 50% | - | - |

በዕለቱ በመማር-ማስተማር ሂደት በአገልግሎት ላይ የዋለውን የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ ማራኪነት፤ የተማሪዎችን ስሜት በተመለከተ መግለጫውን ስንዳስስ፣ በሁለቱ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አብዛኛዎቹ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የደስታ ስሜት እንዳላቸው፤ በሦስቱ የቋንቋ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ደግሞ ግማሽ ያህል ተማሪዎቹ የደስታ ሰሜት

የነበራቸው መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎችን በተመለከተ በሁለቱ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ከተማሪዎቹ አብዛኛዎቹ የደስታ ስሜት እንደፈጠረባቸውና በቀሪዎቹ ሁለቱ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ደግሞ ግማሽ ያህል ተማሪዎች የደስታ ስሜት የፈጠረባቸው መሆኑን መረጃው ያስረዳል፡፡ በአጠቃላይ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የደስታ ስሜት የነበራቸው ሲሆን ይህም በምዕራፍ ሁለት በተራ ቁጥር 2.4.3 ከተገለፀው ሀሳብ ጋር የተስማማ መሆኑን ያመላክታል፡፡

የክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ሂደትን የተሟላ ለማድረግ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ ማስተማር ጠቀሜታው የጎላ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ስለትምህርት መርጃ መሣሪያዎችም አጠቃቀም በምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተገለጸው በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም በተማሪዎች አዕምሮ ላይ አዳዲስ ዕውቀቶችና ክሂሎች እንዲቀረጹ፣ ተቀርፀውም በተገቢው ጊዜና ቦታ በተግባር እንዲገለገሉባቸው ያደርጋሉ፡፡ ምክንያቱም የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የተለያዩ ተግባራትንና ልምዶችን በማቅረብ የተማሪዎችን ፍላጎት በማነሳሳት፣ ትኩረታቸውን ወጥሮ በመያዝ ወደሚፈለገው ግብ እንዲያመሩ በክፍል ውስጥ ጥሩ ተሳትፎ እንዲያሳዩ መምህራን የሚገለገሉበት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያና አጠቃቀም ይወስናል በማለት ተገልጾ ነበር፡፡ ከዚህ ሐሳብ በመነሣት መምህራን የተገለገሉባቸው የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የማድረግ ደረጃውን በተመለከተ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ "እጅግ በጣም ጥሩ ነው"፣ "በጣም ጥሩ ነው"፣ "ጥሩ ነው"፣ "አነሰተኛ ነው" በሚሉ ገላጭ ቃላት እንዲለካ ተደርጎ ቀርቧል፤

**ሠንጠረዥ ዘጠኝ፡-** በአገልግሎት ላይ በዋሉት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመቀጠም ተማሪዎች የሚያሳዩት የክፍል ውስጥ ተሳትፎ

| የክፍል ደረጃ | በአገልግሎት ላይ የዋሉት የተምህርት ቋንቋ መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | በአገልግሎት ላይ በዋሉት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመቀጠም ተማሪዎች የሚያሳዩት የክፍል ውስጥ ተሳትፎ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እጅግ በጣም ፈጣን ነው | | በጣም ፈጣን ነው | | ጥሩ ነው | | ዝቅተኛ ነው | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁ ጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) |
| 7ኛ ክፍል | 5 | - | - | 2 | 40% | 3 | 60% | - | - |
| 8ኛ ክፍል | 4 | - | - | 2 | 50% | 2 | 50% | - | - |

ከሠንጠረዥ ዘጠኝ የምንረዳው መምህራን በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ በመታገዝ ሲያስተምሯቸው ተማሪዎች ያላቸው የክፍል ውሰጥ ተሳትፎ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች ሲቃኝ

በሁለት በሁለት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመጠቀም የሚያሳዩት የክፍል ውስጥ ተሳትፎ "በጣም ጥሩ" በሆነ ደረጃ ላይ መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም በሰባተኛ ክፍል በሦስት በስምንተኛ ክፍልም በሁለት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተማሪዎች ያላቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በ"ጥሩ" ደረጃ ላይ ነው፡፡ ምንም እንኳን መምህራን የተገለገሉባቸው በቁጠር "አነስተኛ" የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ቢሆኑም የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በጥሩ ደረጃ ላይ መገኘቱን ያመለክታል፡፡

### 4.2.1 በአገልግሎት ላይ የዋሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተገቢነት

የጥናቱ ታላሚ መምህራን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በሚያስተምሩባቸው ክፍሎች የተጠቀሙባቸው የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በዕለቱ ሊሰጥ የታቀደውን ረቂቅ የትምህርት ይዘት ተጨባጭና ግልፅ ከማድረግ አኳያ ምን ያህል ተገቢነት እንዳላቸው በክፍል ውስጥ ምልከታ ጊዜ ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡ የተገቢነት ደረጃውም "እጅግ በጣም ጥሩ"፣ "በጣም ጥሩ"፣ "ጥሩ" እና "አነስተኛ" በሚሉት ገላጭ ቃላት እንዲለካ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት በክፍል ውስጥ ምልከታ በተራ ቁጥር 15 ላይ የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ እንደሚከተለው ቀርቧል፤

**ሠንጠረዥ አስር፡-** በምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተገቢነት

| የክፍል ደረጃ | አገልግሎት ላይ የዋሉ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | በአገልግሎት ላይ የዋሉ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተገቢነት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እጅግ በጣም ጥሩ | | በጣም ጥሩ | | ጥሩ | | አነስተኛ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) |
| 7ኛ ክፍል | 5 | - | - | 3 | 60% | 1 | 20% | 1 | 20% |
| 8ኛ ክፍል | 4 | - | - | 2 | 50% | 1 | 25% | 1 | 25% |

አብዛኛዎቹ መምህራን እጅግ ውስን በሆኑ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አልፎ አልፎ ቢጠቀሙም፣ የዕለቱን ትምህርት ዓላማ ከማሳካት አኳያ የተደረገው የአጠቃቀም ብቃት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ተገቢነት የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ በአንፃሩ ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀም የጥቂት መምህራንን የቅድመ ዝግጅት ብቃት ማነስን ያመላክታል፡፡

### 4.2.2 መምህራን እውነተኛ በሆኑ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የመጠቀም ልምድ

በእውነተኞች የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም ቶሎ ሊረሱ የሚችሉትን ረቂቅ የሆኑ አስተሳሰቦችን፣ የነገሮችን እንቅስቃሴ፣ ጥልቀት፣ ክብደት፣ ጠረን፣ ስሜት፣ ጣዕምና፣ ቀለም በተጨባጭ ከማስረዳት አኳያ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለውና ከተቻለ አዲስና ወጥ በሆነ እውናዊ የትምህርት ልምምድን ተጠቅሞ ማስተማር ሌሎች ወካይ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ከመጠቀም ይልቅ የተሻለ እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት ላይ በተራ ቁጥር 2.2 ላይ ተገልጾ ነበር።

በዚህም መሠረት በመማር-ማስተማር ሂደት የክፍል ውስጥ ምልከታ በተካሄደበት ወቅት የተስተዋሉትንና የተመዘገቡትን እና በመምህራኑ ዓመታዊ ዕቅድ የ2001 ዓ.ም. የሁለተኛ መንፈቀ ዓመት የሰባተኛና የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዕቅድ መካከል የአንድ ትምህርት ቤት ተወስዶ ከየርዕሶቹ አንፃር የተጠቆሙትን እውነተኛ የሆኑትን አጋዥ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት ለመቃኘት ተሞክሯል፤

**ሠንጠረዥ አስራ አንድ፡-** በክፍል ምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ከዓይነት አንፃር ሲታዩ

| የክፍል ደረጃ | በአገልግሎት የዋሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች | በአገልግሎት ላይ የዋሉ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዓይነትና ብዛት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እውነተኛ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | | ዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ብዛት | | ድምፃዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | | ድምፃዊ ወዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) |
| 7ኛ ክፍል | 5 | 1 | 20% | 4 | 80% | - | - | - | - |
| 8ኛ ክፍል | 4 | 3 | 75% | 1 | 25% | - | - | - | - |

ከሠንጠረዥ አስራ አንድ መገንዘብ የሚቻለው በክፍል ምልከታ ወቅት ለሰባተኛ ክፍል የመማር-ማስተማር ሂደት መምህራኑ ከተጠቀሙባቸው አምስት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መካከል አንዱ እውነተኛ (20%) ሲሆን፣ በስምንተኛ ክፍልም ከቀረቡት ከአራቱ እንዲሁም ሦስቱ (75%) እውነተኛ ናቸው። እነዚህንም በዝርዝር ሲታዩ ሰባተኛ ክፍል ከቀረበው በአራቱ ትምህርት ቤቶች በአንደኛው ላይ በተካሄደ የክፍል ውስጥ ምልከታ የትምህርቱ ርዕስ "ደብዳቤ"

ስለነበር በትክክል የመስሪያ ቤት ደብዳቤዎችና የመምህሯን የግል ደብዳቤ በማቅረብ እንደእውነተኛ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ነው መምህሯ የተጠቀሙበት፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በስምንተኛ ክፍል የክፍል ውስጥ ምልከታ ወቅት የትምህርቱ ርዕስ ስነቃል ስለነበር፤ ተማሪዎች ያሰባሰቡትን ሥነቃል በክወና እንዲያቀርቡ የተደረጉት ተማሪዎች ሲሆኑ ተማሪዎቹ ያሰባሰቡትን ሥነቃል በክወና በመተግበራቸው እንደ እውነተኛ የትምህርት መርጃ መሣሪያ በመቁጠር የተቀመረ ስሌት ነው፤

በሠንጠረዥ አስራ አንድ በ2001 ዓ.ም. የሁለተኛ መንፈቀ ዓመት ለናሙና የአንዱን ትምህርትቤት (መሠረት ትምህርት ቤትን) በመውሰድ እውነተኛ የሆኑ አጋዥ መሣሪያዎችን ዳሰናል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ በዚሁ ትምህርት ቤት በክፍል ምልከታ ወቅት እና ከመምህራን የመንፈቀ ዓመት ዕቅድ መረጃዎች በመነሳት ለመማር ማስተማር ሂደት በአጋዥነት በአገልግሎት ላይ የዋሉት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በዓይነት ተከፋፍሎ እንደሚከተለው ቀርቧል፤

**ሠንጠረዥ አስራ ሁለት፡-** ከታላሚ ትምህርት ቤቶች ለናሙና በአንዱ (በመሠረት ትምህርት ቤት) የአማርኛ ቋንቋ የትምህርት እቅድ ውስጥ የተጠቆሙትን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት በዓይነት ተለይቶ ሲቃኝ

| የክፍል ደረጃ | በዕቅድ ለመጠቀም የተጠቆመ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣርያዎች ዓይነት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በዕቅድ ደረጃ የተጠቆሙ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | የሚታዩ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ ብዛት | | የሚደመጡ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | | የሚደመጡና የሚታዩ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) |
| 7ኛ ክፍል | 13 | 13 | 100% | - | - | - | - |
| 8ኛ ክፍል | 11 | 11 | 100% | - | - | - | - |

ከዚህ በላይ ከቀረበው መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው በተያዘው የትምህርት ዘመን ሁለተኛ መንፈቀ ዓመት፣ ከታላሚ ትምህርት ቤቶች በአንደኛው ለሁለቱም የክፍል ደረጃዎች መምህራን ሊጠቀሙ ከአቀዷቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መካከል ዕውነተኛ ነገርን የሚጠቁም አንድም አልነበረም፡፡

በምዕራፍ ሁለት በተራ ቁጥር 2.3.2 እንደተገለፀው የሚታዩ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በሁሉም የትምህርት እርከኖች ለሚሰጡ የቋንቋ ትምህርት የሚያገለግሉ ቢሆንም በተለይ በአንደኛ ደረጃ አንደኛና ሁለተኛ ዕርከን የቋንቋ ትምህርት የመማር-ማስተማር ሂደት ትምህርቱን ግልፅ፣ ቀላልና ተጨባጭ አድርጎ ለማቅረብ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ መምህራን ከየትኛውም የትምህርት መርጃ መሣሪያ ዓይነት ይልቅ በሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ ማስተማር ይቀላቸዋል፤ ያዘወትራሉም፡፡ በተለይም ቻርቶች፣ ሥዕሎች፣ ሰሌዳዎች፣ ፍላሽ ካርዶች እና የመሳሰሉት የቋንቋ ትምህርት መምህራን በቀላሉ የሚጠቀሙባቸው የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሊሆኑ ይችላሉ በማለት ተገልጿል፡፡

በሠንጠረዥ አስራ አንድ ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው በክፍል ምልከታ ወቅት በሰባተኛ ክፍል በአገልግሎት ላይ ከዋሉት አምስት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መካከል አራቱ እንደዚህም በስምንተኛ ክፍል ከአራቱ  መካከል አንዱ የሚታይ ነበር፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በሠንጠረዥ አስራ ሁለት ከተጠናቀረው መረጃ እንደምንገነዘበው በተያዘው የትምህርት ዘመን ከታላሚ ትምህርት ቤቶች በአንደኛው ከታቀዱ የሰባተኛ ክፍል አስራ ሦስት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መካከል አስራ ሦስቱ የሚታዩ ሲሆኑ እንደዚሁም አስራ አንድ የስምንተኛ ክፍል የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በሙሉ ዕይታዊ መሆናቸውን መረጃው ያመለክታል፡፡

የሚደመጥ እና የሚደመጡና የሚታዩ በሆኑ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን መጠቀም መምህሩ የማስተማር መርሖዎች ማለትም፣ ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ እና በተግባር እየከወኑ መማር የሚሉትን ዓይነት መርሕ መምህሩ እንዲከተል ከማስቻላቸውም በተጨማሪ በክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች በፍላጎት ላይ የተመሠረተ የትምህርት አቀባበል ላይ ዘላቂነት ያለው ምቹ ዐወድ በመፍጠር፤ የትምህርት ሂደቱን ምቹ ከማድረጋቸውም በላይ የመምህሩን የሥራ ጫና ያቃልላሉ የሚል በምዕራፍ ሁለት በተራ ቁጥር 2.3.3 ጠቅሰው ነበር፡፡

በዚህም መሠረት በጎንደር ከተማ አስተዳደር አራት አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ዕርከን ትምህርት ቤቶች በሚሰጡ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜያት በተደረገው የክፍል ውስጥ ምልከታም ሆነ በመምህራኑ በተዘጋጀ የ2001 ዓ.ም ሁለተኛ መንፈቀ ዓመት በሁለቱም ክፍሎች የአማርኛ

ቋንቋ ትምህርት ዕቅዶች ውስጥ አንዱም የሚደመጥና እና የሚደመጥና የሚታይ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ አልተጠቀሰም፤ መምህራኑም ሲጠቀሙበትም አልታዩም።

የሚደመጥ የሚደመጥና የሚታይ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያን በሚመለከት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መኖር /አለመኖራቸውን ለማወቅ ለመምህራን በተራ ቁጥር አስራ አራት በትምህርት ቤትዎ ትምህርት የሚተላለፍበት ሬዲዮ አለ? የሚል የቃል ጥያቄ ቀርቦ ነበር። የተገኘው ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል፤

መ1፡- አዎ አለ፤ ነገር ግን ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አገልግሎት አይሰጥም፣

መ2፡- አዎ አለ፤ ነገር ግን በአሁኑ ዘመን ያለው የሬዲዮ ስርጭት ለአማርኛ ቋንቋ ጊዜ አልተመደበም፣

መ3፡- አዎ አለ፤ ነገር ግን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የስርጭት ፕሮግራም ለሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት ስለተመደበ አሁን የቋንቋ ትምህርት የስርጭት ጊዜ የለውም፣

መ4፡- አዎ አለ፤ ይሁን እንጂ ለቋንቋው ትምህርት አገልግሎት አይሰጥም፣

መ5፡- አዎ አለ፤ ቢሆንም ባዶ የሬዲዮ ካሴት ታቅፈን ቀርተናል፤ ለአማርኛ ቋንቋ የስርጭት ጊዜ አልተመደበለትም፣

መ6፡- አዎ አለ፤ በብልሽት ምክንያት ለሁሉም የትምህርት ዓይነት አገልግሎት አይሰጥም፤ ነገር ግን ለአማርኛ ቋንቋ የጊዜ ሰሌዳ ስለሌለው ብልሽቱ ባይኖርም አንጠቀምበትም፣

መ7፡- አዎ አለ፤ እንደ አስፈላጊነቱ በቴፕ አስገልብጠን መጠቀም ከቻልን ካሴቱ አለ እንጂ የሰርጭት ጊዜ ተነሥቶበታል፣

መ8፡- አዎ አለ፤ የሬዲዮ ስርጭት ለሥነምግባርና ሥነዜጋ ትምህርት ስለዋለ የቋንቋው ስርጭት ጊዜ የለውም፤ በቴፕ ካሴት ግን አስገልብጦ መጠቀም ይቻላል።

ይህ በጽሑፍ መጠይቅ ተራ ቁጥር 25 ለቀረበው ጥያቄ መምህራን ከሰጡት ምላሽ ጋር ይመሳሰላል፣

ከፍ ሲል ከተዘረዘሩት የመምህራን ምላሾች መረዳት እንደሚቻለው ሬዲዮ በትምህርት ቤቶቹ ውስጥ “አዎ አለ” የሚል ምላሽ በዋናነት የተደጋገመ ሲሆን ሆኖም ግን የሬዲዮ ትምህርት ስርጭት አገልግሎት ለቋንቋ ትምህርት ያልተመደበ መሆኑን ያሳያል። በቃል ጥያቄ ቁጥር አስራ አምስት እና አስራ ስድስት ላይ በትምህርት ቤትዎ ውስጥ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት

የሚያገለግል ከሬዲዮ ሌላ፣ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ለመጠቀም የሚያግዙ መሣሪያዎች አሉ? ካሉ መምህራን ለምን ዓይነት አገልግሎት ያውሉዋቸዋል? መሣሪያዎቹ እንዴት ተገኙ? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር፡፡ የተገኘው ምላሽም እንደሚከተለው ቀርቧል፤

መ1፡- አዎ አለ፤ ኢንተርኔት፣ ቴሌቪዥን፣ ኮምፒውተርና ከአናትበላይ ፕሮጀክተር አሉን፤ ለድራማና ሥነጽሑፍ ክበብ እንቅስቃሴ ይውላል፤ በመምህራን ጥረት ከጎንደር ሊንክ ኢንግላንድ ግብረሰናይ ድርጅት የተሰጠ ስጦታ ነው፡፡

መ2፡- አዎ አለ፤ ቴሌቪዥን፣ ኮምፒውተር፣ ኢንተርኔትና ከአናትበላይ ፕሮጀክተር አገልግሎቱ ለድራማና ሥነጽሑፍ ክበብ የሥራ እንቅስቃሴ የሚሉ ሲሆኑ መምህራን ባደረግነው መልካም ግንኙነት ጎንደር ሊንክ ኢንግላንድ ግብረሰናይ ድርጅት በስጦታ ሰጠን፡፡

መ3፡- አዎ አለ፤ ቴፕ፣ ኢንተርኔት፣ ኮምፒውተርና ቴሌቪዥን አሉን ለድራማና ሥነ ጽሑፍ ክበብ የሥራ ዕንቅስቃሴና ለትምህርት ቤቱ፣ መምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞች አገልግሎት ይሰጣሉ፣ መንግሥትና የዳሽን ቢራ ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መምህራን የተለያዩ የማስታወቂያ! ስራዎችን በመሥራታችን ለትምህርት ቤቱ በስጦታ ሰጠን፡፡

መ4፡- አዎ አለ፤ ኢንተርኔት፣ ኮምፒውተር፣ ቴፕና ቴሌቪዥን ለድራማና ስነፅሁፍ የሥራ ዕንቅስቃሴና ለትምህርት ቤት መምህራንና የአስተደደር ሰራተኞች የተለያዩ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ መንግስትና የዳሽን ቢራ ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ከመምህራን ጋር ባደረጉት የተለያዩ ግንኙነቶች የተሰጠ ዕርዳታ ነው፡፡

መ5፡- አዎ አለ፤ ቴፕ፣ ኮምፒውተርና ቴሌቪዥን ከአናትበላይ ፕሮጀክተር ከቀይ መስቀልና ከፀረ ኤች አይ ቪ ኤድስ ድርጅት መምህራን ፕሮጀክት ፕሮፖዛል በመቅረፅ በስጦታ የተገኘ ነው፡፡ ለድራማና ለሥነጽሑፍ ክበብ የሥራ እንቅስቃሴና ለአስፈላጊ የትምህርት ቤት የሥራ እንቅስቃሴዎች ያገለግላሉ፡፡

መ6፡- አዎ አለ፤ ቴፕ ከአናት በላይ ፕሮጀክተር፣ ኮምፒውተርና ቴሌቪዥን ከፀረ ኤች አይ ቪ ኤድስ ድርጅትና ከቀይ መስቀል በዕርዳታ የተሰጠን ነው፡፡ ለድራማና ሥነጽሑፍ ክበብ እና አስፈላጊ የትምህርትቤት የሥራ እንቅስቃሴዎች ይከናወኑበታል፣

መ7፦ አዎ አለ፤ ቴፕ፣ ኮምፒውተር፣ ከአናትበላይ ፕሮጀክተር፣ ጎንደርና ፈረንሳይ የሁለት እህትማማቾች ከተማ ግብረሰናይ ድርጅት የተሰጠ ነው። ለተለየዩ የትምህርት ቤት ስብሰባዎች ለክበባት የሥራ እንቅስቃሴ ያገለግላሉ፣

መ8፦ አዎ አለ፤ ከአናትበላይ ፕሮጀክተርና ኮምፒውተር ከጎንደርና ፈረንሳይ የሁለት እህትማማቾች ከተማ የዕርዳታ ሰጭ ድርጅት በስጦታ የተገኘ ነው። ለክበባት የሥራ እንቅስቃሴና አስፈላጊ ለሆኑት የትምህርት ቤት የሥራ ክንውን ሁሉ እንጠቀምበታለን።

ከመምህራን መልስ መረዳት እንደሚቻለው፣ በሁሉም ታላሚ ትምህርት ቤቶች ሬዲዮ መኖሩን፣ ነገር ግን የአማርኛ ቋንቋ ሬዲዮ የስርጭት ጊዜ እንዳልተመደበለትና ለቋንቋው ትምህርት አገልግሎት እንደማይሰጥ ሁሉም ተጠኚ መምህራን (100%) ገልፀዋል፡ ፡ ይህም በጽሁፍ መጠይቅ ተራ ቁጥር ሃያ ስድስት መምህራን ከሰጡት ምላሽ ጋር አንድ ነው። በቃለ መጠይቅ ጥያቄ በተራ ቁጥር አስራ አምስትና አስራ ስድስት ስለሬዲዮና ሌላ የኤሌክትሮኒክስ መሣርያ መኖር አለመኖርና ለምን አገልግሎት እንደሚውልና እንዴት ተገኘ? ለሚለው ጥያቄ ከሬድዮ መሣሪያ ሌላ "አዎ አለን"፣ በማለት አብዛኛዎቹ ኢንተርኔት፣ ኮምፒውተር፣ ቴፕ፣ ቴሌቪዥንና ከአናትበላይ ፕሮጀክተር አለን ሲሉ ጥቂቶች ኢንተርኔት የሌላቸው መሆኑን ገልፀዋል። ያገኙትም ከመንግሥትና ከተለያዩ ግብረሰናይ ድርጅቶች በስጦታ እንደሆነና አገልግሎት የሚሰጠውም ለድራማና ሥነጽሑፍ ክበብ የሥራ እንቅስቃሴና የተወሰኑት ለትምህርት ቤቱም የተለያየ አገልግሎት እንደሚውሉ ገልፀዋል። ነገር ግን በመማር-ማስተማር ሂደት የተሟላ የቴክኖሎጂ መሣሪያዎች እያሏቸው ለቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደት ድምፃዊና ድምፃዊ ወዕይታዊ መሣሪያዎችን እንደማይጠቀሙ ጥናቱ አረጋግጧል።

### 4.2.3 መምህራን በኅትመት ውጤቶች የመጠቀም ልምድ

የኅትመት ውጤቶች ሲባል ለልዩ ልዩ የቋንቋ ትምህርት ክህሎት ማዳበሪያ የሚያገለግል ተጨማሪ መጽሐፍ፣ ጋዜጣ፣ መጽሔት፣ ከተለያዩ ጽሑፎች ተቀንጭበው የተወሰዱ ቅንጫቢዎች፣ በራሪ ወረቀቶችና ፖስተሮች የመሳሰሉትን ያጠቃልላሉ። ከዚህ አንፃር የጎንደር ከተማ አስተዳደር አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ዕርከን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራን በኅትመት ውጤቶች የመጠቀም ልምዳቸው ሲታይ በአብዛኛው የማይጠቀሙ ሲሆን በሰባተኛ ክፍል ሁለት ትምህርት ቤቶች ላይ ሁለት መምህራን (25%) በኅትመት ውጤቶች ሲጠቀሙ በክፍል ምልከታ

ወቅት ታይቷል፤ የትምህርቱ ርዕስ “ግጥም” የሚል ስለነበር መምህራን ቅንጫቢ ጽሑፎችን በማባዛት ለተማሪዎች የተባዛውን ግጥም በማደል የመማር-ማስተማር ሂደቱ በጎትመት ውጤቶች መታገዙን መመልከት ቢቻልም፤ አብዛኛዎቹ 75% መምህራን በምንም ዓይነት የጎትመት ውጤቶች ያልተጠቀሙና በዕቅዳቸው ውስጥም ያልተካተቱ መሆናቸውን በጥናቱ ውጤት መመልከት ተችሏል፡፡

### 4.2.4 መምህራን በተለያዩ ሠሌዳዎች የመጠቀም ልምድ

የመማሪያ ክፍሎች በተለየዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መሟላትና መዋብ እንደሚኖርባቸው ይታመናል፡ እነዚህም መርጃ መሣሪያዎች የተለያዩ ሠሌዳዎችን ያካትታሉ፡፡ በምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተገለፀው በአንድ መማሪያ ክፍል ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸው ሠሌዳዎች ዓይነት፣ የተለያዩ ትምህርታዊ ማስታወቂያ የሚለጠፍበት ሰሌዳ፣ የተለያዩ ፍላሽ ካርዶች፣ ሥዕሎች፣ ፎቶግራፎችና ቻርቶች፣ ወዘተ. የሚንጠለጠሉበት ከወፍራም ሱፍ ጨርቅ የተሠራ ሻሽ ሠሌዳ እና ብረት ነክ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚያያዙበት መግነጢሳዊ ሠሌዳዎች ምልከታ በተካሄደባቸው የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሉም፡፡ የቋንቋ መምህሩ የሚቀጠሙባቸውን የተለያዩ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በሚገባ በተዘጋጁ ሠሌዳዎች መጠቀም ትልቁ የመምህራን ቁልፍ ተግባር ነው፡፡ በእርግጥ በፋብሪካ የሚመረቱ እንደመግነጢሳዊ ሠሌዳ ዓይነቶችን ማግኘት ሊያስቸግር ይችላል፡፡ ነገር ግን በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ እንደማስታወቂያ ሠሌዳ፣ ሻሽ ሠሌዳ በመሳሰሉት በመጠቀም በሥርዓት የመማር-ማስተማር ሂደቱን መተግበር ይቻል ነበር፡፡ ይህም የክፍሉን ውበት ከመጠበቁም በላይ የተማሪዎችን ስሜት በማነቃቃትና ፍላጎታቸውን በመቀስቀስ ረገድ ጥሩ ሚና ይኖረው ነበር፡፡ ነገር ግን የቋንቋ መምህራኑ በሠሌዳዎች የመጠቀም ልምዳቸው እጅግ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

## 4.3 ታላሚ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በተመለከተ ስለአጋጠማቸው ችግር ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ሲገመገም

- መምህራኑ በትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም የገጠማቸው ችግር ሲገለጽ፤ ተገቢ የሆነ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያን ለመጠቀም አስፈላጊ ወጭ ማግኘት

ባለመቻላችን በራሳችን እንደመፍትሔ በመጠቀም ከተለያዩ አጋር ድርጅቶች ጋር የፈጠርነውን ግንኙነትና የተገኘውን ገንዘብ ለቀረፅነው ዓላማ ማስፈፀሚያ ማድረግ አልቻልንም። ምክንያቱም በትምህርት ቤቱ ሒሳብ ክፍል ገቢ ይሆንና ለትምህርት መርጃ መሣሪያ ያልነው በጀት አገልግሎት ሳይሰጥ ለተለያዩ የትምህርት ሥራዎች ይውላል፤

- መምህራን ለፍተው ደክመው ለተደጋጋሚ ጊዜ ሊያገለግል ይችላል ብለው የሚጠቀሙበትን የትምህርት መርጃ መሣሪያ አንድ ጊዜ ተጠቀምና ውርውር የሚል የሥራ ተነሳሽነትን የሚቀንስ አመራር አለ። ፈጣሪ ነህ ሁልጊዜ አዲስ ተጠቀም በማለት ተገቢ ያልሆነ አመራር መኖር፤
- ማስተማር የህሊናና የሙያ ሥራ መሆኑ እየታወቀ የትምህርት መርጃ መሣሪያ የመገምገሚያ መስፈርት ላይ ሰፍሮ መምጣቱና የምንገለገልባቸውን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እንደማያገለግሉ ተቆጥሮ መጣላቸው፤ የትምህርት ቤቱ አቅም ስለማይፈቀድ የተለያዩ መጪዎችን ለማግኘት መጣር እንጂ እንዴት ልጠቀም የሚለውን ብዙ እንዳናስብ ችግር ፈጥሮብናል፤
- እራሱን የቻለ የቋንቋ ክፍል አለመኖር፤
- የማስተማሪያ መሣሪያዎች ተሟልተው አለመገኘት፤

ያጋጠሙን ችግሮች ናቸው በማለት መምህራን ገልፀዋል።

## 4.4 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችና የማስተማሪያ መሣሪያዎች

የማስተማሪያ መሣሪያዎች በሚል የተጠቃለሉት መርሐ ትምህርቱ፣ የተማሪው መጽሐፍ እና የመምህሩ መምሪያ ናቸው። እነዚህ መሣሪያዎች በምዕራፍ ሁለት እንደተጠቀሰው የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በመጠቀም በኩል ለመምህሩ ያላቸው እገዛ ከፍተኛ ነው። የዚህ ክፍል ዋና ትኩረትም በ1996 ዓ.ም. ተሻሽሎ የተዘጋጀ የሰባተኛና የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርሐ-ትምህርት እና በ1997 ዓ.ም. ተሻሽሎ የተዘጋጀ የሰባተኛና ስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪው መምሪያ መጽሐፍ እና የመምህሩ መምሪያ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን መምህሩ እንዲጠቀም ምን ያህል እገዛ እንደሚያደርጉላቸው ለማወቅ በቃልና በጽሑፍ መጠይቅ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው ነበር፤ የተገኘውም መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል፤

### 4.4.1 ለመምህራን ከቀረበው ቃለመጠይቅ

በዚህ ክፍል የማስተማሪያ መሣሪያዎቹ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለመጠቀም ለመምህራኑ የሚያደርጉትን እገዛ ለማወቅ ከቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሚከተለው ምላሽ ተገኝቷል፤

በተራ ቁጥር ስምንት የቋንቋ ማስተማሪያ መሣሪያዎቹ የቋንቋ ትምህርትን በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለመጠቀም እገዛ አላቸውን? ለምን? የሚል ጥያቄ ቀርቦ፣ ሁሉም መምህራን (ስምንቱም) 100% በጣም ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡ ለምን ለሚለው ጥያቄ ከአብዛኛዎቹ ስድስቱ (75%) መምህራን መርሐ ትምህርቱና የመምህሩ መምሪያ በምን ዓይነት እና እንዴት? ባለ ሁኔታ መጠቀም እንደሚኖርብን ዓይነታቸውንና አጠቃቀሙን በመጠቆም በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ስላላቸው በቀላሉ ማግኘት የሚቻል ከሆነ የተጠቆመውን ስለምንጠቀም የተማሪው መፅሀፍም በጥንድ፣ በቡድንና በተናጠል ምንን? እንዴት? መጠቀም እንዳለብን ስለሚጠቁም ለአጠቀቀም እጅግ ከፍተኛ እገዛ አላቸው ሲሉ ቀሪዎቹ ሁለቱ መምህራን (25%) መርሐ ትምህርቱ ካለ ሁሉንም አጠቃሎ ስለሚይዝ መርሐ ትምህርቱ ነው የበለጠ ጠቀሜታ ያለው፤ ይሁን እንጂ በደረጃ ሁሉም እንደሚያስፈልጉ ግልፅ ነው የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

በተራ ቁጥር ዘጠኝ በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ ለመጠቀም ያግዘናል ብለው በማሰብ የሚገለገሉት የትኛውን የማስተማሪያ መሣሪያ ነው? በሚል ለቀረበው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ የሚከተለው ነው፤

ሁሉም መምህራን (100%) አንዱ በተጓደለበት ሁኔታ መርጃ መሣሪያን ተጠቅሞ የቋንቋን ትምህርት ማስተማር አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም አንዱም በተጓደለበት የተሟላ የመማር ማስተማር ሒደት አይተገበርምና፤ ነገር ግን ስምንቱም መምህራን (100%) በየትምህርት ቤታቸው ከተወሰነ የተማሪ መጽሐፍ ሌላ መርሐትምህርትም ሆነ የመምህር መምሪያ የሌለ መሆኑና እስከ ክልል ትምህርት ቢሮ ድረስ አመልክተው ማግኘት እንዳልቻሉ፤ ከጎንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅም ኮፒ አድርገን እንመልስ ብለው ጠይቀው ምንም እንዳላገኙና የዓመታዊ የትምህርት ዕቅዳቸውን የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ ብቻ መሰረት በማድረግ እንደሚያቅዱና የትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹንም በዚህ መንገድ አቅደው እንደሚጠቀሙ

ገልፀዋል፡፡ በዚህ ምክንያት የተሟላ የቋንቋ ትምህርት እንደማንሰጥ እናውቃለን በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

### 4.4.2 ለመምህራን ከተሰራጨው የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

ከቃለመጠይቁ የተገኘውን መረጃ በጽሑፍ መጠይቅ ለማጎልበት በተራ ቁጥር አስራ ሰባት የማስተማሪያ መሣሪያዎች መምህራን በትምህርት መርጃ ታግዘው እንዲጠቀሙ አጋዥ ናቸው? እንዴት? የሚል ጥያቄ ለመምህራኑ ቀርቦ የተገኘው መልስ ስምንቱም መምህራን (100%) "አዎ" በሚል መልስ አመችነታቸውን ገልፀዋል፡፡ እንዴት? ለሚለው ጥያቄ ዛሬ እኛ የመምህሩ መመሪያም ሆነ መርሐ ትምህርቱ በእጃችን ላይ ስለሌለ በተማሪው መጽሐፍ ብቻ ዕቅድ ለማዘጋጀትም ሆነ ለመጠቀም በመገደዳችን ምን ያህል እንደምንቸገር ተገንዝበናል፡፡ ስለዚህ ሁሉም በተሟላ መልኩ ከተገኙ አመቺ መሆናቸውን እናውቃለን፡፡ በተለይ በትምህርት መርጃ መሣሪያ ለመጠቀም የሁሉም የማስተማሪያ መሣሪያዎች ተሟልቶ መገኘት እጅግ አስፈላጊ ናቸው በማለት ገልፀዋል፡፡

ታላሚ መምህራን ከቃለ መጠይቅና ከጽሑፍ መጠይቁ ከሰጡት ምላሽ መረዳት እንደተቻለው በጥናቱ ታላሚ የሆኑት አራት ትምህርት ቤቶች የቋንቋ መምህራኑ የሰባተኛና የስምንተኛ ክፍል መርሐ ትምህርት እና የመምህሩ መምሪያ የሌላቸውና የተወሰኑ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍት ብቻ እንዳላቸው ነው፡፡ እነዚህ የትምህርት መሣሪያዎች ባልተሟላ ወይም ጎደሎ በሆኑበት ሁኔታ በቂ የቋንቋ ትምህርት እየተሰጠ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡ መምህራን የመንፈቀ ዓመቱንም ሆነ የዕለት ዕቅዳቸውን አዘጋጅተው ለመጠቀም መሣሪያዎቹ እጅግ አስፈላጊ ናቸው፡፡ በምዕራፍ ሁለት Widdowson (1990:129) ማስተማሪያ መሣሪያዎች ለመምህራን የመማር ማስተማር ሂደቱን እንዴት እንደሚተገበሩና ምን? ለምን? እንደሚጠቀሙ መሪ ናቸው በማለት ገልጸዋል፡፡ ስለዚህ የተሟላ ትምህርት እየተሰጠ ነው ለማለት እንደማያስችልና እነዚህ መሣሪያዎች ባለመኖራቸው ምክንያት የመንፈቀ ዓመቱንም ሆነ የዕለት ዕቅዳቸውን ለማቀድና ለመጠቀም እንደአማራጭ የወሰዱት የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ መጠቀምን ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም በየትምህርት ቤቶቹ መማር-

ማስተማር ሂደት ላይ ያለውን ሁኔታ ለማነፃፀር የሚረዳን መረጃ ቀጥሎ በቀረቡት ሠንጠረዦች እንዳሰስ፡፡

መግለጫዎቹ በ1996 ዓ.ም. ተዘጋጅተው አገልግሎት በሚሰጡት የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ውስጥ ለሁለተኛው መንፈቀ ዓመት ትምህርት የተጠቆሙት የሰባተኛ እና የስምንተኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በተጓዳኝ ደግሞ በየክፍል ደረጃዎቹ ያለ እነዚህ በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ብቻ በመጠቀም ያቀዱትና በዚህ የመንፈቀ ዓመት ዕቅድ ላይ የጠቆሟቸውን የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር ደረጃ በደረጃ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ከመንፈቀ ዓመቱ ጋር ቅርበት እንዲኖረው የሁለተኛው መንፈቀ ዓመት በአስረጅነት ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ አስራ ሦስት**፡- በሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ውስጥ የተጠቀሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር /ሁለተኛው መንፈቀ ዓመት/

| የቋንቋ ትምህርት ክፍል | የትምህርት ይዘት | የተጠቀሙት የትምህርት መረጃ መሣሪያዎች |
|---|---|---|
| ጽሕፈት | ዓረፍተ ነገርን አገጣጥሞ አንቀፅ መጻፍ | ናሙና አንቀፆችን<br>በተማሪዎች የተጻፉ የተመረጡ አንቀፆች |
| ሥነልሳን | በአያያዦች መጠቀም | የአያያዦች ዝርዝር<br>በአያያዦች የተጣመሩ ዓረፍተ ነገሮች |
| ንባብና ማስተዋል | አምዶችን ከጋዜጦችና ከመጽሔቶች መለየት | ጋዜጦች<br>መጽሔቶች |
| ጽሕፈት | ዋናና ንዑስ ርዕሶችን እንዲሁም ፍሬ ነገሮችንና ዝርዝሮችን መለየት | ፍሬያማ ዝርዝሮቻቸው የተጻፉባቸው ሞዴል ወረቀቶች |
| ጽሕፈት | ልዩ ልዩ ደብዳቤዎችን መጻፍ | የደብዳቤ አጻጻፍ መመሪያዎች<br>የልዩ ልዩ ደብዳቤዎች ናሙናዎች |
| ጽሕፈት | አስተዋፅኦ መነደፍ | አስተዋፅኦ አነዳደፍን የሚያሳዩ ሞዴሎች |
| ጽሕፈት | አንቀፆችን አገጣጥሞ አጭር ጽሑፍ መጻፍ | የጽሑፍ ጥበብ መምሪያ |
| ሥነጽሑፍ | ግጥም | የግጥም ዓይነቶችን<br>ሞዴል ግጥሞች<br>በተማሪዎች የሚጻፉና የተመረጡ ግጥሞች |
| ንባብና ማስተዋል | ማውጫ መጠቀም | መጻሐፍት<br>ቤተ-መጻሕፍት |
| ሥነፅሁፍ | ሥነቃል፣ ተረቶችና ምሳሌያዊያዊ አነጋገሮች | ተረቶች<br>ምሳሌያዊ አነጋገሮች<br>አባባሎች |
| ንግግርና ማዳመጥ | ተጠየቃዊ አስተሳሰብ<br>የድርጊቶችና የጊዜ ቅደም ተከተል | የድርጊቶችና ቅደም ተከተል የያዘ ጽሑፍ<br>የጊዜን ቅደም ተከተል የሚያሳይ ቻርት |
| ጽሕፈት | ማስታወሻ መያዝ | የማስታወሻ አያያዝ ዘዴን የሚገልፅ ጽሑፍ |
| ንግግር | አንድን ሐሳብ በተለያዩ አባባሎች መግለፅ | አንድን ሐሳብ በልዩ ልዩ አባባሎች የሚገልፁ ምሳሌዎች |
| ጽሕፈት | ውጥን ታሪክን መጨረስ | ያልተጨረሱ ታሪኮች ጽሑፍ<br>የተጠናቀቁ ጽሑፎች ሞዴል |
| ጽሕፈት | የራስን የሕይወት ታሪክ መጻፍ | ሞዴል የሕይወት ታሪኮች<br>የግል ሕይወት ታሪክ አጻጻፍ መመሪያ |
| ሥነጽሑፍ | ልቦለድ ጽሑፍ | የልቦለድ ዓይነቶች እና ልዩነታቸውን የሚያሳይ ጽሑፍ |
| ጽሕፈት | የሀቀኛና የፈጠራ ጽሑፍ አንድነትና ልዩነት | የልቦለድና ኢልቦለድ ጽሑፎች ባሕርያትን የሚያሳይ ጽሑፍ |

**ምንጭ**፡- የቋንቋዎች ት/ሥ/ት/ዝ ቡድን (1996፣22-32)፡፡

ሠንጠረዥ አሥራ ሦስት ላይ እንደሚታየው ከሰባተኛ ክፍል የሁለተኛው መንፈቀ ዓመት የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ውስጥ ሃያ ስምንት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በአጋዥነት እንዲያገለግሉ ተጠቁመዋል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ቀጥሎ በቀረበው የመምህራን የመንፈቀ ዓመት የትምህርት ዕቅድ ውስጥ ሦስት ያህሉ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብቻ በአጋዥነት እንዲያገለግሉ ተደርገው ተጠቁመዋል፡፡ መርሐ ትምህርት የሃገሪቱን አጠቃላይ የትምህርት ፍልስፍና፣ የቋንቋ ትምህርት ፖሊሲ መነሻ አድርጎ መምህሩ ማስተማር የሚገባውን፣ ተማሪው መማር ያለበትን የሚገልፅ መሠረታዊ የትምህርት አካል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር መርሐ ትምህርት የአንድን ሀገር የቋንቋ ትምህርት ፖሊሲ ስለሚያንፀባርቅ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አደራጆች፣ የመማሪያ መሣሪያ አዘጋጆች፣ መምህራን፣ የፈተና ክፍሎች፣ በአጠቃላይ የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን መረጃ የሚያገኙት ከዚሁ ሰነድ ነው የሚል በምዕራፍ ሁለት በተራ ቁጥር 2.7.2 ተጠ ቅሷል፡፡ ነገር ግን በታላሚ ትምህርት ቤቶች የታየው ዕቅድ አወጣጥ ከመርሐ ትምህርቱ በቅርፅና በይዘት ያልተስማማ መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

**ሰንጠረዥ አስራ አራት**፡- በ2001 ዓ.ም. ለሁለተኛ መንፈቀ ዓመት ለሰባተኛ ክፍል በተዘጋጀው ዕቅድ ውስጥ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር /ከታላሚ ትምህርት ቤቶች መካከል የአንዱን /የመሠረት/ን በናሙናነት የተወሰደ

| የቋንቋ ትምህርት ክፍል ዘርፎች | የትምህርት ይዘት | የተጠቆሙ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች |
|---|---|---|
| የሥነቃል ምንነትና ዓይነቶች | የሥነቃል ዓይነቶችንና ምንነት መለየት | የሥነቃል ዓይነትና ቻርት |
| የአንቀፅ አገነባብ | የአንቀጽ አገነባብን ይለያሉ | - |
| ልዩ ልዩ ጽሑፎች መረዳትና መጻፍ | የጋዜጣ፣ መጽሔት ዓይነቶችንና የአምድ ምንነት | ጋዜጦች፣ መጽሔቶች |
| የደብዳቤ ዓይነቶች | የግልና የመስሪያቤት ደብዳቤን ይለያሉ | የደብዳቤ ዓይነቶች |
| ውጥን ታሪክና ድርሰት መጻፍ | ወጥን ታሪክን በመጨረስ የተሟላ ድርሰት ይጽፋሉ | - |
| ተመሳሳይ ዓረፍተ ነገሮችን መተካት | ለአንድ ዓረፍተ ነገር ተመሳሳይ ዓረፍተ ነገር መተካት | - |
| ማወዳደርና ዝርዝር ሐሳቦች | ከሠንጠረዥ እያወዳደሩ ወደ ዓረፍተ ነገር ቀይሮ መጻፍ | - |
| ድርሰት | የድርሰት ምንነትን መገንዘብ፣ማወቅ | - |
| የድርሰት አፃፃፍ ስልት | አመዛዛኝ ሥዕላዊ ገላጭ መሆናቸውን ማወቅ | ጋዜጦች መጽሔቶች የደብዳቤ ዓይነቶች |

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የስምንተኛ ክፍል ሁለተኛ መንፈቀ ዓመት መርሐ ትምህርት እና የስምንተኛ ክፍል ሁለተኛ መንፈቀ ዓመት መምህራን ዕቅድ ላይ የተጠቀሙት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣርያዎች ንፅፅር በተመሳሳይ ሁኔታ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ አስራ አምስት**፡- በስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሐ-ትምህርት ውስጥ የተጠቀሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር (የሁለተኛው መንፈቀ ዓመት)

| የትምህርት ክፍል | ይዘት | የትምህርት መርጃ መሣርያዎች |
|---|---|---|
| ጽሕፈት | ዓረፍተ ነገርን በመገጣጠም አንቀፅ መጻፍ | የአንቀፅ ምንነትና ቅርፆቹን የሚያሳይ ማብራሪያ |
| ጽሕፈት | አንቀፆችን አገጣጥሞ አጭር ጽሑፍ መጻፍ | ናሙና ጽሑፎች የተለያዩ ዓይነት የአጻጻፍ ስልት ያላቸው ናሙና ጽሑፎች /ተራኪ፣ ገላጭ፣ አመዛዛኝ.../ |
| ሥነልሳን | የአያያዦች አጠቃቀም | አያያዦችን የያዙ ካርዶች በአያያዦች የተያያዙ ሞዴል ዓ. ነገሮች |
| ንባብና ማስተዋል | ተጠየቃዊ አስተሳሰብ<br>የመንስኤና ውጤት ግንኙነት<br><br>ማገናዘብ /አናሎጅ/ | ሥዕሎች<br>የተለያዩ መንስኤና ውጤት ያለባቸው ዝርዝሮች<br>ሞዴል ሥዕል |
| ጽሕፈት | የደብዳቤዎች አጻጻፍ | ናሙና ደብዳቤዎች፣ ናሙና ፖስታዎች |
| ጽሕፈት | የአስተዋፅኦ አነዳደፍ | ሞዴል የተነደፉ አስተዋፅኦዎች |
| ሥነጽሑፍ | ሥነቃል/ተረቶች ምሳሌያዊ አነጋገሮች ወዘተ./ መጠቀም | ናሙና ስብሰብ ሥነቃሎች |
| ሥነጽሑፍ | ግጥም | ናሙና ግጥሞች |
| ጽሕፈት | ማስታወሻን የመውሰድ /የመያዝ ልምድ | ናሙና ማስታወሻዎች |
| ማዳመጥና ንግግር | በራስ አባባል ማቅረብ | ስለቤተሰብ ምጣኔ፣ ስለአካባቢ እንክብካቤ፣ ስለ ኤድስ የሚገልፅ ፖስተሮች፣ ሥዕላ ሥዕሎችና መግለጫዎች |
| ጽሕፈት | ውጥን ታሪክን መጨረስ | የጽሑፍ፣ የሥዕል፣ የካርቶን ናሙናዎች |
| ጽሕፈት | የሌላ ሰው የሕይወት ታሪክ ይጽፋሉ | ናሙና የሕይወት ታሪክ |
| ማዳመጥና ንግግር | አንድን ሐሳብ በልዩ ልዩ አባባል መግለፅ | የተለያዩ አባባሎች የሚያሳይ ሠንጠረዥ |
| ጽሕፈት | ጽሑፉን ማሳጠርና ማስፋፋት | ያጠረ ናሙና ጽሑፍ<br>ስለማስፋፋት የቀረበ የጽሑፍ ምሳሌ |
| ጽሕፈት | በሀቀኛና በፈጠራ ጽሑፎች መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት | ናሙና ጽሑፍ |
| ሥነ ጽሑፍ | ልቦለድ ጽሑፍ | የረጅምና አጭር ልቦለዶች ባሕርያትን /አንድነትንና ልዩነትን/ የሚያሳይ ቻርት<br>የተለያዩ ልቦለድ ጽሑፎች |

**ምንጭ**፡- የቋንቋዎች ት/ሥ/ት/ዝ ቡድን (1996፣24-40)፡፡

ሠንጠረዥ አስራ አምስት ላይ እንደሚታየው በስምንተኛ ክፍል የሁለተኛው መንፈቀ ዓመት መርሐ ትምህርት ውስጥ ሠላሳ ዓይነት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በአጋዥነት እንዲያገለግሉ ተጠቁመዋል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ቀጥሎ በቀረበው የ2001 ዓ.ም. የመምህራን የትምህርት ዕቅድ ውስጥ ስምንት የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ብቻ በአጋዥነት እንዲያገለግሉ ተደርገው ተጠቁመዋል፡፡ በዕርግጥ በመምህራኑ በተዘጋጀው የሁለተኛው መንፈቀ ዓመት ዕቅድ ላይ የተመለከቱትን የትምህርት ይዘቶችን ስናይ ሁሉም በመረጃ መሣሪያ መደገፍ የነበረባቸው ሲሆኑ በዝግጅት ማነስ የተነሳ ያለመርጃ መሣሪያ ታቅደዋል፡፡ እነዚህም ቢሆኑ በመርሐ ትምህርት ውስጥ ከተጠቆሙት ጋር ያላቸው የይዘትም ሆነ የቅርጽ ተመሳስሎ እጅግ ውስን ነው፡፡

**ሠንጠረዥ አስራ ስድስት፡-** በ2001 ዓ.ም. ለሁለተኛው መንፈቀ ዓመት ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጀው ዕቅድ ውስጥ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር /ከታላሚ ትምህርት ቤቶች መካከል የመሠረትን በናሙናነት የተወሰደ

| የቋንቋ ትምህርት ክፍል ዘርፎች | የትምህርት ይዘት | የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች |
|---|---|---|
| የመረጃ ምንጮች<br>ማስታወሻ አያያዝ<br>ቅጥያ<br>ሥርዕተ ነጥብ<br>አንቀፅ | የመረጃ ምንጮች<br>የማስታወሻ አያያዝ ስልት<br>ጥገኛና ነፃ ምዕላድ<br>ሥርአተ ነጥቦች<br>የአንቀፅ አጻጻፍ ቅርፅ | ሠንጠረዥ<br>ፎቶግራፍ<br>ቻርት<br>ሥዕል<br>ግራፍ<br>መጽሔት |
| የአረፍተ ነገር ቅደም ተከተል | የአረፍተ ነገር ቅደም ተከተል | ሞዴል ጽሑፎች |
| አያያዥ ቃላትና ሐረጋት | ድርሰት አጻጻፍ አያያዥ ቃላትን ተጠቀሞ ብቃት ያስጨብጣል | - |
| ድርሰት | ድርሰት መጻፍ | - |
| አስተዋጽኦ አነዳደፍ | አንቀፆችን ማስተካከል | - |
| የደብዳቤ ቅርፆች | የግል፣ ማስታወቂያ፣ ማመልከቻ ደብዳቤ ይለያሉ፡፡ | - |
| የድርሰት ዓይነቶች | የልቦለድና ኢልቦለድ አፃፃፍን ያጎለብታሉ | - |
| ጽሑፍ ማሳጠርና ማስፋፋት | ጽሑፍ የማሳጠርና የማስፋፋት ሥራ | - |
| ሥነቃል | ሥነቃል | - |
| ሥነግጥም | የተለያዩ ግጥሞች | - |

ባጠቃላይ መግለጫዎቹ የሚያመላክቱት ለሁለቱም ክፍሎች በተዘጋጁት መርሐ ትምህርቶች ውስጥ በተዘረዘሩት የትምህርት ይዘቶችና ለይዘቶቹ ማስተማሪያ በተጠቁሙት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እና መምህራኑ ያለ መርሐ ትምህርት ባዘጋጁት የመንፈቀ ዓመት ዕቅዶች ላይ በተጠቆሙት ይዘቶችና የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መካከል የታየው መመሳሰል እጅግ ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡

## 4.5 የመምህራንን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ብቃት የሚወስኑት ተላውጦዎች /Variables/

በዚህ ክፍል በጥናቱ የተካተቱ ታላሚ መምህራን የቋንቋ ትምህርት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ምን እንደሚመስልና የትምህርት መርጃ መሣሪያዎ የብቃት ደረጃ በምን በምን መልክ ሊገለፅ እንደሚችል በዝርዝር ተገልጿል፡፡ በዚህም ዙሪያ የተሰበሰቡት መረጃዎች በሁለት መንገድ ተከፍለው ተብራርተዋል፡፡ እነዚህም በግለሰባዊ ተላውጦዎች ዙሪያ እና በተቋማዊ አመራሩ አካላት (በትምህርት ቤት አመራር አካላቱ) ባሉ ተላውጦዎች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ናቸው፡፡

### 4.5.1 ግለሰባዊ ተላውጦዎች

#### 4.5.1.1 የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ ቅድመ የሥራ ላይ ሥልጠና

ለትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተግባራዊነት ውድቀትም ሆነ ዕድገት እውቀትና ብቃት በጣም አስፈላጊና ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው፡፡ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም የሚጎለብተው ለመምህራን በሚሰጥ ቅድመ ሥራ ላይ ሥልጠናዎች እና እንደዚሁም ባገኙት ሥልጠና መሠረት በሥራ ላይ በሚያደርጉት ተግባራዊ ልምምድ ነው፡፡

የሚቀጥለው መረጃ የመምህራንን የትምህርት ደረጃና የትምህርት መርጃ መሣሪያን በተመለከተ ስለአገኙት ቅድመ የሥራ ላይ ሥልጠና የሚገልፅ ነው፡፡

**ሰንጠረዥ አስራ ሰባት፡-** *የታላሚ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያን በተመለከተ የቅድመ ሥራ ላይ ሥልጠና*

| መምህር/ት | ዕድሜ | ፆታ | | የትምህርት ደረጃ | በዋናነት የሰለጠነበት የትምህርት መስክ | የአገልግሎት ዘመን | | | | የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በተመለከተ ቅድመ ሥራ ላይ ሥልጠና ራሱን ችሎ በኮርስ ደረጃ ወስደዋል | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሴት | ወንድ | | | በሰርተፍኬት | በዲፕለማ | በዲግሪ | ድምር | አዎ | የለም |
| 1 | 49 | ✓ | | ዲፕሎማ | አማርኛ | 10 | 20 | - | 30 | | ✓ |
| 2 | 58 | | ✓ | ዲፕሎማ | አማርኛ | 4 | 25 | - | 29 | | ✓ |
| 3 | 51 | | ✓ | ዲፕሎማ | አማርኛ | - | 32 | - | 32 | | ✓ |
| 4 | 50 | ✓ | | ዲፕሎማ | አማርኛ | 15 | 18 | - | 33 | | ✓ |
| 5 | 45 | | ✓ | ዲፕሎማ | አማርኛ | - | 26 | - | 26 | | ✓ |
| 6 | 43 | ✓ | | ዲፕሎማ | አማርኛ | 3 | 20 | - | 23 | | ✓ |
| 7 | 47 | ✓ | | ዲፕሎማ | አማርኛ | - | 22 | - | 22 | | ✓ |
| 8 | 46 | | ✓ | ዲፕሎማ | አማርኛ | - | 21 | - | 21 | | ✓ |

ከዚህ በላይ በቀረበው ሠንጠረዥ ሁሉም ታላሚ መምህራን የዲፕሎማ ምሩቅ፣ መሆናቸውንና በዋናነት የሠለጠኑበት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መሆኑንና ስምንቱም (ሁሉም) ታላሚ መምህራን የቅድመ የሥራ ላይ ሥልጠና የትምህርት መርጃ መሣሪያን በተመለከተ ራሱን የቻለ ኮርስ እንዳልወሰዱ ገልፀዋል፡፡ ስለዚህ በምዕራፍ ሁለት ተራ ቁጥር 2.5.3 ላይ መምህራን ሥልጠናን ባለማግኘታቸው ምክንያት በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚፈጥር ተገልጿል፡፡ ከዚህ አንፃር ታላሚ መምህራን ሥልጠና ያልወሰዱ መሆናቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ብቃትን የሚወስን ተላውጦ ነው፡፡

### 4.5.1.2 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አጠቃቀም በተመለከተ የታላሚ መምህራን የሥራ ላይ ሥልጠና

የትምህርት መርጃ መሣሪያን አጠቃቀም በተመለከተ ቅድመ የመምህርነት ሙያ ላይ ሥልጠና ቢሰጥም ባይሰጥም እንኳን መምህራን ተመርቀው ወደ ሥራው ዓለም ከተሠማሩ በኂላ የሙያ ላይ ሥልጠና ወይም የተሐድሶ ሥልጠና በሥራ ላይ ሆነው ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም ዓይነት የሥራ ላይ ሥልጠና የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም ብቃታቸውንና ክህሎታቸውን ያጠናክርላቸዋል፡፡ መምህራን የሥራ ላይ ሥልጠና መካፈልና አለመካፈላቸውን ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል፤

**ሠንጠረዥ አስራ ስምንት፡-** የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምን በተመለከተ መምህራን ያገኙት የሥራ ላይ ሥልጠና

| መልስ የሰጡ መምህራን ብዛት | ሥልጠና የወሰዱበት ዙር ብዛት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከአንድ ጊዜ በላይ የተካፈሉ | | አንድ ጊዜ ብቻ የተካፈሉ | | ምንም ያልተካፈሉ | |
| | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) |
| 8 | 1 | 12.5% | 1 | 12.5% | 6 | 75% |

ከዚህ በላይ ካለው ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው ከስምንቱ የጥናቱ ታላሚ መምህራን መካከል ስድስቱ (75%) መምህራን የትምህርት መርጃ መሣ ሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ ወደ ሥራ ዓለም ከተሠማሩ በኂላ ምንም ዓይነት ሥልጠና ያልተካፈሉና አንድ መምህር (12.5%) አንድ ጊዜ የሥራ ላይ ሥልጠና እንዳገኘና ሌላው ቀሪው አንድ መምህር (12.5%) ከአንድ ጊዜ በላይ ወደ ሥራ ዓለም ከተሠማሩ በኂላ ሥልጠና መካፈላቸውን በቃለ መጠይቅ ጥያቄ ተራ ቁጥር 10 ገልፀዋል፡፡ በፅሁፍ መጠይቅ ተራ ቁጥር 17 የቃለ መጠይቁን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ለወጣው ጥያቄ የሰጡት ምላሽም ከዚህ ጋር አንድ ዓይነት መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ስለዚህ በምዕራፍ ሁለት ተራ ቁጥር 2.5.3 ላይ ለመምህራን የሥራ ላይ ሥልጠና ማግኘት ከወቅታዊ መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምና የማስተማር ዘዴ ጋር እንዲተዋወቅ ያግዛል፡፡ በቅድመ ሥራ ላይ በጥልቀት ያላዩትን (በንድፈ ሐሳብ ብቻ ገረፍ ገረፍ አድርገው የታለፉትን) የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አጠቃቀም እውቀትና ክህሎት ለመከለስ እድል

ይሰጣቸዋል፡፡ ነገር ግን የሥራ ላይ ሥልጠና አለማግኘት አሉታዊ ተፅዕኖ አለው፡፡ ከዚህ አንፃር የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ብቃትን የሚወስን ተላውጦ ነው፡፡

### 4.5.1.3 በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለመጠቀም የቋንቋ መምህራኑ ፍላጎትና ተነሳሽነት

የቋንቋ መምህራኑ የቅድመ ሥልጠናም ሆነ የሥራ ላይ ሥልጠና ማግኘት በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለመጠቀም በቋንቋ መምህራኑ ፍላጎትና አጠቃቀም ረገድ ምን? ለምንና እንዴት? እንደሚጠቀሙ ዕውቀትና ክህሎት ስለሚኖራቸው የሥራ ፍላጎትና የተነሳሽነት ስሜት ይፈጥርላቸዋል፤ ከዚህ በተጨማሪ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ የሚያስተምሩት የቋንቋ ትምህርት በተማሪዎች ላይ የሚፈጥረውን የትምህርት አቀባበል ለውጥና ዕድገት ሲመለከቱ ሁልጊዜ የመጠቀም ፍላጎት ተነሳሽነት ያድርባቸዋል፡፡ በአንፃሩ ግን ቅድመ የሥራ ላይ ሥልጠናም ሆነ ወደ ሥራ ዓለም ከተሰማሩ በኋላ ሥልጠና ያልወሰዱ መምህራን ስለትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ለሚኖራቸው ፍላጎትና ተነሳሻነት ዝቅተኛ መሆን አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

ቀደም ሲል በሠንጠረዥ አስራ ሰባት እና በሠንጠረዥ አስራ ስምንት ላይ በተገለፀው መሠረት የጥናቱ ታላሚ የቋንቋ መምህራን ስምንቱም በሙሉ በመደበኛ የቅድመ መምህርነት ሥልጠናቸው ወቅት ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የሚመለከት ራሱን የቻለ ኮርስ እንዳልተማሩና ከአብዛኞቹ ታላሚ የቋንቋ መምህራን መካከል ስድስቱ (75%) ወደ ሥራው ዓለም ከተሠማሩ በኋላ ምንም ዓይነት የትምህርት መርጃ መሣሪያን የሚመለከት የሥራ ላይ ስልጠና እንዳልተካፈሉ፣ አንድ መምህር (12.5%) ለአንድ ጊዜ ያህል የስራ ላይ ሥልጠና እንደወሰዱ ሌላው ቀሪው አንድ መምህር (12.5%) ከአንድ ጊዜ በላይ የ ሥራ ላይ ሥልጠና እንዳገኙ በሠንጠረዥ አስራ ሁለት ላይ ተገልጿል፡፡ ይህንን በተመለከተ Newby et al. (1996:263) በምዕራፍ ሁለት፣ መምህራን ወደ ሥራ ዓለም ከመሠማራታቸው በፊት በሥልጠና ወይም በሥራ ላይ እያሉ ሥልጠና በመስጠት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ክህሎት ማስጨበጥ አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኞቹ ታላሚ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያን የሚመለከት ቅድመም ሆነ የሥራ ላይ ሥልጠና ያልተሰጣቸው መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ይህም በቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ ላይ መምህራኑ በትምህርት መርጃ

መሣሪያዎች ለመጠቀም ላላቸው ፍላጎትና ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆን ምክንያት (ተላውጦ) ሊሆን ይችላል፡፡

### 4.5.2 ተቋማዊ ተላውጦዎች

#### 4.5.2.1 ቦታን በተመለከተ

የጥናቱ ታላሚ የሆኑት አራት ትምህርት ቤቶች የቋንቋ መማሪያ ክፍሎች ሲታይ፣ ሁሉም መደበኛ መማሪያ ክፍሎች ናቸው፡፡ ይህም በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለመጠቀም ለምሳሌ በተለያዩ ሠሌዳዎች፣ የሚደመጡ፣ የሚደመጡና የሚታዩ መሣሪያዎች ለመጠቀም ወደመማሪያ ክፍሎች መሸከምና ማመላለስ አስቸጋሪ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ በምዕራፍ ሁለት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አጠቃቀም በተመለከተ ከተገለጹት ጠቃሚ እሴቶች መካከል ለመያዝና ለመፈተሽ የሚሰጡት ዕድል፣ በመስህብነታቸው ምክንያት ትኩረት እንዲሰጡ ያደርጋሉ በመባል ተገልጾ ነበር፡፡ ነገር ግን ለመያዝ አስቸጋሪና ለማስዋብም ሆነ ሳቢ ለማድረግ የተለየ ቦታ (መማሪያ ክፍል ከሌለ) ሁሉም የትምህርት ዓይነት መርጃ መሣሪያን ይገለገላሉና በክፍሏ የመደራረብና ተማሪዎች ሁሉንም የትምህርት ዓይነት መርጃ መሣሪያዎችን ተንጠልጥለው ስለሚያዩ በአንደኛው ክፍለ ጊዜ ወደ ሌላው ትምህርት ዓይነት የመሳብ ክፍተት ስለሚኖር ቦታም (የመማሪያ ክፍል እራሱን ችሎ አለመኖር) በትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም ላይ አንድ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡ ይህም መምህራን የሚፈጠረውን ሁኔታ በመፍራት በተገቢው መንገድ የትምህርት መርጃ መሣሪያን እንዳይጠቀሙ ጫና ሊያመጣ እንደሚችል ያመላክታል፡፡ ከዚህ አንፃር ቦታ አንድ ተላውጦ ነው፡፡

#### 4.5.2.2 በጀትን በተመለከተ

መምህራን በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለመጠቀም የትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹን በግዥና በስጦታ ነው የሚያገኙት፡፡ በግዥ ከሆነ ደግሞ ይብዛም ይነስም ገንዘብ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይህንን በሚመለከት ታላሚ ለሆኑት መምህራን በተደረገላቸው ቃለመጠይቅ በጥያቄ ተራ ቁጥር አስራአንድ ላይ  ሁሉም መምህራን የሰጡት ምላሽ የሚጠቀሙበትን የትምህርት መርጃ መሣሪያ ለማግኘት የበጀት ችግር እንዳለባቸው ነው፡፡ ይኸውም በየዓመቱ ለትምህርት ቤቱ በሚያቀርቡት ዓመታዊ ዕቅድ አስፈላጊ አጋዥ መጻሕፍትን ከነዋጋቸው፣ ሌሎችን ልዩ ልዩ መሣሪያዎችና

አጠቃላይ አስፈላጊ ወጭዎችን በመዘርዘር ካላቸው አስፈላጊነት አንፃር በጀት አቅደው ቢያቀርቡም፣ የትምህርት ቤቱ አመራር አካላት ግን የተወሰኑ የጽሕፈት መሣሪያዎችና ጥቃቅን ነገሮችን ብቻ እንደሚገዙላቸው አብራርተዋል፡፡ በተጨማሪም በዕቅዱ መሠረት የተፈለገውን ማንኛውንም ዓይነት ዕቃ በበቂ ደረጃ ማግኘት እንደማይችሉ ገልፅዋል፡፡ እንደአማራጭ ከተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር መምህራን በቡድንና በግል ግንኙነት በመመሥረት፣ የፕሮጀክት ፕሮፖዛል በመቅረፅ የተለያዩ በጀት ቢያገኙም፤ የተገኘውን እርዳታ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ለትምህርት ቤቱ ገቢ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ከገባ በኋላም ትምህርት ቤቶቹ ካለባቸው የበጀት ውስንነት የተነሳ ለሌሎች ፕሮግራሞች ያውሉታል፡፡ በዚህም የተነሣ ያገኙትን እርዳታ መምህራን ለአቀዱት ዓላማ ለማዋል እንዳልቻሉና የቴክኖሌጅ ውጤት የሆኑትን ግብረሰናይ ድርጅቶች እየገዙ እንደሰጧቸውና በእነዚህ መሣሪያዎች ለመጠቀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ዕቃዎችን ለመግዛት መምህራን የበጀት ችግር እንዳለባቸው ገልፀዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው የበጀት አለመኖር ወይም ዝቅተኛ መሆን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አጠቃቀም ብቃትን ሊወስኑ የሚችሉ በትምህርት ቤት በኩል የሚታዩ ተላውጦዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ ነው፡፡

### 4.5.2.3 የተለያዩ የትምህርት ባለሙያዎች አመራር

የተለያዩ የትምህርት ባለሙያዎች፣ መምህራን በየጊዜው ለመማር-ማስተማር ሂደት የሚጠቀሙባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አገልግሎት መስጠት ያለባቸው ለአንድ ጊዜ ብቻ ነው፤ ምክንያቱም መምህር መሪና ተመራማሪ እንደመሆኑ መጠን በየጊዜው አዳዲስ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን እየፈጠረ መጠቀም ይገባዋል ይላሉ፡፡ ከአንድ ጊዜ በላይ መጠቀም አላስፈላጊ ነው፡፡ ተጠቅማችሁ አስወግዱ ይላሉ፡፡ ይህን በተመለከተ በምዕራፍ ሁለት ተራ ቁጥር 2.5.3 ተማሪዎች በንቃት ለመሳተፍ እንዲችሉ ለማድረግ የሚገለገሉባቸው ናቸው፡፡ ከትምህርቱም ጎናዊና ተዋረዳዊ ዝምድና አንፃር የወደፊቱን የመማር-ማስተማር ሁኔታ በማሰብ መጠቀም ቀዳሚ ተግባር ነው፡፡ ዛሬ ለማስተማር አገልግሎት ላይ የዋለው የትምህርት መርጃ መሣሪያ ለሚቀጥለውና በተከታታይ ለሚቀርቡት ትምህርቶች መሠረት ሊሆን ይገባል፡፡ ለአንድ ጊዜ ብቻ ተጠቅመን ለሌላ ጊዜ እንዳማያገለግል ቆጥረን በሥርዓት የማናስቀምጠው ከሆነ

ከትምህርቱ ተለጣጣቂነት፣ ተከታታይነትና ተዛማጅነት አንፃር የሚሰጠው ፋይዳ እንደማይኖረው ከተገለፀው ሐሳብ ጋር የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከዚህ አንፃር በታላሚ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ብቃትን ሊወስኑ የሚችሉ ተቋማዊ (በትምህርት ቤት ውስጥ የሚታዩ) ተላውጦዎች ናቸው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና እና አስተያየት

በዚህ ክፍል በጥናቱ የመረጃ ውጤት ትንተና እና ማብራሪያን መሠረት በማድረግ የጥናቱ ማጠቃለያና አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በጎንደር ከተማ አስተዳደር አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡ ይህ ዓቢይ ዓላማ የሚያካትታቸው ዝርዝር ዓላማዎችም፡-

- በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም ተገቢ ሥልጠና ያገኙ መሆኑን መፈተሽ፣
- በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ያሉት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አጠቃቀም በተመለከተ ያላቸውን ግንዛቤና ዕውቀት መዳሰስ፣
- በተመረጡት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም ዙሪያ የሚያጋጥሟቸው ችግሮች ካሉ ለመለየት፣
- የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መሣሪያዎች (መርሐ ትምህርቱ፣ የመምህሩ መምሪያና የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ) ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ያላቸውን አስተዋጽኦ ለመዳሰስ፣ እና
- መምህራን የሚጠቀሙባቸው የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን እገዛ ምን ያህል እንደሆነ ለመዳሰስ ተሞክሯል፣

መምህራኑ ተገቢ የሆነ የትምህርት መርጃ መሣሪያ መጠቀም የሚያስችላቸውን የቅድመ ሥራም ሆነ የሥራ ላይ ሥልጠና ማግኘት የሚገባቸው ቢሆንም በቂ የሆነ ሥልጠና ባለማግኘታቸው በአጠቃቀም ረገድ ያላቸው ተሳትፎ አናሳ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ማቀድ፣ ማፈላለግና መምረጥ ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ዋናው ነገር የታቀዱትንና በሥጦታም ሆነ በግዥ የተገኙትን መርጦ በመማር-ማስተማር ሂደት በክፍል

ውስጥ በአግባቡ መጠቀም ወሳኝ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ በተካሄዱት የክፍል ውስጥ ምልከታዎች ማረጋገጥ እንደተቻ  ለው ከ58% እስከ 67% ያህሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚያስተምሩት ያለ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በቃል ብቻ ነው፡፡

መምህራን የሚጠቀሙባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሳቢ እንደሆኑ መጠናቸው ጉልህ ሆኖ መታየት የሚችል፣ ማራኪና ተስማሚ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ከዚህ አኳያ መምህራን የተጠቀሙባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመጠን ሆነ ከማራኪነት አንፃር ደረጃቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከተገቢነት አንፃርም አንዳንድ የዝግጅት ማነስ የሚታይባቸው መምህራን ተገቢ ያልሆኑ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሲጠቀሙ የተጠቀሙ መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

መምህራን የተጠቀመባቸው የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በዓይነት ተለይተው ሲታዩ አብዛኛዎቹ እይታዊ ናቸው፡፡ ሌሎች የሚደመጡ፣ የሚደመጡና የሚታዩ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በአራቱም ታላሚ ትምህርት ቤቶች በእርዳታ የተገኙ በቂ የሆኑ የኤሌክትሮኒክስ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እያሉ አገልግሎት ሲሰጡ አልታየም፡፡ አገልግሎት ላይ እንዳይውሉ ምክንያት የሚሆነው የኤሌክትሪክ ኃይል ነበር፡፡ ነገር ግን ሁሉም ትምህርት ቤቶች የሃያ አራት ሰዓት የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቀሚ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎቹ ለቋንቋው መማር-ማስተማር ሂደት አገልግሎት ሲሰጡ አልተስተዋሉም፡፡ ነገር ግን መምህራኑ ራሱን የቻለ የቋንቋ መማሪያ ክፍል ባለመኑሮ ለማንንዝ አስቸጋሪ በመሆኑ እንዳልተጠቀሙ ገልፀዋል፡፡

መምህራን ለመማር-ማስተማር ተግባር የሚያገለግሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለአንድ ጊዜ ብቻ እየተጠቀሙ እንዲጥሉ ከትምህርት ባለሙያዎች መመሪያ የተሰጣቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የክፍል ምልከታ በተካሄደባቸው ስምንት የመማርያ ክፍሎች ውስጥ ምንም አይነት እንደ መርጃ መሣሪያዎች የሚያገለግሉ ሰሌዳዎች አልነበሩም፡፡ ባለመኖራቸው በመማር-ማስተማር ሂደት የሚያገለግሉ እይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በሥርዓት በመስቀልና በመለጠፍ ረገድ መምህራኑ ሲቸገሩ ተስተውሏል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ መምህራኑ በእርዳታ ያገኙትን ባጀት

ላቀዱት ዓላማ እንዳያውሉ የየትምህርት ቤቶቹ አስተዳደር ባጀቱን ለሌላ አስተዳደራዊ ሥራ እያዋሉት መሆኑን ጥናቱ አመላክቷል፡፡

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ታግዘው ለማስተማር በቅድሚያ የቋንቋ ማስተማሪያ መሣርያዎች (መርሐ ትምህርት፣ የመምህር መምሪያና የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ)ን ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ይሁንና በጥናቱ በተካተቱ ትምህርት ቤቶች ግን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መሣሪያዎች ከተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ውጭ ሌሎች እንደሌሉ ተረጋግጧል፡፡ በዚህም የተነሣ የመንፈቀ ዓመቱንም ሆነ የዕለቱን ትምህርት ለማቀድና በአንፃሩም በተገቢ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ለመጠቀም አስቸጋሪ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡ የመንፈቀ ዓመት ዕቅዳቸውም ከመርሐ ትምህርቱ ጋር የየትምህርት ቤቶቹ እቅዶች የቅርፅና የይዘት ልዩነት ይታያል፡፡

እነዚህ የተጠቀሱት ችግሮች እንዳሉ ሆነው መምህራን በተገለገሉባቸው የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ግን የተማሪዎች የእርስ በርስ መስተጋብር እና የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በጥሩ ደረጃ እንደሚገኝ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

## 5.2 አስተያየት

በዚህ ጥናት ማጠቃለያ ላይ ለቀረቡት ችግሮች መፍትሔ ሊሆኑ ይችላሉ በማለት የሚከተሉት አስተያየቶች ቀርበዋል፤

ሀ. ለመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን በሚመለከት ተከታታይነት ያለው የሙያ ሥልጠና (ወርክሾፕ) ቢሰጣቸው፣

ለ. መምህራን፣ ቋንቋ ውስብስብ መሣሪያ መሆኑን ተረድተው ይህንን ውስብስብ መሣሪያ ግልፅ፣ ቀላልና ተጨባጭ በሆነ መንገድ ተማሪዎች እንዲማሩት ጥረት ቢያደርጉና መጠኑ የተሟላ፣ የተገቢነት ደረጃውን በጠበቀ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ በመጠቀም ቢያስተምሯቸው፤

ሐ. መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹን በዕርዳታ ማግኘት ብቻ ሳይሆን በተገቢው መንገድ ቢገለገሉበት እና በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች (በሚደመጥ፣ በሚደመጥና በሚታይ) ዓይነት የትምህርት መርጃ መሣሪያ በመገልገል ተማሪዎቻቸውን የተለያዩ የቋንቋ ክህሎት በሚያጎለብት መልኩ ቢያስተምሯቸው፡፡

መ. መምህራን አስፈላጊ ነው ብለው የተጠቀሙባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለዛሬ ትምህርት የተጠቀሙበት የትምህርት መርጃ መሣሪያ ለነገውና በተከታታይ ለሚቀርቡት ትምህርቶች መሠረት ጣይና አጎላማሽ ይሆናል እንጂ፣ ዛሬ በአንድ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ተጠቅሞ ለነገውና ለሚቀጥሉት ተከታታይ ትምህርቶች እንደማያገለግሉ ተቆጥሮ መጣላቸው ጉዳት እንጂ ጥቅም ስለሌለው በዚህ ረገድ ማሻሻያ ቢደረግ፤

ሠ. የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ የተለያዩ ሥልጠናዎችን ማዘጋጀትና እንዲሳተፉ ማድረግ እንጂ የመጠቀም ኃላፊነቱን የሙያ ሥራ በመሆኑ ለመምህራኑ ለራሳቸው ቢተው፤

ረ. በየትምህርት ቤቱ የቋንቋ መማሪያ ክፍል ከተሟላ ወንበር ጋር ቢዘጋጅ፤ ትምህርት ቤቶችም ለዚህ ተግባር ሁኔታዎችን ቢያመቻቹ እና መምህራን በዕርዳታ የሚያገኙትን ገንዘብ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ቅድሚያ ለቀረፁት ዓላማ እንዲያውሉት ቢያደረግ፤

ሰ. የተለየ የቋንቋ መማሪያ ክፍል በማዘጋጀት መምህራን በቀላሉ ሊያገኛቸውና ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ ሰሌዳዎች ቢሟሉ፤ በዚህም ሁኔታ የተለያዩ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በሠሌዳዎቹ ላይ በመለጠፍና በመስቀል በሥርአት በማደራጀት መጠቀም ቢቻል፤

ሸ. የሚመለከታቸው የትምህርት የበላይ አካላት በየትምህርት ቤቱ በቂ የቋንቋ የትምህርት ማስተማሪያ መሣሪያዎች (መርሐ-ትምህርት፣ የመምህሩ መምሪያና የተማሪ መጽሐፍ) በተቻለ መጠን በወቅቱ ለትምህርት ቤቶቹ በተገቢ መንገድ እንዲደርስ ቢያደርጉ፤

ቀ. መምህራን የሚገለገሉባቸውን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመጠቀም ተማሪዎች የእርስ በርስ መስተጋብራቸውና የክፍል ውስጥ ተሳትፏቸው እንዲጨምር መምህራን በብቃት ተገቢ የሆነ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም ዕውቀት እንዲኖራቸው የተለያዩ ጥረቶችን ቢያደርጉ ትምህርት ቤቱም ሁኔታዎችን ቢያመቻች እና መምህራንም ከአቻ ትምህርት ቤት መምህራን ጋር የልምድ ልውውጥ ቢያደርጉ፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


በድሉ ዋቅጅራ፡፡ 1996፡፡ *በሥነጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር፡፡* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ባየ ይማም፡፡ 2000፡፡ *የአማርኛ ሰዋስው፡፡* አዲስ አበባ፣ እሌኒ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፡፡

ተስፋዬ አበራና ማረው አለሙ፡፡ 1993፡፡ *አማርኛ ቋንቋን በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የማስተማር ዘዴ፡፡* ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ፋኩልቲ፣ የአማርኛ ትምህርት ክፍል ለልዩ ዲግሪ ፕሮግራም የርቀት ትምህርት የተዘጋጀ፡፡ (*ያልታተመ*)

ትምህርት ሚኒስቴር፡፡ 1994፡፡ *የትምህርት ፖሊሲና አተገባበሩ፡፡* አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ.፡፡

አለም እሸቱ፡፡ 1995፡፡ *በሁለተኛ ቋንቋ የማስተማሪያ ዝግጅት ሂደት ውስጥ የክህሎች አደረጃጀትና ትኩረት የሚሹ ይዘቶች አወቃቀር።* አዲስ አበባ፣ ከጥቅምት 22-25/1995 ለአማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የተዘጋጀ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍሎች መርሐ ትምህርቶች ለማሻሻል የተዘጋጀ አውደ ጥናት የቀረበ ከሥ/ት/ዝ/ጥ/ም ኢንስቲትዩት፡፡ (*ያልታተመ*)

ጌታቸው ለገሠ፡፡ 1992፡፡ *በአዲስ አበባ መስተዳድር ለ7ኛ ክፍል የማተላለፈው አጋዥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የቋንቋውን ትምህርት ጥራት በማሻሻል ሊያበረክት የሚችለው አስተዋጽኦ፡፡* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ አማርኛን በማስተማር ስነ ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ (*ያልታተመ*)

ጎንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ፡፡ 1997፡፡ *የአማርኛ ቋንቋ የተማሪው መማሪያ መፅሐፍ ሰባተኛ ክፍል*፡፡ አዲስ አበባ፣ *ሜጋ* አሳታሚ ድርጅት፡፡

ጎንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ፡፡ 1997፡፡ *የአማርኛ ቋንቋ የተማሪው መማሪያ መፅሐፍ ስምንተኛ ክፍል*፡፡ አዲስ አበባ፣ *ሜጋ* አሳታሚ ድርጅት፡፡

የቋንቋዎች ት/ሥ/ት/ዝ/ቡድን፡፡ 1996፡፡ *የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል* (ተሻሽሎ የተዘጋጀ)፡፡ አዲስ አበባ፣ ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም ኢንስቲትዩት፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ 2006፡፡ *የምርምር መሠረታዊ መርሖዎችና አተገባበር፡፡* አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚዎች፡፡

Aggarwal, J. 1995 *Essentials of Educational Technology: Teaching Learning Innovations in Education.* New-Delhi: Vikas Publishing House.

Aggarwal, J. 1996 *Principles, Methods and Techniques of Teaching*. New-Delhi: Vikas Publishing House.

Allen, V. 1983 *Techniques in Teaching Vocabulary*. Oxford: Oxford University Press.

Amare Asgedom 1998. *Teacher's Perceptions of Educational Problems in Ethiopia*. In Quality Education in Ethiopia: Vision for the 21 first century. Proceedings of National Conference held in Awassa College of Teacher Education, July, 12-18 1998.

Ashby, E. and Besse, M. 1972 *The Fourth Revolution-Instructional Technology in Higher Education*. New York: McGraw-Hill Co.

Atkins, J. et al. 1996 *Skills Development methodology Part 2.* Addis Ababa: Addis Ababa University Press.

Bestate Terefe 2000 *Application of Instructional Materials in the Primary School of the SNNPR*. Unpublished Master's Thesis, Addis Ababa University, Faculty of Education, Addis Ababa.

Best, J. & Kahn, J. 2003 *Research in Education*. ($9^{th}$ ed.) New Delhi: Prentice Hall.

Bowen, B. M. 1982. *Look Here! Visual Aids in Language Teaching*. Hong Kong: Macmillan Publishers Ltd.

Burns, K. et al. 1999 *Teaching Reading: In Today's Elementary Schools*. ($7^{th}$ ed.) New York: Houghton Mittlin Company.

Celce-Murcia, M. (ed.) 1991 *Teaching English as a Second or Foreign Language.* Los Angeles: Heinle and Heinle Publishers.

Clark, L. and Irving, S. 1996 *Secondary and Middle Schools Teaching Method.* ($7^{th}$ ed.) New Jersey: Prints-Hall.

Cook, V. 1996 *The Study of Language*. Cambridge: Cambridge University Press.

Corder, S. 1975 *Applied Linguistics and Language Teaching*. In Allen, J & Corder, S. (Eds.). *Papers in Applied Linguistics.* (Vol. 2) Oxford: Oxford University Press. PP. 42-51.

Cunningworth, A. 1989 *Evaluating and Selecting EFL Teaching Materials*. Oxford: Oxford University Press.

Day, R. 1990 *Teacher Observation in Language Education*. In J.C. Richards and D. Nunan (Eds), *Language Teacher Education*. Cambridge: Cambridge University Press. PP. 66-72.

Dubin, F. and Olshtain, E. 1986 *Course Design Developing Programs and Materials for Language Learning*. Cambridge: Cambridge University Press.

Farrant, J. 1984 *Principles and Practices of Education*. London: Longman Group Ltd.

Gagne, R. et al. 1992 *Principles of Instructional Design*. (4th ed.) Orlando: Harcourt Brace Jovanovich College Press.

Gower, R. and Walters, S. 1983. *Teaching Practices Handbook.* London: Heinemann.

Grains, R. and Redman, S. 1986 *Working with Words*: *A Guide to Teaching Vocabulary*. Cambridge: Cambridge University Press.

Grant N. 1987 *Making the Most of Your Text Book*. London: Longman Group Ltd.

Harmer, J. 2001 *The Practice of English Language Teaching*. London: Pearson Educational Limited.

Harrison, R. H. and Gowin, L. E. 1995 *The Elementary Teacher In Action*. Sanfransisco: Wadsworth Publishing Company Inc.

Heinich, R. et al. 1996 *Instructional Media and Technologies for Learning*. (5th ed), New Jersey: Prentice–Hall.

Hittleman, D. 1988 *Development Reading, K-8: Teaching From a Whole Language perspective.* (3rd ed.). Columbus: Merrill Publishing Company.

Hutchinson, T. and Waters, A. 1987 *English For Specific Purposes: A Learning Centered Approach*. Cambridge: Cambridge University Press.

I.C.D.R. 1989 *Source Book in the Preparation of Low Cost Teaching Materials For Primary and Junior Geography*. Addis Ababa: M.O.E and Goethe Institute.

Kieffer, R. and Lee, W. 1974 *Manual of Audio Visual Techniques*. New Jersey: Prints-Hall.

Malawi Institute of Education. 2003 *Continuous Assessment: A Training Manual for Educators in Malawi*. Domasi: Malawi Institute of Education.

McArthur, T. 1989 *Foundation Course for Language Teachers*. Cambridge: Cambridge University Press.

McDonough, J. and Shaw, C. 1993 *Materials and Methods in ELT: A Teachers Guide*. Oxford: Blackwell.

Nacino-Brown, R. et al. 1982 *Curriculum and Instruction-An Introduction to Methods of Teaching*. New Delhi: Vikas Publishing House.

Newby, J. et al. 1996 *Instructional Technology for Teaching and Learning*. New Jersey: Prentice Hall.

Nkuuhe, J. 1995 *Instructional Media*. In Barbara, M. et al. (Eds.). *Teach Your Best: A Hand Book for University Lecturers*. Nairobi: Integrated System Ltd. PP. 66-79.

Nunan, D. 1991 *Language Teaching Methodology: A Text Book for Teachers*. New York: Prints-Hall International.

Nunan, D. 1988 *Syllabus Design*. Oxford: Oxford University Press.

Nuttall, C. 1982 *Teaching Reading Skill in A Foreign Language*. London: Heinemann Educational Book Ltd.

Quist, D. 2000 *Primary Teaching Methods*. Oxford: Macmillan Publishers Limited.

Richard, J. and Rodgers, T. 1986 *Approaches and Methods in Language Teaching* (11th ed.). Cambridge: Cambridge University Press.

Romiszowski, A. 1988 *The Selection and Use of Instructional Media*. London: Kogan Private Ltd.

Sheldon, L. E. (ed.). 1987 *ELT Textbook and Materials, Problems in Evaluation and Development*. London: Modern English Publications.

Stern H. H. 1991 *Issues and Options in Language Teaching*. Oxford: Oxford University Press.

Tucker, R. N. 1979 *The Organization and Management of Educational Technology*. London: Croom Helm.

Ur. P. 1996 *A Course in Language Teaching: Practice and Theory*. Cambridge: Cambridge University Press.

Wallace, C. 1992 *Reading*. Oxford: Oxford University Press.

Widdowson, H. 1990 *Aspects of Language Teaching*. Oxford: Oxford University Press.

Wong, H. and Wong R. 1998 *How to be an Effective Teacher: The first Days of School*. Singapore: Harry K. Wong Publication Inc.

Wright, A. 1989 *Pictures for language Learning*. London: Longman.

Yalden, J. 1987 *The Communicative Syllabus: Evaluation Design and Implementation*. London: Prentice-Hall International.

# አባሪ "ሀ"

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
## የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ፅሁፍ ክፍለ ትምህርት
## አማርኛን የማስተማር ሥነዘዴ
## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

የቋንቋ መምህራንን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምን በተመለከተ

የክፍል ውስጥ ምልከታ መከታተያ ቅፅ

**ክፍል አንድ፡-** አጠቃላይ መግለጫ

1. ሀ. የትምህርት ቤቱ ስም ______________

   ለ. የክፍል ደረጃ ____________________

   ሐ. ክፍለ ጊዜ ______________________

   መ. ምልከታው የተካሄደበት ቀን ________ ወር _______ ዓ.ም.

**ክፍል ሁለት፡-** ዝርዝር መረጃዎች

2. የመንፈቀ ዓመቱ የትምህርት ዕቅድ ሀ. ተዘጋጅቷል ለ. አልተዘጋጀም
3. የዕለቱ የትምህርት ዕቅድ ሀ. ተዘጋጅቷል ለ. አልተዘጋጀም
4. የመንፈቅ ዓመቱና የዕለቱ ትምህርት ዕቅድ

   ሀ. በትክክል ይጎዛሉ ለ. አይጎዙም
5. በመንፈቀ ዓመቱ ዕቅድ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

   ሀ. ተጠቅሰዋል ለ. አልተጠቀሱም
6. በዕለቱ የትምህርት ዕቅድ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

   ሀ. ተጠቀሰዋል ለ. አልተጠቀሱም
7. የመንፈቀ ዓመቱ እቅድ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተጠቅሰው ከሆነ ከዕለቱ የትምህርት ዕቅድ መርጃ መሣሪያዎች ጋር ይመሳሰላሉ

   ሀ. ይመሳሰላሉ ለ. አይመሳሰሉም

8. በዕለቱ ትምህርት መምህሩ/ርትዋ የተጠቀሙባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

ሀ. ____________________

ለ. ____________________

ሐ. ____________________

መ. ____________________

9. የዕለቱ ትምህርት ዝርዝር ዓላማዎች

ሀ. ____________________

ለ. ____________________

ሐ. ____________________

10. መምህሩ/ርትዋ/ የዕለቱ ትምህርት የተጠቀሙበትን የትምህርት መርጃ መሣሪያ ለመጠቀም በአጋዥነት ያገለገሏቸው ምንድን ነው?

ሀ. የመምህሩ መምሪያ ለ. መርሐ ትምህርት

ሐ. መምህሩ ከነበራቸው ልምድ በመነሳት ያለምንም አጋዥ (ጠቋሚ) መረጃ ነው የተጠቀሙ

መ. ከመምህሩ መምሪያ፣ ከመርሐ ትምህርቱ የተጠቆሙትን ከራሳቸው ልምድ ጋር በማዋሀድ ነው የተጠቀሙት፡፡

11. መምህሩ /ርትዋ/ የተጠቀሙባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የዕለቱን ትምህርት ዝርዝር ዓላማዎች ከማሳካት አኳያ ያላቸው ተገቢነት?

ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ለ. በጣም ጥሩ ነው

ሐ. ጥሩ ነው መ. አነስተኛ ነው

12. በዕለቱ መምህሩ /ርትዋ/ የተጠቀሙበትን የትመህርት መርጃ መሣሪያዎች የተገኙት እንዴት ነው?

ሀ. ተገዝተው ነው ሐ. ከአካባቢ ከሚገኙ ቁሳቁሶች የተዘጋጁ ናቸው

ለ. በስጦታ መልክ ነው መ. ከትምህርት ቤቱ የተገኙ ናቸው

12.1 ተገዝተው ለአገልግሎት የዋሉ ከሆነ ማን ገዛቸው? ____________________

12.2 ከአካባቢ ከሚገኙ ቁሳቁሶች የተዘጋጁ ከሆነ ማን አዘጋጃቸው? __________

13.3 በስጦታ መልክ የተገኙ ከሆነ ከማን? ____________________

13. በዕለቱ መምህር/ርትዋ/ የተጠቀሙበት የትምህርት መርጃ መሣሪያ መጠን?

ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ነው ሐ. ጥሩ ነው

ለ. በጣም ጥሩነው መ. አነስተኛ ነው

14. በዕለቱ መምህሩ/ርትዋ/ የተጠቀሙበት የትምህርት መርጃ መሣሪያ ጥራት?

ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ነው ሐ. ጥሩ ነው

ለ. በጣም ጥሩነው መ. አነስተኛ ነው

15. በዕለቱ መምህሩ/ርትዋ/ የተጠቀሙበት የትምህርት መርጃ መሣሪያ ለዕለቱ ትምህርት ተስማሚነቱ ምን ያህል ነው?

ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ነው ሐ. ጥሩ ነው

ለ. በጣም ጥሩነው መ. አነስተኛ ነው

16. በዕለቱ መምህሩ/ርትዋ/ የተጠቀሙበት የትምህርት መርጃ መሣሪያ ዓይነቱ ከየትኛው ዓይነት ይመደባል?

ሀ. ዕይታዊ ለ. ድምፃዊ ሐ. ድምፃዊ ወዕይታዊ

17. የመምህሩ/ርትዋ/ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ የመጠቀም ብቃታቸው?

ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ነው ሐ. ጥሩ ነው

ለ. በጣም ጥሩነው መ. በቂ ነው ሠ. አነስተኛ ነው

18. በዕለቱ አገልግሎት ላይ የዋለው የትምህርት መርጃ መሣሪያ ምንን ለማስተማር ነው?

ሀ. የንባብ ክሂልን ሐ. የመፃፍ ክሂልን ሠ. ቃላትና ሰዋስውን

ለ. የማዳመጥ ክሂል መ. የመናገር ክሂልን ረ. ክሂሎችን በቅንጅት

19. ተማሪዎች በትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ በመጠቀም የሚያሳዩት የክፍል ውስጥ ተሳትፎ (participation) ምን ይመስላል?

ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ነው ሐ. ጥሩ ነው

ለ. በጣም ጥሩነው መ. አነስተኛ ነው

20. ተማሪዎች በትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ በመጠቀም የሚያሳዩት የዕርስ በርስ መስተጋብር (Interaction) ምን ያህል ነው?

ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ነው		ሐ. ጥሩ ነው

ለ. በጣም ጥሩነው		መ. አነስተኛ ነው

21. የዕለቱ የትምህርት መርጃ መሣሪያ የመማር ማስተማር ሂደቱን ተማሪ ተኮር ለማድረግ ያለው እገዛ?

ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ነው		ሐ. ጥሩ ነው

ለ. በጣም ጥሩነው		መ. አነስተኛ ነው

22. በዕለቱ የቀረበው የትምህርት መርጃ መሣሪያ ማራኪነት?

ሀ. ሁሉም ተማሪዎች የደስታ ስሜት ይታይባቸዋል

ለ. አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የደስታ መንፈስ ይታይባቸዋል

ሐ. ግማሽ ያህሉ የደስታ መንፈስ ይታይባቸዋል

ሠ. ሁሉም ተማሪዎች የደስታ መንፈስ አይታይባቸውም

23. ተማሪዎች በዕለቱ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ የተማሩትን ትምህርት በክፍለ ጊዜው መጨረሻ መምህሩ ለሚጠይቃቸው ጥያቄዎች የሚሰጡት ምላሽ?

ሀ. እጅግ በጣም ፈጣን ነው		ለ. በጣም ፈጣን ነው

መ. ዝቅተኛ ነው		ሠ. በጣም ዝቅተኛ ነው

# አባሪ "ለ"

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
## የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ፅሁፍ ክፍለ ትምህርት
## አማርኛን የማስተማር ሥነዘዴ
## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

በ2001 ዓ.ም. በሁለተኛ ወሰነ ትምህርት በጎንደር ከተማ አስተዳደር አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ዕርከን በሰባተኛ እና በስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላ የፅሁፍ መጠይቅ፡፡

**ውድ መምህር/ት**

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ዕርከን የሰባተኛ እና የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም መፈተሽና የታዩትን ችግሮች መርምሮ የመፍትሄ ሀሳብ ለመጠቆም ሲባል ለተዘጋጀው ጥናት መረጃ መሠብሰብ ነው፡፡ ጥናቱ ከተፈለገው ግብ እንዲደርስ ተገቢ መረጃዎችን መሰብሰብና ማጠናከርን ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም መልስዎትን በማያሻማ መልኩ በተሰጠው ቦታ ላይ እንዲያሰፍሩልኝ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

<u>ማሳሰቢያ</u>

- በመጠጥቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡
- ጥናቱ ውጤታማ ይሆን ዘንድ የርስዎ ድርሻ ከፍተኛ በመሆኑ ትክክለኛ መረጃ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡
- በመጠይቁ ላይ የሰፈሩትን ጥያቄዎች ከሌላ ሰው በመነጋገር መሙላት በጥናቱ ውጤት ላይ ተፅዕኖ ስለሚያሳድር ብቻዎትን ይሙሉት፡፡
- ከተነሱት ጥያቄዎች ሌላ ተጨማሪ ሀሳብ ካለዎት በመጠይቁ መጨረሻ ላይ ማስፈር ይችላሉ፡፡
- የሚያሰፍሯቸው መረጃዎች በሙሉ መጠይቁ ከተዘጋጀበት የጥናት ዓላማ ውጭ ለምንም ነገር አይውሉም፡፡

ውድ ጊዜዎን ሰውተው ተገቢውን መረጃ ሊሰጡ ፈቃደኛ በመሆንዎ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ሚያዚያ 2001 ዓ.ም.

**ክፍል አንድ፡- የግል ሁኔታ መግለጫ፣**

1. የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ____________________
2. ፆታ ሀ. ሴት ለ. ወንድ
3. የአገልግሎት ዘመን

   ሀ. ከ1-5 ለ. ከ6-10 ሐ. 11-15 መ. ከ16 ዓመት በላይ
4. የትምህርት ደረጃ

   ሀ. የምስክር ወረቀት /መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም ሐ. ዲፕሎማ

   ለ. የ12ኛ +1ኛ ዓመት የኮሌጅ ትምህርት መ. ዲግሪ
5. በኮሌጅ ደረጃ ሰልጥነው ከሆነ የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት /ዐቢይ ____ ንዑስ ______
6. የተመረቁበት ዓ.ም. ______________
7. የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ

   ሀ. 7ኛ ለ. 8ኛ ሐ. 7ኛ እና 8ኛ መ. ሌላ ካለ ይግለፁ
8. በሳምንት ውስጥ ምን ያህል ክፍለ ጊዜያት ያስተምራሉ?

   ሀ. ከ10 በታች ለ. ከ11-15 ሐ. ከ16-19 መ. ከ20-24 ሠ. ከ25 በላይ

**ክፍል ሁለት**፡- ዝርዝር መረጃዎች

9. የትምህርት መርጃ መሣሪያን የሚመለከት ትምህርት ራሱን የቻለ አንድ ኮርስ ሆኖ ተምረውታል?

   ሀ. ተምሬያለሁ ለ. አልተማርኩም ሐ. ትምህርቱም ራሱ መኖሩን አላውቅም
10. በቅድመ ሥራ ላይ ሥልጠና ኮርሱን ወሰደው ከሆነ ስለትምህርት መርጃ መሣርያ አጠቃቀም በቂ የሆነ ተግባሪዊ ልምምድና ትምህርት ያገኙ ይመስልዎታል?

    ሀ. ይመሰለኛል ለ. አይመስለኝም ሐ. አስተያየት ለመስጠት ይከብደኛል
11. ለጥያቄ ተራ ቁጥር "10" መልስዎ ይመስለኛል የሚል ከሆነ ኮርሱ የትምህርት መርጃ መሣርያዎችን አጠቃቀም በሚመለከት ላለብዎት ኃላፊነት በብቃት አዘጋጅቶኛል ብለው ያስባሉ?

    ሀ. በከፍተኛ ደረጃ አዘጋጅቶኛል ሐ. ምንም አላዘጋጀኝም

    ለ. በመጠኑ አዘጋጅቶኛል መ. አላውቀውም

12. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የሚመለከት ትምህርት በኮርስ ደረጃ ተምረው ከሆነ ትምህርቱ ለማስተማር ሥራዎ የሚሰጠውን ጥቅም በሚገባ ያወቁት መቼ ነው?

ሀ. ትምህርቱን በምከታተልበት ጊዜ ሐ. አላስታውስም

ለ. ትምህርቱን ጨርሼ ወደ ሥራ ዓለም ከገባሁ በኋላ መ. ከተወሰነ ዓመት በኋላ

13. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በተመለከተ በሥልጠና ወቅት ኮርሱ ከተሰጠዎ ትምህርቱን በዕርጋታ ለመከታተል በወቅቱ በቂ ጊዜ አግኝተዋል?

ሀ. አግኝቻለሁ ለ. አላገኘሁም ሐ. ዛሬ ላይ አላስታወሰውም

14. በስልጠና ወቅት የትምህርትመርጃ መሣሪያዎችን አጠቃቀም የሚመለከት ፅሁፍ በተቀነባበረ መልኩ (Handout) በአሰልጣኝዎ ተሰጥቶዎታል?

ሀ. አዎ ለ. የለም ሐ. ሌላ መልስ ካለ ይግለፁ _____________

15. ለጥያቄ አስራ አራት መልስዎ "አዎ" የሚል ከሆነ ፅሁፉ በሥራዎ ላይ ምን ያህል ጠቀሞዎታል?

ሀ. እጅግ በጣም ለ. በጣም ሐ. በመጠኑ መ. ምንም አልጠቀመኝም

16. ለጥያቄ አስራ አራትመልስዎ "የለም" የሚል ከሆነ ስለትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የለዎትን ዕውቀት ከየት አገኙት?

ሀ. ከስራ ላይ ሥልጠና ለ. ከተለያዩ ጓደኞቼ

ሐ. ራሴ በማደርገው ጥረት መ. በልዩ ልዩ አጋጣሚና ከግል ተሞክሮ

17. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የሚመለከት የሰራ ላይ ስልጠና ተካፍለው ያውቃሉ?

ሀ. ለአንድ ጊዜ ያህል ተካፍያለሁ ለ. ከአንድ ጊዜ በላይ ተከፍያለሁ

ሐ. በጭራሽ አልተካፈልኩም

18. ለጥያቄ ተራ ቁጥር አስራ ሰባት መልስ "ተካፍዬ አውቃለሁ" የሚል ከሆነ ሥልጠናው የተዘጋጀው?

ሀ. በትምህርት ቤት ደረጃ ለ. በወረዳ ጽህፈት ቤት ደረጃ

ሐ. በዞን ጽህፈት ቤት ደረጃ

19. በአሁኑ ሰዓት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አጠቃቀ በሚመለከት በቂ ዕውቀትና ችሎታ ያለዎት ይመስልዎታል?

ሀ. ከበቂ በላይ አለኝ ለ. በቂ አለኝ

ሐ. በቂና ችሎታ የለኝም መ. ምንም ዕውቀት የለኝም

20. በዕርስዎ አመለካከት የመማር ማስተማሩን ሂደት ስኬታማ ለማድረግ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚጫወቱት ምን ያህል ነው?

ሀ. በጣም ከፍተኛ ሚና ሐ. ዝቅተኛ ሚና

ለ. ከፍተኛ ሚና መ. ምንም ሚና የለውም

21. ትምህርት ቤትዎ ከፋብሪካ የሚገኙ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለመጠቀም የበጀት ችግር አለበዎት?

ሀ. በተወሰነ ደረጃ ችግር አለ ሐ. መኖር አለመኖሩን አላውቅም

ለ. በጣም ችግር አለ መ. ምንም ችግር የለም

22. ተማሪዎች በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ታግዘው ሲማሩ የአቀባበልና የማስታወስ ችሎታቸው ከፍ ይላል ብለው ያምናሉ?

ሀ. በጣም አምናለሁ ሐ. በፍፁም አላምንም

ለ. በመጠኑ አምናለሁ መ. ለመወሰን ያስቸግራል

23. ከትምህርት ቤትዎ ውጭ ካሉ ምንጮች ልዩ ልዩ ለትምህርት መርጃ መሣሪያ የሚያግዙ መሣሪያዎችን ለመግዛት የሚያስችል በጀት በስጦታ መልክ ለማግኜት ምን ያህል ጥረት እያደረጉ ነው?

ሀ. በጣም በርካታ ጥረት ሐ. አነስተኛ ጥረት

ለ. መካከለኛ ጥረት መ. ምንም ጥረት አላደረግሁም

24. በመምህራን መገምገሚያ ላይ የትምህርት መርጃ መሣሪያን መጠቀም የሚመለከት ነጥብ መካተቱ ተገቢ ነው ይላሉ?

ሀ. በጣም ተገቢ ነው ሐ. በተወሰነ ደረጃ ተገቢነት ይኖረዋል

ለ. ተገቢነት የለውም መ. ለመወሰን እቸገራለሁ

25. በትምህርት ቤትዎ ውስጥ የትምህርት ማሰራጫ ሬዲዮ አለ?

ሀ. አዎ አለ ለ. የለም

ሐ ቢኖርም ተበላሽቷል መ. አለ ነገር ገን ለቋንቋ ትምህርት አያገለግልም

26. በትምህርትቤትዎ ውስጥ ከሬዲዮ ሌላ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች አሉ?

ሀ. አዎ አሉ ሐ. አሉ ነገር ግን አገልግሎት አይሰጡም

ለ. የሉም መ. ለትምህርት መርጃ መሣሪያ አገልግሎት አይሰጡም እንጂ አሉ

27. ትምህርት ቤትዎ በቴክኖሌጅ ውጤቶች ለመጠቀም ያለው አመችነት ምን ያህል ነው?

ሀ. ከፍተኛ ነው ለ. መጠነኛ ነው ሐ. ምንም ምቹነት የለውም

28. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምን በሚመለከት ያጋጠመዎት ችግር አለን?

29. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምን በሚመለከት ከመምህራን ምን ይጠበቃል?

30. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምን በሚመለከት ለወደፊቱ አስፈላጊ ነው የሚሉትን ሀሳብ ያስፍሩ?

# አባሪ “ሐ”

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሑፍ ክፍለ ትምህርት

## አማርኛን የማስተማር ሥነ ዘዴ

## የድኅረ ምረቃ መረሐ ግብር

በጎንደር ከተማ አስተዳደር የ1ኛ ደረጃ 2ኛ እርከን ሰባተኛና ስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር የተደረጉ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች

1. የሰለጠኑበት ተቋም የት ነው

   ሀ. ኮሌጅ ለ. ዩኒቨርሲቲ ሐ. ሌላ ካለ ይግለፁ

2. የአገልግሎተ ዘመንዎ ሰንት ነው ___________________

3. በክፍል ውስጥ የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ብዛት በአማካይ ምን ያህል ናቸው? ________________

4. በሰለጠኑበት ተቋም (ኮሌጅ) ትምህርት መርጃ መሣሪያን የሚመለከት ኮርስ ራሱን ችሎ ወሰደዋል?

   ሀ. አዎ ለ. የለም

5. ለተራ ቁጥር አራት ጥያቄ መልስዎ አዎ ከሆነ ወደ ሥራ ከተሰማሩ በኋላ ያደረገለዎት እገዛ?

   ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ለ. በጣም ጥሩ ነው ሐ. ጥሩ ነው
   መ. መጠነኛ ነው ሠ. ምንም አላገዘኝም

6. በትምህርት መርጃ መሣሪያ ተጠቅሞ ማስተማር ጠቀሜታ አለው ብለው ያስባሉ?

7. የቋንቋውን ትምህርት በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ አስደግፎ ማቅረብ ለተማሪው፣ ለመምህሩ ይጠቅማል? ለምን?

8. የትምህርት መሣሪያዎች (የመምህሩ መምሪያ፣ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍና መርሐ ትምህርቱ) በትምህርት መርጃ መሣሪያ ለመጠቀም እገዛ አላቸው? ለምን?

9. እርስዎ የበለጠ ያግዘኛል ብለው የሚጠቀሙበት የትምህርት መሣሪያ (መርሐ ትምህርት፣ የመምህሩ መምሪያ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ) የትኛው ነው በሚገባ ያግዘኛል የሚሉት?

10. የሚጠቀሙባቸውን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚያገኙት ከየት ነው? እንዴት ያገኛቸዋል?

11. በማስተማር ሙያ ላይ እያሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያን በተመለከተ የሙያ ላይ ስልጠና አግኝተዋል በማን አዘጋጅነት?

12. ስለትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም በመምህራን መገምገሚያ ስለመስፈሩ ያለዎት አስተያየት ምንድን ነው?

13. በመማር-ማስተማር ሂደት በትምህርት መርጃ መሣሪያ ከተገለገሉ በኋላ የዕለቱ ትምህርት ለተማሪዎች ግልፅ መሆኑን እንዴት ያውቃሉ?

14. በትምህርት ቤቱ ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚተላለፍበት ሬዲዮ አለ? ለምን አገልግሎት ይውላል? ሌላ የቴክኖሎጂ ውጤት አለ?

15. በትምህርት ቤትዎ ውስጥ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም የሚያገለግሉ ከሬዲዮ ሌላ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች (ለድምፃዊ፣ ለድምፃዊና ወዕይታዊ) የሚያገለግሉ መሣሪያዎች አሉ?

16. ለጥያቄ ተራ ቁጥር 15 መልስዎ አዎ ከሆነ እንዴት ተገኙ? ማን ገዛቸው?

17. በትምህርት ቤትዎ የትምህርት መርጃ መሣሪያን ለመጠቀም የሚያገዙ የተመቻቹ የቴክኖሎጂ ውጤቶች አሉ?

18. የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ በትምህርት ቤትዎ ሃሳብ የሚለዋወጧቸው መምህራን አሉ? በሙያዎት ላይስ ምን ያህል እገዛ አድርጓል?

19. ለእለቱ የትምህርት ይዘት አስፈላጊ ነው ብለው የተጠቀሙበት የትምህርት መርጃ መሣሪያ ተማሪዎችዎን ግራ ያጋባበት ጊዜ ይኖራል? የለም ካሉ ያላጋጠመዎት ለምን ይመስለዎታል?

20. የአማርኛ ቋንቋን የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ ያጋጠመዎት ችግር አለ?

21. አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙበት የትምህርት መርጃ መሣሪያ አይነት ምን አይነት ነው? ለምን?

22. አብዛኛውን ጊዜ የትምህርት መርጃ መሣሪያ የሚጠቀሙት የትኛውን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ለማስፈፀም ነው? ለምን?

23. ለወደፊቱ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ መሆንና መደረግ ስለአለበት ሁኔታ ያለዎት አስተያየት ምንድን ነው?

# አባሪ "መ"

**ከካሴት ወደ ፅሁፍ የተመለሰ የመምህራን የቃለ መጠይቅ ምላሽ**

**ሠንጠረዥ ሀ ቃለ መጠይቁ የፈጀው የጊዜ መጠንና የተደረገበት ቀን**

| ታላሚዎች | $መ_1$ | $መ_2$ | $መ_3$ | $መ_4$ | $መ_5$ | $መ_6$ | $መ_7$ | $መ_8$ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን | 29/8/2001 | 29/8/2001 | 22/8/2001 | 22/8/2001 | 15/8/2001 | 15/8/2001 | 6/9/2001 | 6/9/2001 |
| ቃለመጠይቁ የፈጀው ጊዜ | 7፡00-7፡25 | 7፡35-8፡00 | 7፡30-7፡58 | 8፡15-8፡47 | 7፡15-7፡45 | 8፡00-8፡37 | 10፡20-10፡50 | 9፡18-10፡01 |

**ጥያቄ አንድ**፡- የሰለጠኑበት ተቋም የት ነው?

ሀ. ኮሌጅ ለ. ዩኒቨርሲቲ ሐ. ሌላ ካለ ይገለፅ

መ1፡- እስከ መ5፣ መ7፣ መ8 ኮሌጅ

መ6፡- ተቋምና ኮሌጅ

**ጥያቄ ሁለት**፡- የአገልግሎት ዘመንዎ ስንት ነው?

መ1፡- ሰላሳ

መ2፡- ሃያ ዘጠኝ

መ3፡- ሰላሳ ሁለት

መ4፡- ሰላሳ ሦስት

መ5፡- ሃያ ስድስት

መ6፡- ሃያ ሦስት

መ7፡- ሃያ ሁለት

መ8፡- ሃያ አንድ

**ጥያቄ ሦስት**፡- በክፍል ውስጥ የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች በአማካይ ምን ያህል ናቸው?

መ1 እና መ2 ስልሳ አምስት

መ3 እና መ4፡- ስልሳ

መ5 እና መ6 ሃምሳ አምስት

መ7 እና መ8 ሃምሳ ስምንት

**ጥያቄ አራት**፡- በሰለጠኑበት ተቋም (ኮሌጅ) ትምህርት መርጃ መሣሪያን የሚመለከት ኮርስ ራሱን ችሎ ወስደዋል?

ሀ. አዎ ለ. የለም

መ1 እስከ መ8 የለም

**ጥያቄ አምስት**፡- በተራ ቁጥር 4 መልስዎ "አዎ" ከሆነ ወደ ሥራ ከተሰማሩ በኋላ ያደረገለዎት እገዛ?

ሁሉም የለም ስላሉ አልተጠየቁም፡፡

**ጥያቄ ስድስት**፡- በትምህርት መርጃ መሣሪያ ተጠቅሞ ማስተማር ጠቀሜታ አለው ብለው ያሰባሉ?

መ1፡- አዎ፡- በሚገባ አለው፡፡

መ2፡- አዎ አለው፡፡

መ3፡- ኧ . . . በደንብ አለው፡፡

መ4፡- በሚገባ አለው፡፡

መ5፡- አዎ ጠቀሜታ አለው፡፡

መ6፡- አዎ ኧ . . . ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

መ7፡- አዎ በሚገባ ጠቀሜታ አለው፡፡

መ8፡- አዎ አስባለሁ፡፡

**ጥያቄ ሰባት**፡- የቋንቋውን ትምህርት በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ አስደግፎ ማቅረብ ለተማሪው፣ ለመምህሩ ይጠቅማል? ለምን?

መ1፡- ኧ . . . አዎ ይጠቅማል ምክንያቱም . . . ለተማሪው ትምህርቱን በቀላሉ እንዲረዳው ያግዛል፡፡ ለመምህሩም ጊዜውን፣ ጉልበቱን ይቆጥብለታል፡፡

መ2፡- አዎ ትልቅ ጠቀሜታ ለሁለቱም አለው፡፡ ለተማሪው ማዬት ማመን ነውና እያየና እየሰራ መማሩ ትልቅ ጠቀሜታ አለው፡፡ ለመምህሩም ለግምገማው ያገለግለዋል፡፡

መ3፡- አዎ ለመምህሩም ሆነ ለተማሪው የጎላ ጥቅም አለው፡፡ ምክንያቱም መምህሩ ተማሪውን በተግባር እየተሳተፈ እንዲማር ሲያደርገው የትምህርቱን ዓላማ በግልፅ በቀላሉ ተማሪው እንዲረዳው ያግዘዋል፡፡

መ4፡- ከፍተኛ እገዛ ለሁለቱም አለው። ኸ . . . ምክንያቱም ለመምህሩ ጊዜውንና ጉልበቱን በአግባቡ እንዲገለገል ያደርገዋል ለተማሪው በተግባር እንዲማር ስለሚያግዘው ትምህርቱ ግልፅ ቀላል እንዲሆን ያግዘዋል።

መ5፡- አዎ ኸ . . . ለመምህሩም ሆነ ለተማሪው ያላቸው ጠቀሜታ እጅግ ከፍተኛ ነው። ለተማሪው ትምህርቱን በግልፅ ቀለል ባለ መንገድ በዕውነተኛ ነገርና በተመሳሳይ ነገር ወክሎ እንዲማር ስለሚያግዘው ለመምህሩ ደግሞ ከጊዜና ከጉልበት አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው።

መ6፡- አዎ የጎላ ጠቀሜታ ለግራ ቀኙ አላቸው ምክንያቱም ለተማሪው ትምህርቱን ግልፅ ተጨባጭ እንዲሆን ያግዘዋል ለመምህሩም ለተማሪዎም ትምህርቱን ግልፅ ለማድረግ በቃል ሲያስተምር የሚፈጀው ጊዜ ብዙ በመሆኑ ከጊዜ አንፃር ትልቅ ጠቀሜታ አለው።

መ7፡- ኸ . . . አዎ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። ከሁሉም የበለጠ መምህሩ ተጠቃሚ ነው ምክንያቱም ለመምህሩ የተማሪዎቹ ፍላጎት ተሳትፏቸው ሲጨምርና ውጤታማ ሲሆኑ ሲመለከት የመምህሩ ተሳትፎ ይጨምራል። ኸ . . . ጉልበቱን ይቆጥባል ተማሪዎች በተግባር ተሳታፊ ስለሚሆኑ ለቋንቋው ትምህርት ጥሩ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያግዛል።

መ8፡- አዎ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ለመምህሩ ፍላጎት በመቀስቀስ፣ ጊዜና ጉልበቱን በመቆጠብ በኩል ትልቅ አስተዋፅኦ አላቸው።

**ጥያቄ ስምንት**፡- የትምህርት መሣሪያዎች (የመምህሩ መምሪያ፣ የተማሪ መፅሐፍ እና መርሃ ትምህርት) በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለመጠቀም እገዛ አላቸው? ለምን?

መ1፡- አዎ፡- የማስተማሪያ መሣሪያዎቹ እጅግ በጣም ከፍተኛ እገዛ አላቸው ለምን ለሚለው መርሃ ትምህርቱና የመምህሩ መምሪያ ምን ዓይነትና እንዴት ባለ ሁኔታ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያን መጠቀም እንደሚኖርብን ዓይነታቸውንና አጠቃቀሙን በመጠቆም በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ስላላቸው የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹን በቀላሉ ማግኜት የሚቻል ከሆነ የተጠቆመውን ስለምንጠቀም የተማሪው መጽሐፍም በጥንድ፣ በቡድንና በተናጠል ምንን እንዴት መጠቀም እንዳለብን ሰለሚጠቁም ለአጠቃቀም እጅግ ከፍተኛ ዕገዛ አላቸው።

መ2፡- አዎ የማሥተማሪያ መሣሪያዎቹ እጅግ በጣም ከፍተኛ ዕገዛ አላቸው ለምን ለሚለው የመምህሩ መምሪያና መርሃ ትምህርቱ ምን ዓይነትና እንዴት ባለ መልኩ በመማር-ማስተማር ሂደት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያን መጠቀም እንዳለብን

ስለሚያመላክቱና፤ ይህንንም በቀላሉ ማግኜትና መጠቀም ከቻልን ዓይነታቸውንና አጠቃቀማችን ያመላከታሉ የተማሪው መጽሐፍም የተለያዩ መልመጃዎችን በየቋንቋ ትምህርት ዘርፎቹ ከፍሎ ስለሚያሳይ ጠቀሜታ አለው፡፡

መ3፡- አዎ ኧ . . . ለምን ለሚለው መርሐ ትምህርቱ ሁሉንም አጠቃሎ ስለሚይዝ ሌሎቹ በደረጃቸው አስፈላጊ ቢሆኑም የበለጠ መርሐ ትምህርቱ መሪ ነውና ያስፈልጋል፡፡

መ4፡- አዎ እገዛ አላቸው ኧ . . . ይቅርታ . . . መርሐ ትምህርቱና የመምህሩ መምሪያ ለመማር-ማስተማር ክንውን አስፈላጊ የሆኑትን ጊዜ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ በማመላከት በኩል ከፍተኛ እገዛ አላቸው የተማሪው መጽሐፍም ከእነዚህ የሚቀዳ ሲሆን መልመጃዎችን ክንውንን በማመላከት በኩል ለቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም ያለው እገዛ እጅ ከፍተኛ ነው፡፡

መ5፡- ኧ . . . አዎ ያለው እገዛ እጅግ በጣም ነው ለምን መሰለሽ ኧ . . . በተለይ የመምህር መምሪያ፣ መርሐ ትምህርት የመማር ማስተማሩን ክንውንና ይህ የሚታገዝበትን የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያን ዓላማውን ለማስፈፀም ከሚያገለግል ይዘት ጋር በግልፅ አስፍሮ ስለሚገኝ ዕገዛቸው ወደር የለውም የተማሪው መማሪያ መጽሐፍም ቢሆን የሚተገበሩ መልመጃዎችን የጥንድና የቡድን ውይይቶችን በማመላከት በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ በመታገዝ ትምህርቱን በንቃት መሳተፍ እንዲቻል በማድረግ የሚያግዙ ናቸው፡፡

መ6፡- አዎ እገዛ አላቸው፣ ለምን በተለይ የመምህሩ መምሪያና መርሐ ትምህርቱ አቅጣጫ ጠቋሚ በመሆናቸው የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያን እንዴት ለምን መጠቀም እንደሚገባ ስለሚያመላክቱ ሙሉ ዕገዛ አላቸው የተማሪ መጽሐፍም ቢሆን በደረጃ እንጅ አስፈላጊና እገዛ ያለው መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

መ7፡- ኧ . . . አዎ እገዛ አላቸው፣ ለምን ሁሉም የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በተሟላ መልኩ ከሌሉ የቋንቋው ትምህርት በትምህርት መርጃ መሣሪያ ሊደገፍ ቀርቶ የከሰመ መሆኑ ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡

መ8፡- አዎ ከፍተኛ እገዛ አላቸው፣ መርሐ ትምህርት፣ የመምህሩ መምሪያ የተማሪ መጽሐፍ ሁሉም በጥምረት ለቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ ለመጠቀም ምሰሶዎች ናቸው፡፡

**ጥያቄ ዘጠኝ**፦ እርስዎ የበለጠ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያን ለመጠቀም ያግዘናል ብለው የሚጠቀሙበት የትምህርት መርጃ መሣሪያ (መርሐ ትምህርቱ፣ የመምህሩ መምሪያ፦ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ) የትኛውን ነው?

መ1፦ አንዱ በተጓደለበት ሁኔታ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያን ተጠቅሞ ማስተማር አስቸጋሪ ነው፡፡

መ2፦ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያን በመጠቀም የቋንቋ ትምህርትን ለማስተማር ሁሉም የማስተማሪያ መሣሪያዎች መኖር አለባቸው፡፡

መ3፦ ኧ . . . የቋንቋ ትምህርትን በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ አስደግፎ ለመጠቀም ሁሉም የማሰተማሪያ መሣሪያዎች ሊኖሩ የግድ ነው፡፡

መ4፦ ቋንቋን በክፍል ውስጥ በትምህርት መርጃ መሣሪያ አጋዥነት ለማስተማር ሁሉም የማስተማሪያ መሣሪያዎች ሲኖሩ ውጤታማ መሆን ይቻላል፡፡

መ5፦ ኧ ሁሉም የማስተማሪያ መሣሪያዎች አስፈላጊና ወሳኝ ናቸው፡፡ በተለይ የትምህርት መርጃ መሣሪያን ለመጠቀምና የመማር ማስተማር ክንውኑን ለመምራት እጅግ ጠቃሚ ናቸው፡፡

መ6፦ ሁሉም የማስተማሪያ መሣሪያዎች ይጠቅማሉ አሁን የተጓደለ መሣሪያዎች ስለሆነ ያለኝ በመሆኑ በአግባቡ በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ መጠቀም አልቻልኩም፡፡

መ7፦ የሁሉም ተሟልቶ መገኘት ለቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም ትልቅ ጠቀሜታ አለው፡፡

መ8፦ ኧ . . . የቋንቋ ትምህርት መሣሪያዎቹን በአግባቡ በጥንቃቄ መጠቀም በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም ላይ የሚኖረውን ፋይዳ ያጎላል . . . ይህም ያለእነዚህ መሣሪያዎች መጠቀም ፋይዳ የሌለው መሆኑን ይጠቁማል፡፡

**ጥያቄ አስር**፦ የሚጠቀሙባቸውን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚያገኙት ከየት ነው? እንዴት ያገኟቸዋል ለመጠቀምስ የሚያጋጥምዎት ችግር አለን?

መ1፦ ራሴ በማዘጋጀትና ከተለያዩ የግብረሰናይ ድርጅቶች መምህራን ግንኙነት በመፍጠር ሲሆን የበጀት ችግር አለብን ዕራሱን የቻለ የቋንቋ መምሪያ ክፍል ከተሟላ ወንበሮቹ ጋር አለመኖር ችግር አለ፡፡ አላስፈላጊ የአመራር ችግር፡፡

መ2፦ ኧ ተማሪዎችን እንዲያመጡ በማዘዝ፣ ኧ . . . ዕራሴና ከግብረ ሰናይ ድርጅት የተወሰነ ገንዘብና መሣሪያዎች በስጦታ ስለአገኘን የበጀት ችግር ግን አሁንም በከፍተኛ ደረጃ

አለብን የቋንቋ መማሪያ ዕራሱን የቻለ ክፍል ችግር የትምህርት መርጃ መሣሪያውን ተጠቅማችሁ ወርውሮ በመባል የአመራር ችግር፡፡

መ3፡- ዕራሴና ከተለያዩ በጎፈቃድ ድርጅቶች በዕርዳታ የተገኘ ሲሆን የገንዘብና ዕራሱን የቻለ የቋንቋ መማሪያ ክፍል ችግር አላስፈላጊ የባለሙያ ትዕዛዝ፡፡

መ4፡- ኸ . . . ተማሪዎቼን በማስመጣት፣ ኸ . . . ዕራሴ በመወሰድና አጋዥ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች በመልካም የስራ ግንኙነት፡- የበጀት፣ ተጠቀማችሁ ወርውሩ መርጃ መሣሪያውን የሚባል አመራር እና . . . ደግሞም ኸ ራሱን የቻለ የቋንቋ መማሪያ ክፍል ችግር በአጠቃቀሜ ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡

መ5፡- ኸ . . . እኔ ዕራሴ በማምጣትና ለተለያዩ ድርጅቶች ፕሮጀክት ፕሮዛል በመቅረፅ ገንዘብና መሳሪያ በስጦታ (ራሱን የቻለ ያገኘን ሲሆን) የቋንቋ ትምህርት መስጫ ክፍል ስለሌለን ኸ . . . በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ላይ ትልቅ ጫና አሳድሮብኛል፡፡

መ6፡- ምንም እንኳን ተጠቅሜ እንድጥል ብታዘዝም እኔ ዕራሴ በማምጣት እጠቀማለሁ ኸ . . . እንዲሁም በጋራ ሁነን ፕሮፖዛል በመቅረፅ ከተለያዩ ድርጅቶች ገንዘብና መሣሪያን በስጦታ አግኝተናል፡፡ ነገር ግን የበጀትና የቋንቋ መማሪያ ራሱን የቻለ ክፍል ስለሌለን ችግር አለ፡፡ በትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም ላይ ይህ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡

መ7፡- ኸ . . . ተማሪዎችን እንዲያመጡ በማድረግ፣ ዕራሴ በማምጣት ከመንግሥትና መንግሥታዊ ካልሆነ ድርጅቶች በተሰጠ ዕርዳታ የተገኙ መሣሪያዎች ሲሆኑ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቀቀም ላይ የበጀትና ዕራሱን የቻለ የቋንቋ መማሪያ ክፍል አለመኖርና የተጠቀየቃችሁበትን አስወግዱ በመባላችን ለቀጣይ ስራና ለተነሳሽነት መቀነስ ምክንያት በመሆን ችግር ፈጥሮብኛል፡፡

መ8፡- ኸ . . . ተማሪዎቹን እንዲያመጡ በማድረግና ከመንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች በተገኘ ዕርዳታ የተገኙ መሣርያዎች ሲሆኑ ለቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ችግር በቂ በጀት አለመኖር፣ ኸ . . . ራሱን የቻለ ለቋንቋ መማር ማስተማር የሚውል መማሪያ ክፍል አለመኖር፣ መሣሪያዎቹን እንደልብ ለሚንቀሳቀስ አለመቻልና የተጠቀማችሁበትን የትምህርት መርጃ መሣሪያ አስወግዱ የሚባል አመራር ችግር ፈጥሮብኛል፡፡

**ጥያቄ አስራ አንድ**፡- በማስተማር ሙያ ላይ እያሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያን በተመለከተ የስራ ላይ ስልጠና ተካፍለዋልን? በማን አዘጋጅነት?

መ1፡- አልተካፈልኩም

መ2፡- አልተካፈልኩም

መ3፡- አንድ ጊዜ ተካፍያለሁ በትምህርት ጽ/ቤት አዘጋጅነት

መ4፡- አልተካፈልኩም

መ5፡- አልተካፈልኩም

መ6፡- ከአንድ ጊዜ በላይ ተካፍያለሁ በትምህርት ቤቱ አዘጋጅነት፣ በትምህርት ጽ/ቤት አዘጋጅነት

መ7፡- አልተካፈልኩም

መ8፡- አልተካፈልኩም

**ጥያቄ አስራ ሁለት**፡- ስለትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም በመምህራን መገምገሚያ ስለመስፈሩ ያለዎት አስተያየት፡፡

መ1፡- ጠቀሜታ የለውም ይህ የማስገደድ ሁኔታ እንዳለ ያመላክታል፡፡

መ2፡- ማስተማር ኧ . . . የህሊናና የሙያ ሥራ በመሆኑ አላስፈላጊ ነው ለመምህሩ ለዕራሱ ቢተው ይሻላል፡፡

መ3፡- ለማስተማር ሳይሆን መምህራን ነጥብ ለማግኜት ብቻ አላስፈላጊ ዝግጅት የሌለው ትምህርት መርጃ መሣሪያ እንዲጠቀሙ ያነሳሳል፡፡

መ4፡- ጥሩ ኧ . . . ነው ምናልባት ለነጥብ የሚጓጉ መምህራንን ወይም እንዝላል የሆኑትን ለማነሳሳት ያግዝ ይሆናል፡፡

መ5፡- ጥሩ ነው የመነቃቃትና ልምድ የመለዋወጥ ሁኔታ እንዲፈጠር ያግዛል፡፡

መ6፡- ማስተማር ሙያ ነውና ኧ . . . የሙያውን ሥራ ማቅለል ይመስለኛል፡፡

መ7፡- ከተነደፈው የትምህርት ዓላማና ዓላማውን ለማስፈፀም ከሚቀረፀው ይዘት አንፃር እንጂ ትምህርት መሣሪያ የሚታቀድና የሚጠቀም ከግምገማ ላይ ስለሰፈረ ባለመሆኑ ጥሩ አመለካከት የለኝም፡፡

መ8፡- ኧ . . . ይህ መጥፎ አመለካከት እነዲኖረኝ አድርጎኛል ጥሩና የተከበረውን ሙያ ለነጥብ ብሎ መጠቀም ስራውን እንደማርከስ ያደረገ ይመስለኛል፡፡

**ጥያቄ አስራ ሶስት**፡- በመማር-ማስተማር ሂደት በትምህርት መርጃ መሣሪያ ከተገለገሉ በኋላ የዕለቱ ትምህርት ለተማሪዎች ግልፅ መሆኑን እንዴት ያውቃሉ?

መ1፡- የዕለቱን ትምህርት በግምገማ ጥያቄ ምን ያህል እንደተረዱት በተሳተፏቸው እገመግማለሁ፡፡

መ2፡- በተለያዩ ክንውኖችና በጥያቄና መልስ፡፡

መ3፡- በክፍል ውስጥ በሚያደርጉት የዕርስ በርስ መስተጋብር እና ኧ . . . በሚያከናውኑት ተግባር ነው፡፡

መ4፡- በጥያቄና መልስ፡፡

መ5፡- በክፍልና በቤት ሥራ በሚያደርጉት ተሳትፎ፡፡

መ6፡- በጥያቄ፡፡

መ7፡- ተዛማጅ የሆኑ ሐሳቦችን በማንሳት፣ ጥያቄ በመጠየቅ፡፡

መ8፡- በጥያቄና መልስ፡፡

**ጥያቄ አስራ አራት**፡- በትምህርት ቤትዎ ትምህርት የማተላለፍበት ሬዲዮ አለ?

መ1፡- አዎ አለ፣ ኧ . . . ነገር ግን ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አገልግሎት አይሰጥም፡፡

መ2፡- አዎ አለ፣ ነገር ግን በአሁኑ ዘመን ያለው የሬዱዮ ስርጭት ለአማርኛ ቋንቋ ጊዜ አልመደበም፡፡

መ3፡- አዎ አለ፣ ነገር ግን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የስርጭት ፕሮግራም ለስነዜጋና ስነምግባር ትምህርት ስለተመደበ አሁን የቋንቋ ትምህርት የስርጭት ጊዜ የለውም፡፡

መ4፡- አዎ አለ፣ ይሁን እንጂ ለቋንቋው ትምህርት አገልግሎት አይሰጥም፡፡

መ5፡- አዎ አለ፣ ቢሆንም ባዶ የሬዲዮ ካሴት ታቅፈን ቀርተናል፡፡ ኧረ ተይኝ . . . ለአማርኛ ቋንቋ የስርጭት ጊዜ አልተመደበለትም፡፡

መ6፡- አዎ አለ፣ በብልሽት ምክንያት ለሁሉም የትምህርት ዓይነት አገልግሎት አይሰጥም ነገር ግን ለአማርኛ ቋንቋ የጊዜ ሰሌዳ ስለሌለው ብልሽቱ ባይኖርም አንጠቀምም፡፡

መ7፡- አዎ አለ፣ እንደ አስፈላጊነቱ በቴፕ አስገልብጠን መጠቀም ከቻልን ካሴቱ አለ እንጂ የሰርጭት ጊዜ ተነስቶበታል፡፡

መ8፡- አዎ አለ፣ የሬዲዮ ስርጭት ለሥነምግባርና ሥነዜጋ ስለዋለ የቋንቋው ስርጭት ጊዜ የለውም በቴፕ ካሴት ግን አስገልብጦ መጠቀም ይቻላል፡፡

**ጥያቄ አስራ አምስት እና አስራ ስድስት፡-** በትምህርት ቤትዎ ውስጥ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም የሚያገለግል ከሬዲዮ ሌላ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች (ለድምፃዊ፣ ለድምፃዊ እና ወእይታዊ) ለመጠቀም የሚያግዙ መሣሪያዎች አሉ? መምህራን ለምን አገልግሎት ያውሉታል? መሣሪያዎቹ እንዴት ተገኙ?

መ1፡- አዎ አለ፣ ኢንተርኔት፣ ቴሌቪዥን፣ ኮምፒውተርና ከአናት በላይ ፕሮጀክተር አሉን ለድራማና ሥነፅሁፍ ክበብ እንቅስቃሴ ይውላል ኸ . . . በመምህራን ጥረት ከጎንደር ሊንክ ኢንግላንድ ግብረሰናይ ድርጅት የተሰጠ ስጦታ ነው፡፡

መ2፡- አዎ አለ፣ ቴሌቪዥን፣ ኮምፒውተር፣ ኢንተርኔትና ከአናት በላይ ፕሮጀክተር አገልግሎት ለድራማና ሥነጽሑፍ ክበብ የሥራ እንቅስቃሴ ሲሆን መምህራን ባደረግነው መልካም ግንኙነት ጎንደር ሊንኪ ኢንግላንድ ግብረሰናይ ድርጅት በስጦታ ስጠን፡፡

መ3፡- አዎ አለ፣ ቴፐ፣ ኢንተርኔት፣ ኮምፒውተርና ቴሌቪዥን አሉን ለድራማና ሥነፅሁፍ ክበብ የስራ ዕንቅስቃሴና ለትምህርት ቤቱ መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች አገልግሎት ይሰጣሉ፣ ኸ . . . መንግሥትና የዳሽን ቢራ ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መምህራን የተለያዩ የማስታወቂያ ሥራዎችን በመስራታችን ለትምህርት ቤቱ በስጦታ ሰጠን፡፡

መ4፡- ኸ . . . አዎ አለ፣ ኢንተርኔት፣ ኮምፒውተርና ቴፐና ቴሌቪዥን ለድራማና ሥነጽሑፍ የሥራ ዕንቅስቃሴና ለትምህርት ቤት መምህራንና የአስተደደር ሠራተኞች የተለያዩ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ኸ . . . መንግስትና የዳሽን ቢራ ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከመምህራን ጋር ባደረጉት የተለያዩ ግንኙነቶች የተሰጠ ዕርዳታ ነው፡፡

መ5፡- ኸ . . . አዎ አለ፣ ቴፐ፣ ኮምፒውተርና ቴሌቪዥን ከአናት በላይ ፕሮጀክተር ከቀይ መስቀልና ከፀረ ኤች አይ ቪ ኤድስ ድርጅት መምህራን ፕሮጀክት ፕሮፖዛል በመቅረፅ በስጦታ የተገኘ ነው፡፡ ኸ . . . ለድራማና ለሥነጽሑፍ ክበብ የስራ እንቅስቃሴና ለአስፈላጊ የትምህርት ቤት የሥራ እንቅስቃሴዎች ያገለግላሉ፡፡

መ6፡- አዎ አለ፣ ኸ . . . ቴፐ ከአናት በላይ ፕሮጀክተር፣ ኮምፒውተርና ቴሌቪዥን ከፀረ ኤች አይ ቪ ኤድስ ድርጅትና ከቀይ መስቀል በዕርዳታ የተሰጠን ነው ለድራማና ሥነጽሑፍ ክበብ የሥራ ዕንቅስቃሴና አስፈላጊ የትምህርትቤት የሥራ እንቅስቃሴዎች ይከናወኑበታል፡፡

መ7፡- አዎ አለ፣ ቴፕ፣ ኮምፒውተር ከአናት በላይ ፕሮጀክተር ከፈረንሳይና ጎንደር የሁለት እህትማማቾች ከተማ ግብረሰናይ ድርጅት የተሰጠነው ለተለየዩ የትምህርት ቤት ስብሰባዎች ለክበባት የሥራ እንቅስቃሴ ያገለግላሉ፡፡

መ8፡- አዎ አለ፣ ከአራት በላይ ፕሮጀክተርና ኮምፒውተር ከጎንደርና ፈረንሳይ የሁለት እህትማማቾች ከተማ የዕርዳታ ሰጭ ድርጅት በስጦታ የተገኘ ነው፡፡ ኧ . . . ለክበባት የሥራ እንቅስቃሴና አስፈላጊ ለሆኑት የትምህርት ቤት የሥራ ክንውን ሁሉ እንጠቀምበታለን፡፡

**ጥያቄ አስራ ሰባት**፡- በትምህርት ቤትዎ የትምህርት መርጃ መሣሪያን ለመጠቀም የሚያግዙ የተመቻቹ የቴክኖሌጅ ውጤቶች አሉ?

መ1፡- አዎ በሚገባ አሉ፡፡

መ2፡- አሉ

መ3፡- አዎ አሉ

መ4፡- ሞልተዋል

መ5፡- በተገቢ ሁኔታ አሉ፡፡

መ6፡- ከመጠን ባለፈ ሁኔታ የተሟሉ ናቸው፡፡

መ7፡- በተገቢው መንገድ የተሟሉ ናቸው፡፡

መ8፡- አግባብ ባለው ሁኔታ የተሟሉ ናቸው፡፡

**ጥያቄ አስራ ስምንት**፡- የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ በትምህርትቤትዎ ሐሳብ የሚለዋወጧቸው መምህራን አሉ? በሙያዎትስ ላይ ምን ያህል ዕገዛ አድርጓል?

መ1፡- አዎ አሉ ጥሩ ዕገዛ ያደርግልኛል፡፡

መ2፡- አዎ አሉ በሚገባ እንጂ፡፡

መ3፡- አዎ አሉ በትክክል ጥሩ እገዛ አድርጎልኛል፡፡

መ4፡- አዎ አሉ በትክክል ጥሩ ዕገዛ አድርጎልኛል፡፡

መ5፡- አዎ አሉ በጣም ጥሩ እገዛ አድርጎልኛል፡፡

መ6፡- አዎ አለ ከፍተኛ ዕገዛ ያደርግልኛል፡፡

መ7፡- አዎ አለ፣ ተገቢ የሆነ እገዛ አድርጎልኛል፡፡

መ8፡- አዎ አሉ፣ ለሙያዬ ትልቅ እገዛ አድርገውልኛል፡፡

**ጥያቄ አስራ ዘጠኝ**፡- የዕለቱ የትምህርት ይዘት አስፈላጊ ነው ብለው የተጠቀሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያ ተማሪዎን ግራ ያጋባበት ጊዜ ይኖራል? የለም ካሉ ያላጋጠመወት ምክንያቱ ምን ይሆን?

መ1፡- የለም፣ ምክንያቱም ተገቢ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ስለምጠቀም፡፡

መ2፡- የለም፣ ለዕለቱ ትምህርት ተስማሚ የሆነውን ስለምጠቀም፡፡

መ3፡- የለም፣ ግራ እንዳይጋቡ ተገቢነት ያለው የትምህርት መርጃ መሣሪያ ሰለምጠቀም፡፡

መ4፡- የለም፣ በሚገባ ተገቢ በሆነ መንገድ ስለምጠቀም፡፡

መ5፡- የለም፣ በሚገባ አቅጄ ስለማስተምር፡፡

መ6፡- የለም፣ አግባብ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ሰለምጠቀም፡፡

መ7፡- የለም ተገቢ የሆነ የመማር-ማስተማር ሂደት ስለማካሂድ፡፡

መ8፡- የለም ግራ የማያጋባ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ስለምጠቀም፡፡

**ጥያቄ ሃያ**፡- የአማርኛ ቋንቋን የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ ያጋጠመዎት ችግር አለ?

መ1፡- ኧ . . . አዎ አለ፣ የመማሪያ ክፍል ራሱን የቻለ አለመኖር፣ የበጀት፣ የመርጃ መሣርያውን ተጠቅማችሁ ጣሉ የሚል አመራር፡፡

መ2፡- አዎ አለ፣ የመማሪያ መሣሪያዎች አለመኖር፣ ራሱን የቻለ የመማሪያ ክፍል አለመኖርና የበጀት ችግር፡፡

መ3፡- ኧ . . . አዎ አለ፣ የበጀት ችግር፡- የመማሪያ መሣሪያዎች ተሚልተው አለመገኘት ራሱን የቻለ የቋንቋ መማሪያ ክፍል አለመኖርና ተጠቀማችሁ ጣሉ የሚለው አመራር፡፡

መ4፡- አዎ አለ፣ የበጀት ችግር፣ ራሱን የቻለ የመማሪያ ክፍል አለመኖር፡፡

መ5፡- ኧ . . . አዎ አለ፣ ተጠቀማችሁ ጣሉ የሚባል አመራር የአጠቃቀም ችግር ያመጣል የመማሪያ ክፍል ራሱን የቻለ አለመኖር፣ የአጠቃቀም ችግር አለው የበጀት አለመኖር ችግሮች ናቸው፡፡

መ6፡- ኧ . . . የትምህርት መሣሪያዎች አለመኖር፣ ተጠቀማችሁ ጣሉ የሚለው አመራር፣ ራሱን የቻለ የቋንቋ መማሪያ ክፍል አለመኖር፣ የበጀት ችግር፡፡

መ7፡- አዎ አለ፣ ራሱን የቻለ የቋንቋ ክፍል አለመኖር፣ የበጀት ችግርና የትምህርት መሣሪያዎች አለመኖር፡፡

መ8፡- ኧ . . . አዎ አለ፣ የበጀት ችግር የትምህርት መሣሪያዎች አለመኖር ችግርና ራሱን የቻለ የቋንቋ መማሪያ ክፍል የለመኖር ችግር፡፡

**ጥያቄ ሃያ አንድ፡-** አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙበት የትምህርት መርጃ መሣሪያ ዓይነት ምን ዓይነት ነው? ለምን?

መ1፡- የሚታዩ ነው፡- ለመጠቀምም ሆነ ለማንቀሳቀስ አመች በመሆኑ፡፡

መ2፡- የሚታዩ ነው፡- ለተማሪዎች ግልፅ ሆኖ ስለሚቀርብ፡፡

መ3፡- የሚታዩ ነው፡- ለማስተማር አመች በመሆኑ፡፡

መ4፡- የሚታዩ ነው፡- ለተማሪዎች ግልፅ ሆኖ ስለሚቀርብና ለአያያዝ ስለሚመች፡፡

መ5፡- የሚታዩ ነው፡- ለአያያዝ ስለሚመችና ለተማሪዎች ተስማማ በመሆኑ፡፡

መ6፡- የሚታዩ ነው፡- ለተማሪዎች ግልፅና በቀላሉ ስለሚረዱት፡፡

መ7፡- የሚታዩ ነው፡- በሚገባ ግልፅ እንዲሆን ትምህርቱ ቀላል እንዲሆን ስለሚያግዝ፡፡

መ8፡- የሚታዩ ነው፡- ቀላል በሆነ መንገድ ስለማዘጋጅ ለማስተማርም ምቹ ስለሆነ፡፡

**ጥያቄ ሃያ ሁለት**፡- አብዛኛውን ጊዜ የትምህርት መርጃ መሣሪያ የሚጠቀሙት የትኛውን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ለማስፈፀም ነው? ለምን?

መ1፡- ሁሉንም ለምን ለሚለው የቋንቋውን ትምህርት በዕኩል ሰለምመለከተው፡፡

መ2፡- ሁሉንም፡- የትምህርት መርጃ መሣሪያ አስፈላጊ ከሆነበት ሁሉ እንጂ አልመርጥም፡፡

መ3፡- ሁሉንም፡- የቋንቋ ትምህርት ዓላማን ለማስፈፀም የሚያገለግደውን፡፡

መ4፡- ሁሉንም፡- የተነደፈውን ትምህርት በተገቢ መንገድ ማስተማር ስለማያስፈልግ፡፡

መ5፡- ሁሉንም፡- ለተማሪዎች ግልፅ እንዲሆንና የቋንቋውን ትምህርት የሚያስጨብጥ፡፡

መ6፡- ሁሉንም፡- ለሁሉም አላማ እኩል ትኩረት ስላለኝ፡፡

መ7፡- ሁሉንም፡- ለማስተማር ትምህርቱን ግልፅ ለማድረግ፡፡

መ8፡- ሁሉንም፡- ተገቢ በሆነበት ቦታ ሁሉ፡፡

**ጥያቄ ሃያ ሶስት**፡- ለወደፊት የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ መሆንና መደረግ ሰለአለበት ሁኔታ ያለዎት አስተያየት ምንድን ነው?

መ1፡- የተሟላ የቋንቋ መማሪያ ክፍል ከነውሉ ወንበሩ እንዲዘጋጅ ቢሆንና ለመምህራን የሥራ ላይ ሥልጠና በየጊዜው ቢሰጥ፡፡

መ2፡- ኸ . . . ለመምህራን የሥራ ላይ ሥልጠና በየጊዜው ቢሰጥ ነፀ ራሱን የቻለ የቋንቂ መማሪያ ክፍል ቢኖር፡፡

መ3፡- ኧ . . . ለወደፊቱ የተሟላ ራሱን የቻለ የቋንቋ መማሪያ ክፍል ቢኖርና ለመምህራን የሥራ ላይ ስልጠና በየጊዜው ቢሰጥ፡፡

መ4፡- አስፈላጊ የሆነ የሥራ ላይ ሥልጠና ቢሰጥ የተሟላ ራሱን የቻለ የቋንቋ መማሪያ ክፍል እንዲኖር ቢደረግና ማስተማሪያ መሣሪያዎች ተሟልተው ቢቀርቡ፡፡

መ5፡- የተሟላ የማስተማሪያ መሣሪያ በወቅቱ ለመምህራን እንዲደርስ ቢሆን የተሟላ ራሱን የቻለ የቋንቋ መማሪያ ክፍል እንዲኖር ቢደረግ ለመምህራን በየጊዜው የሥራ ላይ ሥልጠና ቢሰጣቸው፡፡

መ6፡- የትምህርት መሣሪያዎች በተገቢው ጊዜ ለመምህራን እንዲደርስ ቢደረግ፣ የተሟላ የቋንቋ መማሪያ ክፍል ራሱን የቻለ ቢዘጋጅ አላስፈላጊ አመራር ለመምህራን ባይሰጥ፡፡

መ7፡- ራሱን የቻለ የቋንቋ መማሪያ ክፍል ከተገቢ መሣሪያዎች ጋር ቢዘጋጅ ለመምህራን የሥራ ላይ ሥልጠና በየጊዜው ቢሰጣቸው፡፡

መ8፡- ኧ . . . ለመምህራን ከዘመናዊ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ጋር በተገቢ ሁኔታ እንዲላመድ የሥራ ላይ ሥልጠና በየጊዜው ቢሰጣቸው አላስፈላጊ የሆኑ አመራሮች ለመምህሩ ባይሰጡና ራሱን ችሎ እንዲሰራ ቢተው የትምህርት መሣሪያዎች በጊዜው ለመምህራን እንዲደርሱ ቢደረግ፡፡